# ጥቁር ደም

ከአንዳርጌ መስፍን

# ጥቁር ደም

[redacted]

ከአንዳርጌ መስፍን መ. ኢ.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
All Rights Reserved

መጀመሪያ እትም 1980
ሁለተኛ እትም 1981
ሦስተኛ እትም 1981
አራተኛ እትም 1981
አምስተኛ እትም 2002

አከፋፋይ 091143 56 70
091148 01 82

# አ ን ድ

ገና ህፃን ሳለሁ ጀምሮ አያቴ አዘውትረው የሚያጫውቱኝ ስለ እናታቸው ታሪክ ነበር ። በተለይ ማታ ማታ ቁጭ ስንል በተረት ፈንታ የሚተርኩልኝ የናታቸውን ታሪክ ነበር ። ብዙ ካወሩኝ በኋላ ፣ "ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!" ይሉና ከንፈራቸውን በሀዘን ይመጡታል ። ይኸ አይነት አባባላቸው አዘውትረው የሚያሰሙት ነው ።

"የማያልፍ ነገር የለም ፤ እናቴም አልፈዋል ፤ አፈሩ በልቷቸዋል ፤ ደግነቱ ነፍሳቸው ለገነት መብቃቷ ነው ። ጥርጥር የለውም ፤ ይጠድቃሉ ። በሰማይ የሚጠድቅ በምድር ያስታውቅ የል ፤ ተመቃብራቸው ላይ አንዲት ጥድ በቅላለች ። አሁንማ ትልቅ ዛፍ ሁናለች ። ልምላሚዋ ተሌሎቹ የጥድ ዛፎች ሁሉ የተለየች ናት ። ለቁም ነገር ስትበቃ የቅድመ አያትህን መቃብር ማየት አለብህ ። የተባረክህ ፣ የተመረቅህ እንድትሆን ።"

አያቴ የናታቸውን ነገር ባነሱ ቁጥር በሀሳብ ወይንም በትዝታ ልጓም ተስበው እኔ ወደማላውቀው አለም ጭልጥ ይላሉ ። እርሳቸው አርጅተው ሞትን እየተጠባበቁት እያሉ ከሞቱ ብዙ አመት ያለፋቸውን እናታቸውን እያነሱ ያን ያህል መጨነቃቸው ለምን ይሆን? ኋላማ እኔም በቅድመ አያቴ

ታሪክ እየተሳብኩኝ ተረቱን ትተው እሱን እን ዲተርኩልኝ እጠይቃቸው ጀመር ። እርሳቸውም ደስ ይላቸውና ፣ "አየ ፣ ስመኘው!" ይሉና እራሴን እየደባበሱ ይተርኩልኛል ። ሲያወሩ ሰውን የመ ሳብ ተሰጥኦ ነበራቸው ።

"እናቴ ነፍሳቸውን ይማረውና ሰው በልቶ የሚጠግብ አይመስላቸውም ፤ ልግስናቸው ተልክ ያለፈ ነበር ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል !"

አያቴ ምን ጊዜም ቢሆን የሚያነሱት ፣ የሚ ጥሉት እናታቸውን እንጅ አባታቸውን አይደለም ። እንደሚሉት ከሆነ እርሳቸው ልጅ ሳሉ ነው የሞ ቱባቸው ።

"መቼ ነው የቅድመ አያቴን መቃብር የሚ ያሳዩኝ?"

"ትልቅ ስትሆን ፣ ስታድግ ነዋ! ዛሬ ገና ነህ ፤ አገሩ ገደል ስለሆነ መውጣት ፣ መውረድ አትችልም።"

"ግዴለዎትም እችላለሁ!"

"የመስቀች ገደል እንዲህ በዋዛ! እንኳን ለልጅና ላዋቂም ቢሆን ላለመደው ሰው መከራ ነው ። እንደ ዝንጀሮ ተሙጨልጭሎ ነው ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!"

"ለምን ነው ቅድመ አያቴን ተገደል ስር የቀበራችኋቸው? ባገሩ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የለም?"

“እሳምሮ አለ እንጂ ፤ መስቀች መዳህኒ አለም ። አካለ ክርስቶስ የሚቀበር ሰው ግን የሚጠድቅ ነው ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!”

“አካለ ክርስቶስ ምንድናቸው?”

“ጣድቅ ናቸው ።”

“ጣድቅ ምን ማለት ነው?”

“ጥሩ ስራ የሰራ ፣ አማላጅ የሚሆን ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!”

አያቴ አንዳንድ ጊዜ የሚሉኝ አይገባኝም ።

“የኔ የናትህ አገር እንዴት ያለ መሰለህ ፤ ላው አምባ ሆኖ ዙሪያውን በገደል የተከበበ ነው ። ተወልደው ታደጉበት በስተቀር መግቢያ መውጫው አይታወቅም ። ጣሊያን እንኳን በግሩ አረገጠውም ።”

“አገረዎ ጥሩ ተሆነ ተዚህ ለምን መጡ?”

“ልጄን ብዬ ነዋ! እናንተን ብዬ ።”

“ተዚያ ሌላ ልጅ የለዎትም?”

“ታገሬ ሌላ ልጅ ቢኖረኝ ያንተን አባት ተከትዬ እመጣ ነበር? ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!”

“እታለም ምነዎት ናት?”

“እሷማ የታናሽ እህቱ ልጅ ናት ። እናቷ በልጅነቷ ሙታባት አሳድጌያት እንጂ አልወለዳትም ። እሷም መሀን ሆናው ቀረች ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!” ብለው በሀዘን ከንፈራቸውን መጠጡ ።

እያቴ ትውልድ አገራቸውን ፣ መስቀችን ትተው ታች ጋይንት የመጡት ልጃቸውን ፣ የኔን አባት ተከትለው ኖሯል ። ይህን ነገር ከናቴ ጋር ሲኳረፉም ይናገሩታል ።

“ባልሽን ተከትየ ነው የመጣሁት ። አንችም ወንድ ልጅ ወልደሻል ፤ የጅሽን አትጭው!” ይሉና ማቴን ያወርዱባታል ።

“ይቅር ይበሉኝ እናቴ! እኔ አላስከፋዎትም ፤ እርግማንም አይርገሙኝ” ትልና ተግራቸው ላይ ወድቃ ትማፀናቸዋለች ። እናቴ እያቴን ተልክ አልፋ ትፈራቸዋለች ። አባቴም ቢሆን ተጠንቅቆ ነው ። እያቴ ትንሿ ነገር ታስቆጣቸዋለች ። ቶሎ ብለው ሆድ ይብሳቸዋል ። ተኔ ጋር ግን አንድ ቀን ብቻ ተጣልተናል ። መቋጠሪያቸውን ጥየባቸው እርር ድብን ብለው ተናደው ፣ “ፈልጊ ብየሻለሁ!” እያሉ እናቴን ያጣድፏታል ። እናቴ ሽርንቁላው ሁሉ አልቀራትም በንጨት ትጭራለች ።

“አሁን እኔን ምን አድርጊ ነው የሚሉኝ፤ ያጥላቀቁት እራስዎ ነዎት !” እናቴም ክፉኛ አኩርፋለች ። ይዛ እንዳትገርፈኝ ተወደ በሩ በኩል ፈንጠር ብዬ በድንጋጤ ቁሜ እመለከታለሁ ።

መቆጣሪያው ቢወጣ ፣ ቢገባ ጠፍቶ ቀረ ። በዚሁ የተነሳ ፣ "ታጠገቤ እንዳትደርስ!" ብለው አኮረፉኝ ።

ባጠፋሁት ጥፋት አያቴ አኩርፈውኝ ይቀፉ ይሆን፣ እያልኩ ስሰጋ በማግስቱ ምሽት ፣ "ስመ ኘው! ናስቲ ታጠገቤ ተቀመጥና አጫውተኝ" አሉኝ ። እሩጩ ሄጄ ታጠገባቸው ተቀመጥኩ ። መቁጠሪያው ዳግመኛ አልተነሳም ።

"ለምን ነው ስመኘው ያሉኝ?"

"እኔ አባትህን ብቻ ነው የወለደሁት ። ምነው ወንድ ልጅ በወለደልኝ ስል አንተ ተወለ ደህ ። የተመኘሁት በመድረሱ ስመኘው አለሁህ ። ጥሩ ስም ነው ያወጣሁልህ ። አሁን ደሞ ሌላ ነው ምኞቴ ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!"

"ምንድን ነው?"

"አንተ ስታድግልኝ ፣ አንተን ይዤ አገሬን እገባለሁ" አሉኝ ፣ በምኞት ደስ ብሏቸው ። እንደ ተመኙት ግን ሳይሆን ቀረ ።

# ሁለት

ታባቴ ቤት አጠገብ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ተሰራና ተዚያ ገባሁኝ። አያቴ ፈቃደኛ አልነበሩም።

"የፈረንጅ ትምህርት ፤ እኔ እንድትማር የፈለ ገሁት ያባት አድሩን ፣ የቤተ ክህነቱን ነበር ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!" እያሉ በብርቱ ይነቅ ፉት ጀመር ። እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ገና ትምህርት ቤቱ ሲቆ ረቆር ጀምሮ አልተቀበሉትም ነበር ።

አያቴ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ተገባሁ ጀምሮ ለኔ ያላቸው ፍቅር እንደ ቀድሟቸው አልሆን አለ ። የቅድመ አያቴን ታሪክም ማውራቱን ችላ እያሉት መጥተዋል ። እኔም ብሆን እንደ ቀድሞየ አይደለሁም ። ለተረቱም ሆነ ለቅድመ አያቴ ታሪክ እምብዛም ሆኛለሁ ።

አያቴ ደብተርና እርሳስ ይዤ ስቦጫጭር ሲያዩኝ ያሽሟጥጡኛል ፤ "እየ ፣ ጥሁፍቴ! እንዲህ አድርጎም ጥሁፍ የለ!" ይሉኛል ። መፅሀፍ ይዤ እያነበብኩ ከሆነም ፣ "ጠጣው ፣ ዝንጀሮው ፣ ቢራቢሮው ፥ እንቁራሪቱ አይደል ትምህርታችሁ? እንደ እንቦሳ ስትፈነጥዙ ፣ ኳስ ስታነጥሩ ነው የም ትውሉት ። ትምህርቱ እንጂ እሱ ነው ። የኛ ትም

ህርት፣ያባት አደሩ ቢሆን ኖሮ ወይ ታንገት ቀና ። ቀልድ የት አለና ፤ በወይራ ልንብጭ ነው ። ልጅን እነ መምሬ ይሁን፣እነ መሪጌታ መንበሩ ያስተም ሩት እንጂ ። ዋ፣ሁሉም ነገር ያልፋል!” በማለት ያለፈውን እያነሱ ይደረድራሉ ።

እናቴም እንደ አያቴ ፈቃደኛ አልነበረችም ። ብቻ ሀሳባቸው ይለያያል ፤ አያቴ ዘመናዊ ትምህ ርት መማሬን ነው እንጂ የጠሉት የቤተ ክህነቱን እንድማር ይፈልጋሉ ። እናቴ ግን ጭራሹን ትም ህርት የሚባል ነገር አትፈልግም ።

“ቅሪላ ስታለፋ ውለህ መቆያ (መክሰስ) ስትል አታፍርም? እጀን ይሰበረው! ያቀመስሁህ እንደሆነ!” ትለኛለች ፣ ከትምህርት ቤት መልስ መቆያ ያልኳት እንደ ሆነ ።

አባቴ ብቻ ነበር ዘመናዊ ትምህርት እንድ ማር ፈቃደኛ የነበረው ። ዘመድ ልጠይቅ እያለ ጎንደርና አዲስ አበባ ስለሚመላለስ በዚያም ላይ ዳዊት የደገመ ስለ ሆነ ደስ ያለው እርሱ ብቻ ነበር ። አንዳንድ ቀን ተስራ መልስ አረፍ ሲል ፣ “ናስቲ የተማረኸውን አሳየኝ” ይለኛል ። ደብተ ሬን ይገር ታጠገቡ እቀመጣለሁ ። ደብተሬ አንዲት ብቻ ስለሆነች አማርኛውም ሂሳቡም ባንድ ላይ ድብልቅልቅ ብሎ ሲመለደት ያስቸግራል ። አልነበ በው ሲል ፣ “ለይተህ ነው መጣፍ ፣ ዶሮ የጫረው አታስመስለው ። እስቲ ደግሞ መጥሀፍህን እንየው ፤ ምን ምን ይተርካል?” ይላል ።

"እምን ፣ እሱን አሳየኝ በለው ። ጠጣው ፣ ዝንጅሮው. . .እረ ስንቱ ፤ ቁም ነገር የለበትም እንጂ የሌለው ጉድ የለ" ይላሉ አያቴ ፣ ጀርራቸውን ጣል አድርገው ሲያዳምጡን ይቆዩና ።

አያቴ ፡ "ጠጣው ፣ ዝንጀሮው ፣ እንቁራሪቱ. . ." እያሉ የሚያጥላሉትን ያንደኛ ክፍል የሳይንስ መፅሀፌን አምጥቼ እሰጠውና ታጠገቡ በርከክ ብዬ እኔም እመለከታለሁ ። አባቴ ከማንበብ ይልቅ ስእሎቹን ቢያይ ነው ደስ የሚለው ። አንዳንዶቹን ስእሎች ሲያይ በመገረም ሳቅ ይላል ። እንዲህ እያለ ወደ መሀል ሲገባ ፣ "ዝንብ ጠላታችን ናት ፤ ግደሏት!" የሚል በጉልህ የተፃፈበትን ያያል ። የዝንቧም ስእል ክንፎቿን ዘርግታ ፣ በግሮቿ ቆሻሻ ነገር ተሸክማ ትታያለች ። አባቴ ትኩር ብሎ እያየ ፣ "ዝንብ ስትገድሉ ነው እንዴ የምትውሉት? ለመሆኑ የዝንብ ጠላትነቷ ተምኗ ላይ ነው?" ይለኛል ፣ ሳቅ ብሎ ። በዚያን ጊዜ ዘርዝሬ ለማስረዳት እቸገር ነበር ።

"ደሞ ዝንብም አለችበት? እየውልህ እንግዲህ የነሱን ትምህርት ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፉል!" ይላሉ አያቴ ፣ የሽሙጥ ሳቅ እየሳቁ ።

አያቴ ትምህርቴን እያናናቁ ሲያስቸግሩኝ ጊዜ አንድ ቀን ምሽት ፣ "እማ ፣ ለምን ነው ትምህርቴን የሚንቁብኝ?" ስል ጠየኳቸው ።

"የካቶሊክ ትምህርት ነው ብዬ ነዋ!"

"ካቶሊክ ምን ማለት ነው?"

"ተዚያው አስተማሪህን ጠይቀው ፤ እሱ ይነግርሀል" አሉኝ ።

በማግስቱ አስተማሪየን ጠየኩት ።

"ማነው እንደዚህ ያለ ጥያቄ ጠይቅ ያለህ" አለኝ ፣ ቆጣ ብሎ ።

"አያቴ ናቸው" አልኩት ።

"ወገኛ ህዝብ! ከዚያው እርሳቸው ይንገሩህ" ሲል እርሱም ጥያቄየን በዚሁ ዘጋብኝ ።

እኔ ደግሞ አንድ ነገር ጠይቄ መልሱን ካላገኘሁ እረፍት የለኝም ።

ማታ አያቴን ፣ "እማ አስተማሪ የን ብጠይቀው አያትህ ይንገሩህ አለኝ ።"

"ምኑን?" አሉኝ ፣ እረስተውት ኖሮ ።

"ካቶሊክ ያሉኝን?"

"አየ ፣ የልጅ ነገር! ለካ ገና ህጻን ነህ ። ተቤት የተወራው ሁሉ ውጭ ይወራል አሉህ? ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!" በማለት አዘኑብኝ።

"ጠይቀው አላሉኝም ነበር?"

"በል እረፍ! ደሞ ብለህ ብለህ ተማላውቀው ሰው ጋር ታጣላኝ! ሁለተኛ እንደዚህ ያለ ነገር ይድገምህና ላባትህ ነግሬ ነው የማስለበልብህ" በማለት በብርቱ አስጠነቀቁኝ ።

እያቴ ተለት ወደ ለት በትምህርቴ ላይ ያላ ቸው ጥላቻ እየጠነከረ ሄደ ። ምን ጊዜም ቢሆን ከትምህርት ቤት ስመለስ ታላሽሟጠጡኝ አይሆን ላቸውም ።

"የኛ ተማሪዎች ፤ ምንድን ነው የሚሏችሁ ይሆን? እንኮላ! እውነትም እንኮላ! ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!" ይሉና ደረቅ ሳቅ ይስቃሉ ።

"የለም እማ ፤ እንኮላ አይደለም የምንባለው።"

"ምንድን ነው የምትባሉት ዛዲያ? እንኮላ ናችሁ እንጂ"

"የምንባለው ፤ ያስኮላው ተማሪ ሽታው ሎሚ ሎሚ ነው ።"

"እንዲህ አድርጎም የሎሚ ሽታ የለ" ይሉና አሁንም ደረቅ ሳቅ ይስቃሉ ።

"የናንተን ተማሪዎች ደሞ የምንላቸውን ልን ገረዎ?"

"እስቲ ንገረኝ ፤ ደሞ ምን ልትሏቸው ይሆን?"

"የቄስ ተማሪ ዘኬ አባራሪ ፣ ኮቸሮ ለቃሚ ነው የምንላቸው ።"

"ስድብማ ማን ብሏችሁ ፤ ይህንን አይደል ስትማሩ የምትውሉት" ይላሉ ።

ተዚህ ላይ መሳቁን ትተው ፊታቸው ቅሬታ ይለብሳል ።

ዘመኑ፡ መጨረሻ ታንደኛ ክፍል ወደ ሁለተኛ ክፍል ስዛወር ከክፍሌ አንደኛ በመውጣቴ አንዲት ሹራብ ተሸለምኩኝ ። ሹራቧ ቀይ ስለሆነች አይን ትስብ ነበር ። ተዚህ በኋላ አያቴ ማሽሟጠጡን ተውኝ ። ብቻ አንዳንድ ጊዜ ቅር መሰኘታቸው አልቀረም ። ሳባቴ ፣ "ይኽ ልጅ ያባት አደሩን ቢማር እንዴት ያለ ቀለም ተቀባይ ይሆን ነበር ። ዛዲያ ምን ይሆናል ወስደህ ተማይረባ ትምህርት ቤት ዶለኸው" በማለት ይፀፀታሉ ።

በትምህርቴ አድጌ ያንደኛ ደረጃን ጨርሼ ወደ አውራጃው መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነፋስ መውጫ ሄድኩኝ ።

በታህሳስ ፣ ለልደት በአል ትምህርት ቤት ተዘግቶ ስሄድ ፣ አያቴ ተመሀል ቀየው ነጭ በነጭ ለብሰው ፣ አዲስ ያስገዙትን ነጭ መቁጠሪያ ይዘው ፀሎት ሲያደርሱ ነበር የደረስኩት ። ገና ሲያዩኝ የሚወዱትን ፀሎት አቋርጠው ፣ "ስመኘው!" አሉኝ ፣ ተተቀመጡበት ለመነሳት እየተንገዳገዱ ። እሩጬ ሄጄ አቀፍኳቸው ። አገላብጠው ሳሙኝ ። እናቴም ተቤት ወጥታ ተሳመችኝ በኋላ ወደ ቤት ገባን ።

እናቴ እንጀራ አቅርባልኝ ስበላ አያቴ ታጠገቤ ተቀምጠው አይን አይኔን ያዩኝ ነበር ። በጣም መናፈቃቸውን እስተያየታቸው ይገልፃል ። ጥርሶቻቸው ለዛቸውን አላጡም እንጂ አያኖቻቸው ፍዝዝ ብለው ፣ ፊታቸው ተጨማዶ ፣ መስመር

መስመር አበጅቷል ። እርጅና ጉዙን ጠቅልሎ ወድቆባቸዋል ።

ማታ የቅድመ አያቴን ታሪክ እንዲተርኩልኝ ጠየኳቸው ።

"ምን ዋጋ አለው ፤ እናቴ ያገር ዛፍ መጠ ለያ ፣ ለተቸገረ ደራሽ ፣ ለታረዘ አልባሽ ፣ ትልቅ እመቤት ነበሩ ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!"

"መቼ ነው ታዲያ የቅድመ አያቴን ባድማ የሚያሳዩኝ? አገረዎትንም ልየው ።"

"ተንግዲህ ወዲያማ ምኑን አየኸው? ከንቱ ሆነ! ዋ፣ሁሉም ነገር ያልፋል!" አሉ በቃከተ እንጋገር ። በኔ ጨርሶ ተስፋቸው ተሟጧል ።

የእረፍት ጊዜየን ጨርሼ ወደ ነፋስ መውጫ ለመሄድ ስነሳ አያቴ ያለ ወትሯቸው እንባ አቀረሩ ።

"ምነው እማ? በዝጉኮ እመጣለሁ ።"

"ገና እስከ ሰኔ? በሰኔ አይደል የምትመጣው?" አሉኝ ፣ ሰኔ የብዙ አመት ያህል እርቋቸው ።

"አዎን ፣ በሰኔ አንደኛዬን የምመጣበት ነው ። ተዚያ ወዲህም በየወሩ ስንቄን ለመውሰድ እመጣ ለሁ ።"

"ኤዲያ! ይህ ሁሉ ከንቱ ነው ። ይልቅ ለቁም ነገር ስትበቃ የቅድመ አያትህን ባድማ መስቀች ሄደህ እንድታየው ። ሲሆን ሚስት አግብ

ተህ ፣ ተዘያው ቤት ሰርተህ ስማቸውን አድሰው ። አባትህ እንደ ሆነ ለንዲህ አይነቱ ነገር ግዴለውም። ‘ወንድ ልጅ ያባቱን አገር አይለቅም’ የሚል ፈሊጥ አለው ። እኔ መቼም ልጅ ብዬ ወጥቸ መቅረቴ ነው ። ላካለክርስቶስ አፈር አልበቃሁም ፤ ተናቴ ጎን አልተቀበርሁም ። ተዚህ እሬሳ ተሸክሞ መስቀች ድረስ የማይሆን ነው ። ለልጂም እንደዚህ ያለውን ነገር ተናዝዤ ችግር አልፈጥርበትም ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፉል!” አሉና እንባቸውን እርግፍ እያደረጉ ሳሙኝ ። እኔም የርሳቸውን እንባ ሳይ ጊዜ እንባዬ መጣብኝና አለቀስኩኝ ።

“የምን መላቀስ ነው እቴ! ነገ ተመልሶ ለሚመጣው ነገር ። ነፍስ መውጫ ዳር አገር ሆነ እንዴ?” በማለት እናቴ ተቆጣቻቸው ።

ተሰናብቻቸው ሜዳውን ጨርሼ ቁናታውን ስያያዝ መለስ ብዬ ሳያቸው ከቆሙበት አልተነ ቃነቁም ፤ ባይኖቻቸው ይከተሉኛል ። አያቴ ለምን እንደዚያ ሀዘን እንደ ገባቸውና ተስፋ እንደ ቆረጡ አልገባኝም ። አያቴ ሳውቃቸው ብርቱና ጠንካራ ሴት ነበሩ ። በመጀመሪያው ፣ በመስከረም ስለያቸው እንኳን ይህን ያህል አልባቡም ። ዛሬ ግን ክፉኛ ተሸበሩ ።

# ሶ ስ ት

ታንድ ወር በኋላ ቀለቤ አልቆብኝ ለማምጣት ስሄድ ያባቴ ቤት እንግዳ ነገር ሆኖ አገኘሁት ። ያለ ወትሯቸው አያቴም ተመሀል ቀየው የሉም ። እናቴ በር ድረስ መጥታ ተቀበለችኝ ። ፊቷ ሁሉ በሀዘን ጠውልጓል ። እታለም የምላት ያያቴ የት ንሽ እህታቸው ልጅ ከመስቀች መጥታ ኖሮ ተወደ ቤት ብቅ አለች ። እኔን ስታይ ጥርሶቿ ተገ ለጡ ። እንደ አያቴ ውብ ጥርሶች አሏት ። ድሮ ሳውቃት ፀጉሯን ቁንዳላ (ስሬት) ነበረች ። የዚያን እለት ግን ትኩስ ልጭት ነች ። አያቴን ተከትላ እሷም ስሙኘው ነው የምትለኝ ።

“ስሙኘው! ናስቲ ሳመኝ ፤ ጎርምሶ የል እንዴ!” ብላ እያገላበጠች ሳመችኝ ። አክስቴንና እናቴን ተከትዬ ወደ ቤት ስገባ ቤቱን እንግዳ ሞልቶ ኃል ። ተሩቅ አገር የመጡ ዘመዶቻችን ሁሉ አሉ ። ሁሉም እየተቀባበሉ ተሳሙኝ በኋላ ታክስቴ አጠገብ ተቀምጬ የቀረበልኝን እንጀራ እየበላሁ አይኖቼ ቢቃብዙ አያቴ የሉም ። የት ሄደው ነው ብዬ ለመጠየቅም ፍራት ፍራት አለኝ ። ሁሉም የሚጠብቀው የኔን በልቶ ማብቃት ነው ። በልቼ እንዳበቃሁ እናቴ ሞሰቡን አንስታ ወደ ጓዳ አስ ቀመጠችና ስትመለስ ፤ “እናቴ ፣ እመቢቴ!” እያ

ለች ልቅሶዋን ለቀቀችው ። አባቴም ማልቀስ ያዘ ። እክስቴ እንገቴን አቅፋ ይዛ ፤ "እያትህ ፤ አቀማጥላ ያሳደገችህ ሞተች!" ብላኝ እርሷም ታለቅስ ጀመር ። ተቤት ያለው ሰው ሁሉ ልቅሶ በልቅሶ ሆነ ። እኔ ግን በድንጋጤ ደርቄ ቀረሁ ። እክስቴና እናቴ እፍር አሉ ። እነርሱ እርምጥምጥ ብሎ ያለቅሳል ብለው ገምተው ኖሯል ። ያልጠበቁት ነገር ሆነባቸው ።

"በሉ በቃችሁ ዝምበሉ ፤ ለሳቸው ማልቀስ አይገባም ። በድሜቸው ነው የሄዱት ። ነፍሳቸውን በሰማይ ይማረው" አሉ ፤ አንዱ እጎታችን ። ማንም አላንገራገረም ፤ ሁሉም በጨርቁ ጫፍ እንባውን ይጠራርግ ጀመር ። እኔ ግን ምኑን እጠርገዋለሁ? እንገቴን ደፍቼ ፀጥ አልኩኝ ። የቤቱ ሰው ሁሉ ታዘበኝ ።

እያቴ ፤ 'ልጅ ብዬ ታገሬ ወጥቼ መቅረቴ ነው ። ዋ ፤ ሁሉም ነገር ያልፋል!' እንዳሉት አለፉ ። ሞት ለካ እንደዚህ ቅርብ ነው ። ለናታቸው እንደዚያ ሲያዝኑ እርሳቸውም አረፉ ። በምን ምክንያት እንደ ሞቱ አልጠየኩም ። ብቻ ሌሊት እናቴ ላክስቴ ለሶስት ቀናት ያህል ብርድ ብርድ አለኝ ብለው መሞታቸውን ስትነግራት ሰማሁ ። እክስቴም ለካ ተቀብራቸው አልደረሰችም ።

እያቴ አገራቸውን ወስደው ሳያሳዩኝ ሞቱ ። አንድ ቀን ግን ሄጄ ማየቴ የማይቀር ነው ። አደራ ብለውኛል ፤ አደራቸውን እወጣለሁ ። ብቻ ታሉኝ

ሁሉ ልፈፅመው የማልችለው ተቅድመ አያቴ ባድማ ላይ ቤት ሰርቼ ፣ ሚስት አግብቼ መኖሩን ነው ። ይህን ታደረኩኝ ትምህርቴን ማቋረጥ አለብኝ ። ይህን ደግሞ አላደርገውም ። በተረፈ ቃላቸውን ሁሉ አከብራለሁኝ ።

# አራት

ያያቴን አገር ፣ መስቀችን ሄጄ ሳላይ አመታት አለፉ ። እንዲያውም በትምህርቴ ገፍቼ ደብረታቦር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባቴ ለመራቅ ቻልኩ ።

ከስረኛ ወደ አስራ አንደኛ ክፍል ባለፍኩበት አመት ከወላጆቼ ክረምቱን ለመክረም ጋይንት መጣሁ ። ያያቴን አገር የምጎበኝበት ጥሩ አጋጣሚ አገኘሁ ። አባቴን መስቀች ሄጄ አክስቴን እንድጠይቃት ፈቃድ ጠየኩት ። ምንም ሳያንገራግር እንድሄድ ፈቀደልኝ ።

ከዚያ በፊት መስቀችን እረግጫው አላውቅም ። ብቻ ሰባትና ስምንትን ክፍል ነፋስ መውጫ ሁኜ ስማር ባሻጋሪ አየው ነበር ።

በጧት ተነሳሁና ላዩን በደጋው አድርጌ እገሰግስ ጀመር ። የገጠር መንገድ አያሳስትም ። ያገሩን ስም ካወቁ ማንም ሰው መንገዱን ያመለክታል ። ምንም ሳልቸገር ባስር ሰአት ገደማ መስቀች ደረስኩ ። አንድ ሰው አገኘሁና የቅድመ አያቴን ባድማ እንዲያሳየኝ ጠየኩት ።

"ደርሰሀልኮ" አለኝ ፣ አገጩን በማሾል ። እውነቱም ደርሼ ኖሯል ።

የቅድመ አያቱ ባድማ ትልቅ ግቢ ኖሯል ፡፡ ዙሪያው በግንብ አጥር የታጠረ ሆኖ አልፎ አልፎ ተንዷል ፡፡ ከባስ ከባሰበት ላይ ደጋምና የግራር እሾህ ጣል ጣል ተደርጎበታል ፡፡ ከግቢው ውስጥ አራት ያህል ቤቶች አሉ ፡፡ ዘመዶቻችን እንዳሉ አባቴ ነግሮኛል ፡፡ ካጥር ግቢው ስገባ አንድ ሽማግሌ አገኘሁ ፡፡ እኔ አላውቃቸውም ፤ እርሳቸው ግን ገና ሲያዩኝ ፤ "የሽፈራው ልጅ እንዳትሆን?" አሉኝ ፤ አድናቆት በተሞላበት ፈገግታ እየተመለከቱኝ ፡፡

"አዎን ፤ የሱ ልጅ ነኝ" አልኳቸው ፤ አባቴን በማወቃቸው ደስ ብሎኝ ፡፡

"አዬ መወለድ ፤ አባትህ የጠላውን አገር አንተ ለማየት መጣህ? የቅድመ አያትህ አድባር ትቀበልህ!" አሉና ሳሙኝ ፡፡ እኔም ምንም እንኳን ባላውቃቸው እንዱ ዘመዳችን እንደ ሆኑ ገባኝና መልሱን ሳምኳቸው ፡፡ ከዚያም እጄን እየጎተቱ ፤ "እረ ዘነበች! አንች ዘነበች!" በማለት አክስቴን እየተጣሩ ወደ ቤቷ ይዘውኝ ሄዱ ፡፡ ያክስቴ ቤት በሀይለኛ ጢስ ታፍኗል ፡፡ በቤቱ ጣራ በዝግታ ትጉልል እያለ ወደ ሰማይ ይወጣና ትንሽ ከፍ ሲል ብን እያለ በስሱ ይጠፋል ፡፡ የገጠር ቤት ጢስ የሚበዛበት ምጣድ ሲጣድ ወይንም የጠላ እህል ሲዘጋጅ ነው ፡፡ ይህን ድሮ አድርጌ አውቃ ለሁ ፡፡ በመንገድ ስንገላታ ውዬ እርቦኛል ፡፡

"እረ ዘነበች! የለሽም እንዴ?" እያሉ ሽማግ ሌው ያጋግመው ተጣሩ ፡፡

“አቤት! ማነው የሚጠራኝ?” ብላ ብቅ ስትል አይኖቿ ከኔው ላይ አረፉ ። የክንድና የክንዷን ጨርቅ ካንገትየው ጋር በማያያዝ አስራ ዋለች ። ያንገቷ ንቅሳት ደምቆ ይታያል ። ከደረቷ ላይ ያለው የብር ግማደ መስቀል ይፈልቃል ። እራሷን ባርጌ ሻሽ እንደነገሩ ሸብ ኣድርጋዋለች ።

“እየውልሽ ፤ የወንድምሽ ልጅ ሊጠይቅሽ መጣ!” አሏት ።

“ስመኘው” አለችኝ በደስታ ተውጣ ።

ስትስመኝ የደስታ እንባ እየተናነቃት ነበር ። አክስቴ ብቸኛ ሁና ሆድ እንደ ባሳት ተሰማኝ ።

ተያይዘን ወደ ቤት ስንገባ እውነትም አክስቴ ምጣድ ጥዳለች ። ቤቷ እንደ ሌሎቹ የገጠር ቤቶች ክብ የሳር ቤት ነች ። ከቤት ሲገቡ ላይን ማረፊያ የሚሆነው ባለላ ያገጠ ሞሰብ ከባለ ደልገን ጎታ ላይ ገብ ብሎ ይታያል ።

አክስቴ አምስት ባል በየተራ እያገባች ፈታለች ። ዛሬ ግን ባል አልፈልግም ብላ ካያቷ ባድማ ላይ ጎጆ ቀልሳ በብቸኝነት ትኖራለች ።

“መሀን በመሆኔ የተነሳ ልጅ እንዳልወልድ አውቄ ያደረገሁት ይመስል ወንዶቹ ሁሉ እያገቡ ይፈቱኛል ። እንግዲህስ ወዲያ የማንንም ቤት አላ ሚሽም!” ትል ነበር ፥ ቀድሞ ካያቴ ዘንዳ ስትመጣ ።

ትኩስ እንጀራ ባዋዜ ሰጥታኝ ስበላ ሽማግሌው ከተቀመጡበት እየተነሱ፣ "በይ መጣሁ ዘነበች ፤ የሁላችንስ እንግዳ አይደል ። የመቤቴ ልጅ ሲመጣ ዝም ብዬ አላይ" አሉና ወደ ቤታቸው ሄዱ ። አንድ ነገር ለማምጣት እንዳሰቡ ገባኝ ።

ሽማግሌው ብዙም ሳይቆዩ የፍየል ወጠጤ እያስጎተቱ መጡ ።

"ዘነበች ቢልዋ ሳይልኝ ፤ ገበታም አዘጋጅ ለደሙ መቀበያ" አሏት፣ ቀድመው ወደ ቤት እየገቡ ። አክስቴ ትንሽ እንኳን አላንገራገረችም ። ቶሎ ብላ የጠየቋትን አቀረበች ።

"እረ አባክዎን ተው ፤ እንደዚህ ያለ ነገር አይሆንም" አልኳቸው፣ ከተቀመጥኩበት እየተነሳሁ ።

"ተው ልጄ ተቀመጥ ። የመቤቴ ልጅ መጥተህ እንደዚህ አይነቱን ነገር የምሞክረው ይመስልሃል? ላባትህ ቢሆን ኖሮ አንድ ነገር አላደርግለትም ነበር ። አንተማ ጥቁር እንግዳዬ ነህ ። የመቤቴ አጥም ይወቅሰኛል ። ይልቅ ናሳመው ፤ ይኸ የኔ ልጅ ነው" ብለው ፍየሉን እየጎተቱ የመጣውን ልጃቸውን አስተዋወቁኝ ።

"በል ተቀመጥ ፤ እንኳን ፍየል ለምን በሬ አይሆንም ። እረግጠኸው የማታውቀውን ባድማ ስትረግጥ ፤ ሙች እንዲህ ነበር ልጄ. . . አንተም እግዚአብሔር ያቆይህ! የዘመድ አውራ ያድርግህ!

ይህን ማን ያደርገዋል ፤ ታርጌ ባድማ አንተ በመገ ኘትህ አይደል” በማለት አክስቴ ሽማግሌውን መረቀች ። እኔም ሽማግሌው ቁርጠኛ ዘመዳችን ናቸው ብዬብ ሆዴ አመስግኜ ተቀመጥኩ ።

ወዲያው ፍየሉን ልጃቸው ከወለሉ ላይ ጣለው ። የፍየል ምላስ መብረቅ ነው ፤ ጆሮን በሚ ሰነጥቅ ሁኔታ ጮኸ ። እግሮቹን ባንድ እጁ ግጥም አድርጎ በመያዝ በሌላው እጁ አፉን እፍን አደረ ገው ። ፀጥ ብሎ ጅራቱ ብቻ ተርገበገበች ፤ አይ ኖቹም ፈጠጡ ። አክስቴ ገበታውን ይዛ ካጠገባ ቹው በመቆም በፈገግታ ትመለከታለች ። ሽማግ ሌው ፣ “በስመ አብ ወወልድ . . .” ብለው ቢል ዋውን ከፍየሉ አንገት ላይ ሲያሳርፉት ሰውነቴን ስቅጥጥ አለኝ ። ፍየሉ በታፈነ ድምፅ ፣ “ሙዋ. . .” ብሎ ጮኸ ። ሽንቱ ጨርጨር ፣ በጠጡ ፍትልክ ፍትልክ ይል ጀመር ። ደሙ ባንገቱ ፉዋ . . . ! ብሎ ሲወርድ አክስቴ ገበታውን ለገተች ። ወዲያው እንደ መንፈራገጥ ብሎ ሽልብ አለ ።

የፍየሉን እግር ስንዛዘሩለትና ፣ “በል ቶሎ አድርሰው” ብለው ካጠገቤ መጥተው ተቀመጡ ። ሽማግሌው ድሮ አያቴ ይተርኩልኝ የነበረውን የቅድመ አያቴን ታሪክ እያነሱ ያወሩኝ ጀመር ። ቅድመ አያቴ ትልቅ እመቤት እንደነበሩ በሽማግ ሌው አንደበትም ተረዳሁ ። እኔም የርሳቸው ልጅ ቁብዬ በመከበሬ በጣም ደስ አለኝ ።

ቡና ተፈልቶ ጠጥተን ካበቃን በኋላ እራት እስቲደርስ ድረስ ሽማግሌው የቅድመ አያቴን

ግቢ እያዞሩ ያስጎበኙኝ ጀመር ። አዳራሹም ፣ እል ፍኝቱም ድርምስምስ ብለው ፈርሰው ፣ ሳማና ሙጃ በቅሎባቸዋል ። ሁሉን ነገር በጥንቃቄ ነው የምመ ለከተው ። የቅድመ አያቴ ባድማ የጥንት መሆኑ የሚያስታውቀው ድንጋዩ ሳይቀር ሸብቷል ።

“ጠጅ እንደ ውሀ እንዳልተጠጣበት ፣ ስጋ እንደ ጎመን እንዳልተበላበት ፣ የመቤቴ ባድማ ሳማና ሙጃ በቀለበት” አሉ ሽማግሌው ፣ ትክዝ ብለው ። እየተዘዋወርን ስንመለከት ቆይተን ወደ ቤት ገባን ።

ማታ አንደኛው አጎቴ ደግሞ ገንቦ ጠላና ሞሰብ እንጀራ ሚስቱን አሲዞ መጣ ። ይህን ያህል መከበሬ በቅድመ አያቴ መልካም ተግባር በመሆኑ አሁንም ኩራት ተሰማኝ ። እራት ላይ አያቴን አልፎ አልፎ ያነሷቸዋል እንጂ በተረፈ ጫዋታቸው ሁሉ ስለ ቅድመ አያቴ ነው ። ምን ዓይነት እመቤት ኖረዋል? የሚለው ጥያቄ በአእ ምሮዬ እየጎላ መጣ ። አካለክርስቶስ ወርጂ መቃብ ራቸውን የማይ መሆኔን ስገልፅላቸው የምርቃት ነገር አይነሳ ።

ሁለቱን ቀን አካባቢውን እየጎበኘሁ አካለክርስ ቶስ ሳልሄድ ቀረሁ ። በሶስተኛው ቀን ማታ ላክስቴ አካለክርስቶስ የምሄድ መሆኔን ነገርኳት ።

“እኔ ነበረሁ ይገርህ የምሄደው ፣ ተዚያ መዳ ህኒአለም የማልቀርበት ቀጠሮ አለኝ ። ሌሎቹም ነገ ስራ ነው ፣ አይገኙም ። የዘር ወቅት ስለ ሆነ

ሰው ማስቸገር ይሆናል ። ምን ይሻላል?" ስትል ተጨነቀች ።

"ከዚያ መቃብሩን የሚያሳየኝ ሰው ካላጣሁ አትጨነቂ ። እኔ ደርሼ እመጣለሁ ።"

"ማሳየትማ የገዳሙ መነኩሴ ሁሉ ያሳይሃል ። የወይዘሮ ደብሪቱን መቃብር የማያውቅ የለ ። እንዳው ብቻህን ሙሄዱ ቅር አለኝ እንጂ ።"

"እንግዳው አታስቢ ።"

"ገደሉን በጫማህ አይደል የምትወርደው፣ መቼም ያለ ጫማ አትሄድ?"

"አይዞሽ ፣ ጫማዬ አያንሸራትትም" አልኳት፣ እግሬን እንደ ማንሳት አድርጌ ሸራ ጫማዬን የውስጡን በኩል እያሳየኋት ።

"ይኸ ሱሪህም ወደ ላይ ታልጠቀለለኸው እየተወናጨፈ ጠልፎ ይጥልሃል" አለችኝ ፣ ከቅሬታዋ ፈቀቅ ሳትል ።

ካክስቴ ላይ ሁለት አይነት ጭንቀት አየሁባት ። አንደኛው ፣ የቅድመ አያቴን መቃብር ብቻዬን ማየቴ ደስ አላላትም ። ሁለተኛው ፣ ገደሉን መውረድ ያልቻለ እንደ ሆነ ብላ ሰግታለች ። በርግጥም ሁለቱን ቀን ብቻህን አይሆንም እያለች ነው ያስቀረችኝ ። እኔ ደግሞ ቅድመ አያቴን እስከነ ህይወታቸው የማገኛቸው ይመስል ቸኩያለሁ ።

በማግስቱ ጧት ቁርስ ሰጥታኝ ከበላሁ በኋላ ቅር እያላት በር ድረስ ሸኝታኝ ፣ “ተጠንቀቀህ ፣ እርከን እርከኑን እያየህ ነው መርገጥ” ብላኝ ፣ ትንሽ ቆም ብላ አካሄዴን አስተዋለችና ወደ ቤቷ ተመለሰች ።

# አምስት

መንገዱ አያሳስትም ፤ አንድ ወጥ ወደ ገዳሙ የሚያዘልቅ ፤ እርቀቱም አንድ ሰአት ቢያስኬድ ነው ። ብቻ ገደል ስለ ሆነ እሩቅ አገር አስመስሎታል ።

አግድመቱን ጨርሼ ካፋፉ ብቅ ስል ገዳሙ ከገደሉ ስር በጥድ ደን አጅብ ብሎ ታየኝ ። ገደሉ ግን ያስፈራል ። የዝንጀሮ መንጋ በገደሉ ገደሉ ሁሉንም ጥግለጥግ ይውካካል ። ትንሽ ቆም ብዬ ሁሉንም ካስተዋልኩ በኋላ ቁልቁለቱን እየተንተረተርኩ ወረድኩ ። የምሄድበት መንገድ ራሱ ደን ስለ ሆነ ያስፈራል ። ቆቆች አስር ጊዜ ግርር እያሉ አስደነበሩኝ ። ሁለት ጊዜ ደግሞ ሰሳዎች መንገዱን አቋርጠው ጡብ ጡብ እያሉ እሮጡ ። ትንሽ እንደ ወረድኩ ሳይን ከሚያስፈራ ገደል ደረስኩ ። ቁል ቁል ስመለከት የመሬቱ እርቀት የትና የት ነው ። እውነትም አክስቴ ልትጨነቅ ይገባታል ። አያቴም ቢሆኑ ፡ "ገና ልጅ ነህ ፤ ገደሉን መውረድ ፥ መውጣት አትችልም" ያሉኝ እውነታቸውን ኖሯል ። ያን የገጠጠ ገደል ለመውረድ ይቅርና ትክ ብሎ ለማየት እንኳን አልደፈርኩም ። ቶጥ ብዬ መቆሙ ራሱ ኸርው ብዬ የምሄድ መሰለኝና ካፋፉ ላይ ተቀመጥኩ ። በርግጥም ስቀመጥ ተሻለኝ ፤ የሚያ

ዞረኝ ሁሉ ቀለለኝ ። ለመውረድ ግን አልቻልሁም ። ካፉፉ ላይ ተጎልቼ አሽቆልቁዬ መመልከት ሆነ ። እንዳልመለስ ዘመዶቼ ሊስቁብኝ ነው ። የመጣሁ ለት ማታ ገደሉን አይሆንልህም ሲሉኝ ፎክሬያለሁ ። አክስቴም ብቻህን አይሆንም ስትለኝ ግዴለሽም ብያታለሁ ። ይኸ ሁሉ አሳፈረኝ ።

እንደ ምንም ተደፋፈርኩና እግሮቼን ወደ ፊት በማስቀደም በንፍቅቄ ሞከርኩት ። ጭራሽ የማይሞከር ነገር ነው ። በህይወቴ ከመሰላል ላይ እንኳን ወጥቼ አላውቅም ። ተወልጄ ያደኩበት አካባቢ ለጥ ያለ ሜዳ ነው ። አልሆንልኝም ፤ እየተንፏቀኩ ወደ ነበርኩበት ተመለስኩ ።

እንደ ተቀመጥኩ ብዙ ሳስብ አንድ ነገር ታወሰኝ ። ከቅድመ አያቴ መቃብር ላይ እንዲት ጥድ መብቀሏን ሁሉም ተርከውልኛል ። ጥሩ ምልክት ነች ። የቅድመ አያቴን መቃብር አይቼ መጣሁ ፤ ጥዷም አድጋለች ብዬ ማውራት ነው ። ደግሞስ ምን አየህ? ምልክቱ ምንድን ነው? እያሉ አይጠይቁኝ ። ለመመለስ ሳመንታ የቅድመ አያቴ አፅም የሚታዘበኝ ፣ አካለክርስቶስ የሚናገሩብኝ መሰለኝ ። መልሼ ከምሸሽ አልኩኝ ። ምን አይነት ፈተና ነው? እወቁኝ እወቁኝ ብዬ አሁን ደግሞ መሸሸጊያ አጣሁኝ ። የመጣሁ ለት ፍየል ታርዶልኝ ፣ ጠላ ቀርቦልኝ ፣ በጨዋ ደረጃ ፣ በሞቅታ ብዙ ዘላብጃለሁ ። ይኸ ሁሉ የትዝብት አይኑን አፈጠጠብኝ ። እረ ስንቱ የዘመዶቼ ምርቃን ፣ ያክስቴ የደስታ

እንባ ተራራ አሳክሎኛል ። አስመስሎ የመዋሸቱ ነገር ከንቱ ነው ።

ለሁለተኛ ጊዜ መሞከር ግድ ሆነብኝ ። የመቆሙ ነገር ሙከራም አይሞከር ፤ በቅምጡ ማንፏቀቁን ቀጠልኩ ። ከብለል ብል እንኳን የሚያግደኝ ዛፍ ነገር የለም ፤ ጠላ ገደል ነው ። አስቀድመው እጆቼ ልፍስፍስ ይላሉ ። የሆነው ይሁን ፤ ስም ከሆነም የቅድመ አያቱን መቃብር ለማየት ሲሄድ ገደል ገብቶ ሞተ ነው ። ከሁሉም ያሳዘነችኝ አክስቴ ነች ። ሰው እንደማትሆን እርግጠኛ ነኝ ።

ግራና ቀኝ በጆቼ ጠንከር ያለውን ድንጋይና የገደል ሳር እየያዝኩ ፥ በግሮቼ እርከን እርከኑን እየረገጥኩ ትንሽ ወረድኩ ። ዘቅዝቄ ስመለከት ሲኦል ነው ። ቀና ብዬ ሳይ ገደሉ ያፈጠጠብኝ መሰለኝ ። በወጥመድ እንደ ተያዘች አይጥ ተጨነኩ ። እግሮቼም ፥ እጆቼም ተንዘፈዘፉ ። የላቡ ነገር አይነሳ ፤ ጠቅላላ ሰውነቴ ዋዠቀ ። ይባስ ብሎ ሀይለኛ ነፋስ ደኑን እየተራመሰ መጣ ። ድምፁ የሰማይ ነጎድጓድ ይመስላል ። ከገደሉ ጋር አብሬ የተሰፋሁ ይመስል ልጥፍ አልኩኝ ። ነፋሱ በላዬ ላይ ጋለበና አለፈ ። ነፍሴ ለቅፅበት ከኔ የተለየች መሰለኝ ። ሳይታይ ይቅር አልኩና ፊቴን አዞሬ በደመነፍስ ገደሉን እየቧጠጥኩ ወጣሁ ። ከዚያ በላይ ግን ቆርጬ ለመሄድ አልቻልኩም ። ምን አይነት እልህ ነው?

ካፋፉ ተቀምጬ ልውረድ ወይንስ ልመለስ ፤ እያልኩ ሳስብ ከኋላዬ ኮቴ ሰማሁ ። ቀና ስል እርሳ

ቸውም ፥ እኔም ደነገጥን ። እርሳቸውም ባሉበት ቁመው ፥ እኔም እንደ ተቀመጥኩ በመገረም መተያየት ሆነ ። በተለይ የርሳቸው አስተያየት አድናቆት የተሞላበት ነበር ፥ "የከተማ ልጅ ከየት ፈለቀ?" የሚሉ አይነት ።

ያረጀ ቆብ ከራሳቸው ደፍተዋል ። ከላይ ደበሎ ፥ ከስር ዘባተሎ የሆነ ጨርቅ ለብሰዋል ። በትልቅ አኮፋዳ ፥ የልመና እንጀራ ይዘዋል። ካስደነቀኝ ነገር አንዱ እኔ ወጣቱ ባዶ እጄን ለመውረድ ተቸግሬ እርሳቸው ያን ሁሉ ቅራቅንቦ ተሸክመው ለመውረድ ማሰባቸው ነው ።

መሄድ የለ ፥ መናገር የለ ዝም ብለው ተገተሩ ። አያቴ ፥ "የገዳሙ መነኩሴዎች አንዳንዶቹ ሰው ሲያዩ አውሬ ያዩ ያህል ይደነብራሉ ። ወይንም አይናገሩ ተዘግተው አይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ ዝም ነው ። ዋ ፥ ሁሉም ነገር ያልፋል!" ያሉኝ ትዝ አለኝ ። የንግግሩን መክፈቻ እኔው ልጀምረው አልኩና ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ፥—

"እንደምን አደሩ አባ!" አልኳቸው ።

"እግዚአብሄር ይመስገን!" አሉኝ ። ድምፃቸው ቀስ ያለ ነው ።

"ከታች ጋይንት ነበር የመጣሁት ፤ የወይዘሮ ደብሪቱ የልጅ ልጅ ነኝ" በማለት መቼም ባገሩ የሚታወቁት ቅድመ አያቴ ናቸው ብዬ የርሳቸውን ስም ጠራሁ ።

"ወይዘሮ ደብሪቱ ...ወይዘሮ ደብሪቱ ..." አሉ ፣ ግንባራቸውን ቋጥር እድርገው እያሰቡ ።

"ከሞቱ ቆይተዋል" በማለት አስታወስኳቸው።

"እህ... ወይዘሮ ደብሪቱ መስቀች ? አዎን ፣ ከሞቱ ቆይተዋል ። የተቀበሩትምኮ ተዚሁ አካላ ክርስቶስ ነው" አሉኝ ።

"አዎን ፣ ከዚሁ ነው ።"

"ዛዲያ ምን ሆነህ ነው ተዚህ የገደል አፋፍ ብቻህን የተቀመጥ'ከው?"

"የቀድሞ አያቴን መቃብር ለማየትና ወዲያ ውም ቤተክርስቲያን ለመሳለም ነበር ። ገደሉን ስላልመድኩት ለመውረድ ተቸግሬ ነው ።"

"ገደሉማ እንኳን ላንተ ላልለመድ'ከው ለኛም ላደግንበት ችግር ነው" አሉና በዝግታ እርምጃ ወደኔ መጡ ። "ዛዲያ ጫማ አድርገህ አይሆንም ፣ ጫማህን አውልቅና ያዘው" አሉኝ ። እንዳሉኝ አደረኩ ።

"ገደሉን ቁልቁለህ አትየው ፤ ያየ'ከው እንደ ሆነ ያዞርሃል" በማለት ካስጠነቀቁኝ በኋላ ምርኩዛቸውንና አኮፋዳቸውን በግራ እጃቸው ይዘው ፣ በቀኝ እጃቸው ጠንከር ያለውን ድንጋይ ያዝ እያደረጉ ወረዱ ። ዞረው ሲያዩ ገና በንብርክኬ ነኝ ።

"አይዞህ! በጎን ነው መሄድ ፤ ፊት ለፊት አይደለም ። ፀጉርህ እጣቶችም ቆንጥጥ" ሲሉ አደ

ፋፈሩኝ ። እንዳሉኝ በቀኝ ታፋዬ ገደሉን ተጠግቼ የሚይዙትን እየያዝኩ ፣ የሚረግጡትን እየረገጥኩ ተከተልኳቸው ። እየዞሩ እያበረታቱኝ ከገደሉ ወገብ ደረስን ። እርሳቸው ግን ትንሽ እንኳን የፍርሃት ምልክት አይታይባቸውም ። በደበሳቸው ገደሉን ሲገፉት ፣ ሲንኳኩ ይሰማኛል ። የዝንጀሮ ግመሬ መሰለው ፤ ያን ሁሉ ቅራቅንበ ተሽከመው ሲወርዱ አስደነቁኝ ። እኔም እርሳቸውን ሳይ ፍራቴና ሙን ቀጥቀጤ ቀስ በቀስ ለቀቀኝ ።

በመጀመሪያ እርሳቸው ዘብጥ እረገጡ ። ቀጥዬ እኔ ፤ ካንድ አዘቅት የወጣሁ ያህል በረጅሙ ተነፈስኩ ። ቁጭ ብዬ ጫማዬን ሳደርግ ፣

"የፈረንጅ ትምህርት ፣ አስኮላ ትማራለህ?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

"አይ ...አይ ..." አልኳቸው ግራ በመጋባት አይነት ።

"አይዞህ! ዘመን ያመጣው ነው" አሉኝ ፣ እንደ ዋሽኋቸው ሲያውቁ ትንሺ ፈገግ ብለው ።

እንዳው ቢጨንቀኝ እንጂ አለባበሴ ሁሉ ያስታውቅብኛል ። የታጠኩት ቡላ ካኪ ሱሪና የርሱው ግጥም ካኪ ጃኬት ፣ እንዲሁም ካንገቴ ላይ ጠምጠም ያደረኳት ፎጣ ይመሰክሩብኛል ። ምን ላድርግ ፤ አያቴም የዘመኑን ትምህርት ይጠሉት ነበር ። ከመነኩሴው ጋር ያራራቀኝ እንደ ሆነ ብዬ ፈርቼ ነው ።

እርሳቸው እየመሩ ፣ እኔ እየተከተልኩ መንገዳችንን ቀጠልን ። ጫማ የሚያስወልቅ ፣ የንብርክክ

የሚያስኬድ ገደል ዳግመኛ አልገጠመንም ። ከደ ልዳላው ቦታ ደርሰን ትንሽ አግድመት እንደ ሄድን ከቤተ ክርስቲያኑ ደረስን ። ቀና ብዬ ገደሉን ስመለከተው ሰማዩን ተሸክሞ የቆመ ይመስላል ። ከቤተ ክርስቲያኑ በታች እንዲሁ ኸገው ያለ ገደል እንዳለ መነኩሴው ነግረውኛል ። ቤተክርስቲያኑ የሳር ክፍክፍ ነው ። ከላይ ጉልላቱም እንዲሁ የሳር ክፍክፍ ነው ። በውጭ ከተሳለምን በኋላ መነኩሴው ካንገታቸው የንጨት መቁጠሪያ አውጥተው ፀሎት ጀመሩ ። እስኪጨርሱ ድረስ ቆሜ ጠበኳቸው ። መነኩሴው ፀሎታቸውን ሲጨርሱ መቁጠሪያቸ ውን በምራቃቸው እንትፍ እንትፍ ብለው በጃቸው አሻሽተው ካንገታቸው አጠለቁት ። አያቴም እንደ ዚህ ያደርጉ ነበር ።

መነኩሴው ወደኔ መለስ ብለው ፣ "ይህ ነው ያገርህ ገዳም ፤ ብቻ እንደ ከተማው ቤተ ክርስቲያን ቆርቆሮ አለበሰም" አሉኝ ። ወደ ምስራቅ አቅጣጫ እያመለከቱ ፣ "የወንዱ ገዳም ያውና ። ተዘርፎ ተገ ደሉ ስር" ሲሉ አሳዩኝ ። እውነትም ትንሽ ጎጆ ዎች የንብ ቀፎ መስለው ታዩኝ ። የሴቱ ገዳም ደግሞ በምእራብ በኩል እንዳለ ነግረውኛል ። ነገር ግን በደን የተሸፈነ ስለሆነ ባይኔ አላየሁትም ። ከዚህ በኋላ የቅድመ አያቴን መቃብር ሊያሳዩኝ ይዘውኝ ሄዱ ።

"ይህ ነው የቅድመ አያትህ መቃብር" አሉኝ ፣ ቆም እያሉ ።

"የቱን?" አልኳቸው ፣ በሩቁ እየተመለከትኩ ።

"ይህ ፣ ተፊትህ ያለው ጥድ" አሉኝ ፣ በጃቸውም ፣ ባገጫቸውም እያመለከቱኝ ።

"ይኸን?" አልኳቸው ፣ እኔም በጄ እያመለከትኩ ።

"አዎን" አሉኝ ።

ለምን እንደ ሆነ እንጃ ስሜቴ ሁሉ ቅዝቅዝ አለ ። በርግጥ ጥዷ ትልቅ ሁናለች ። በተረፈ መቃብር መሆኑ እንኳን አያስታውቅም ። መሬቱ ተስተካክሎ ድንጋዩ ሳይቀር ጠልሟል ። ጥዷም ፀድቀው ነው የበቀለችው ያሉኝ እንዲሁ ነው ። ከሌሎቹም መቃብር ላይ ጥድም ፣ ሌላም ዛፍ በቅሏል ። ሁሉም ፀድቀው ከሆነ ጥሩ ነው ። አያቴ ሞኝ ኖረዋል የሚል ሀሳብ ተሰማኝ ። ያገኘሁትቁም ነገር ቢኖር ደግ ሰው ከመቃብር በላይም ቢሆን ስሙ ለዘላለም ሲወሳ መኖሩ ነው ።

የመቃብሩን ጉዳይ ጨርሰን እልፍ ብለን በመቆም ጭውውት ጀመርን ። ገዳሙ ከዚያ ገደል ስር ለምን እንደ ተሰራ የማወቅ ጉጉት አደረብኝና ጠየኳቸው ።

"እሱን ተውው ፤ የኛ ስራ አይደለም" አሉኝ ።

ሳላውቅ ፣ መጠየቅ የማይገባኝን ጥያቄ ጠይቄ ይሆን? ወይንስ ፣ መነኩሴው የገዳሙን ታሪክ አያውቁት ይሆን? የጠየኳቸውን ጥያቄ ወደ ጎን በመተው

ስለ ከተማ ኑሮ ፣ ባጠቃላይ ስለ ውጪው አለም ይጠይቁኝ ጀመር ። የተቻለኝን ያህል መለስኩላቸው ። በምነግራቸው ሁሉ ይደነቃሉ ። ይህ ሁሉ ሲሆን እንደ ቀምን ነው ። እኔ ለመሄድ ቸኩያለሁ ። እርሳቸው ደግሞ ቶሎ የሚለቁኝ አይደሉም ።

"ዛሬያ አሁን ለመሄድ ትቸኩላለህ?" አሉኝ ፣ እንድቆይላቸው አይናቸቸው ሳይቀሩ እያባበሉኝ ።

"ትንሽ ብቆይም ግደለ" አልኳቸው ፣ ቸኩያለሁ ለማለት ከበደኝና ።

"እንግዳው አረፍ እንበል" ብለው ወደ ትልቁ የጥድ ዛፍ ስር አመሩ ። መቃወሙ ችግር ነው ፤ ተከተልኳቸው ። የገዳሙ መነኩሴዎች ሰው በብዛት አይተው አያውቁም ፤ ካውሬ አይሻሉም ። በዚያም ላይ የከተማ ልጅ ነኝ ። እንኳን ለርሳቸው ላካባቢው ህዝብም ብርቅየ ነኝ ። በሌላ በኩልም አንድ ነገር ሊያጫውቱኝ አስበው ይሆናል ። ወይንም እኔ እንዳጫውታቸው ፈልገው ። ነፍሳቸውን ይማረውና እያቴ ፣ "መነኮሳቱ የዚችን አለም ኑሮ ጥለው ገዳም የሚገቡት አንድ ነገር አድርገው ንስሃ ለመግባት ፣ ወይንም አንድ ነገር ሲደርስባቸው ከሰው ለመራቅ ነው ። ዋ ፣ ሁሉም ነገር ያልፋል!" ያሉኝ ታወሰኝ ። ስለዚህ መነኩሴውም አንድ ታሪክ ይኖራቸው ይሆናል ። ወይንም ከዚሁ ቅር ፣ መንን ፣ ድንግል ሁን ቢሉኝስ? ለማንኛውም ትንሽ መታገስ እንዳለብኝ ወሰንኩ ።

የጥዱን ዛፍ ደገፍ ብለው ተቀመጡ ። አኮፋዳቸውን ዝንብ እንዳይወርባቸው በደበኋቸው ስር ወተፍ አድርገው ዘባተኋቸውን ለበስ አደረጉት ። እኔ ከፊት ለፊታቸው ነው የተቀመጥኩት ።

የግሮቻቸውና የጆቻቸው ጥፍሮች ተንጨፍረው ያሞራ ጥፍር ይመስላሉ ። እጆቻቸውም ሆኑ እግሮቻቸው ውሃ ነክቷቸው አያውቅም ፤ ያርጀና ገላ መስለው ቅርፊት ሰርተዋል ። ፂማቸው ራሱ መልኩን ለውጦ ወይቧል ። በቆባቸው ስር ቅጫም ፍስስ ብሎ ይታያል ። ፀጉራቸውም የተቆጣጠረ ነው ። ሽበት በመጠኑ ወሯቸዋል ። ጠረናቸው ሁሉ የዱር አውሬ ጠረን ነው ። አሁን ደህና አድርጌ አስተዋልኳቸው ፤ ፊታቸው ሁሉ ፍርግርግ ያለ ነው ።

በጥዱ ዛፍ እያለፈ የፀሀይ ጨረር ዘባተኋቸውን ሲነካው ቅማሉ ከስር ይፈላ ጀመር ። ጥቃቅን ፥ ትልልቅ ፥ አንዱ በአንዱ ላይ እየተዛዘለ ይርመሰመስ ገባ ። ይህን ሳይ ዘገነነኝ ። እጄን ላክ አድርጌ ቅማል ላነሳ ስል ፥ "ተው!" አሉኝ ፥ በቁጣ እጄን ቀብ እያደረጉ ። በድንጋጤ ሽምቅቅ አልኩኝ ። መደንገጤን ሲያዩ መልሰው ፈገግ አሉና ፥ "እነዚህም ፍጡሮች ናቸው" አሉኝ ። እውነትም አሉም መናቅ አልኩኝ በሆዴ ።

"መቼም የተባረክህ ዘር ነህ ፤ ተዚህ ገዳም መጥተህ አንድ ታሪክ ይዘህ መሄድ አለብህ ። የማጫውትህ ጉዳይ አለኝ ፤ ታስጨርሰኝ እንደ ሆን

ልጀምርልህ ። በተረፈ ከንቱ ነው›› አሉኝ፣ በል መና መልክ ።

‹‹ግዴለም ፤ አስጨርስዎታለሁ›› አልኳቸው ።

‹‹እግዚአብሄር ይባርክህ!›› በማለት መረቁኝ ።

መንኩሴው ግንባራቸውን ቋጥር ፊታ እያደረጉ መላልሰው ጎንበስ ቀና ካሉ በኋላ ‹‹መቼም የጌታ ፈቃዱ ሆኖ የሰማይ ቤቱን ቢፈቅድልኝ እንጂ የመሬቱማ ነገር አብቅቷል ። የሰው ምላስ እንደ እንጨት አያደርቅም እንጂ በቁመናዬ እደ ርቅ ነበር ። ግና አለሁኝ›› አሉ አይኖቻቸውን ከገደሉ ስር ተክለው ። ሲናገሩ ምርር እያሉ ነው ። እስካሁን ምን እንደሚሉ አልገባኝም ። ጨርሶ ለኔ የሚያወሩ አይመስሉም ። ፊታቸው የሀዘንና የፀፀት ምልክት ይታይበታል ።

‹‹እየውልህ ፤ ታሪኩ እንዲህ ነው›› አሉኝ ። ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው ፣ ‹‹እናትና አባቴ እኔንና የኔን ታላቅ ወልደው ፣ ጥሩ የተደላደለ ፣ የዘመናይ ኑሮ ባይኖሩም ፣ ደስ ብሏቸው ተከብረው ይኖሩ ነበር ። ከኔ በታችም ሆነ ከወንድሜ በላይ ሌላ ልጅ አልነበራቸውም ። እናቴ ፣ ‘እንደ አህያ ጥሎት ሁለት ልጆች ብቻ ወልጄ ቀረሁ’ እያለች ታዝን ነበር ። ብዙ ጊዜም ለታቦት ተስላለች። ግና የጌታ ፈቃዱ ሳይሆን ቀርቶ ሌላ ልጅ ሳትወልድ ቀረች ። በኋላም የልጅ ልጅ ለማየት ፣ የኛን ልጆች ለመታቀፍ ነበር ምኞቷ ። ግና ሳይሆን ቀረ ።

"እየውልህ ፤ ሊነጋጋ አቅራቢያ አንድ አበል ጀችን የሆን ተተኛሁበት መጥቶ ቀሰቀሰኝ ። በጤናው እንዳልሆን አውቄዋለሁ ። እየተጣደፈሁ ልብሴን ለባብሼ ስወጣ ፡ 'ወረታውን ያቶ ፈንቴ መንገሻ ልጆች ሳይደበድቡት አልቀሩም ፤ የሰው ጩኸት ሰምቻለሁ' አለኝ ።

"ተቤቱ መኖር አለመኖሩን አረጋግጠሀል? ስለው ፤ 'ተቤቱ ሄጄ አለመኖሩን ሚስቱ ነግራኝ ሙስሎኝ ወዳንተ የመጣሁት' አለኝ ። እየተሯሯጥን ስንደርስ ወንድሜን አጥር ስር ወድቆ አገኘነው ። ልሳኑ ተዘግቶ መናገር አይችልም ። መሀል አናቱ ተጠርምሶ ፣ በደም ተጨማልቋል ። ሃፍረተ ስጋውም እንደ ወይፈን በሬ ተቀጥቅጧል ። ተሳይ ፣ ተታች ብንል ምን ዋጋ አለው ፤ አንባጓሮ አናነሳ ያለነው ተሰው ግቢ ነው ። ገላጋይ ፣ 'በዚህ ሰአት ተሰው ግቢ ምን ልታደርጉ መጣችሁ?' ሊለን ነው ። ውሾን ያነሳ ውሾ አልንና ወንድሜን ተሸክመን ፣ እያንዘባዘብን ወደ ቤታችን ሄድን ።

"እየውልህ ፤ ወንድሜ አንቋሮ አንቋሮ ተረፉዱ ላይ ሞተ ። ተሞቱ አሟሟቱ ነውና ወንድሚ አሟሟቱ ከፋ ። ተሰው ጓዳ ውስጥ እንደ ኑግ ተወግጦ ጥራጊ ይመስል አጥር ስር ተጣለ ። ተልቅሶው ላይ ቆሞ አልቃሽ ፡—

'ቀጥቅጠው ገደሉት እንደ ጥቅምት ገብስ ፤
ወንድም እንደ ሌለው ደሙን የሚመልስ'
ብሎ ጊጠመ ።

"እየውልህ ፤ እናቴ ፣ 'ሁለት ልጆች ብቻ ወልጄ ቀረሁ' እያለች ስታዝን ፣ እኛም ሳንባረክትላትቀረን፡

# ስድስት

‘‘እየፀውልህ ፤ ወንድሜ በሰው እጅ ተደብድቦ ሊሞት የቻለው የሰው ሚስት በመድፈሩ ነው ። ተመንደራችን በዛ ፈንቴ የተባለ ሰው ነበር ። እናት አባቱ በልጅነቱ ሙተውበት አጎቱ ፥ አቶ ፈንቴ መንገሻ ነበር አሳድጎ ለወግ ለማረግ ያበቃው። ዛዲያ ሚስቱ ተልክ ያለፈች ቤሰኛ ነበረች ። ወንድ የተባለ አያልፋትም ። ተውሽሞቿ መሀከል አንዱ የኔ ወንድም ወረታው ተበጀ ነበር ። እሱም እንደ ሷው ሴሰኛ ፥ ቀሚስ ያጠለቀች ሴት አታመልጠውም ። ዛዲያ እንደ በዛ ፈንቴ ሚስት ያበደላት ሴት የለችም ። የበዛፈንቱ ሚስትም እንደኔ ወንድም የከነፈችለት ወንድ የለም ። ወፍጮ ስትፈጭም ሆነ እንጨት ስትለቅም ፦

‘እናቱ ምን አሉኝ ፥ አባቱ ምን አሉኝ ፤

እባካችሁ ሰዎች ሚስቲቱን አማልዱኝ ፤

የስርቆሹ አልሆነም ለጭራሹ ትስጠኝ ።’

እያለች ታንጎራጉር ነበር ። ወንድሜ ለበዛ ፈንቴ ሚስት የባል ያህል በመሆኑ እረኞችም ፦

‘እህያ መጣች ተጭና ኮለል ፤

የበዛ ልፋት እንዳው የበለል ።

እህያ መጣች ተጫኑና ሲሜት ፤
የበዛን ቅቤ ወረታው በሳት ።'
እያሉ ይዘፍኑበት ነበር ።

“በዛ ፈንቴ ተስራ በስተቀር ሌላ ነገር የማያውቅ የግዜር ሰው ነበር ። እረኛው በዘፈን ፣ አዋቂው በይሩ ሲያወራው እሱ ትንሽ እንኳን አልቆጠቁጠው አለ ። በዚህ የተነሳም ያዶ ፈንቴ መንገሻ ልጆች አንጀታቸው አረረ ። አቶ ፈንቴ መንገሻ ሶስት ወንዶች ልጆች ነበሩት ። የመጨረሻ ልጁ የኔ የድሜ ጓደኛዬ ሲሆን ማህበርተኛም ነበርን ። መሀከለኛው ደሞ የወንድሜ ጓደኛ ነበር ። ወንድሜን ለመደብደብ አስበዋል እንደ ተባለ እናቴም ፣ አባቴም ፣ ‘እርጉም ሁን ! ዳግመኛ ተበዛ ፈንቴ ሚስት የደረስህ እንደ ሆነ’ ብለውት ነበር ። እኔም ባቅሜ መክሬዋለሁ ። ግና የተለከፈ ስል ሆነ የማንንም ምክር አልተቀበለም ። በመጨረሻም ሊያገኙት የቻሉት በዛ ፈንቴ በርበሬ ለማምጣት ወደ ፎገራ ስለ ሄደ ተዚያው አዳር በመያዙ ነው ። እየውልህ ፤ ሚስቱን ተቤቱ አጋድሞ ተሰው ሚስት ሲያፎደፉድ የናፉ ተያዘ ። እረኞችም እንደ ልማዳቸው ፦

‘እሁድ ተለቅልቆ ሰኞ ተበራዬ ፤
ተሰው ሚስት አይሄድም ወረታውን ያዬ ።
እረ አንቺው ነይልኝ እኔስ አልመጣም ፤
እንዳቶ ወረታው በጉዴ አልወጣም ።’

እየተባለ ተሞቶ ወዲያ እንኳን ያገር መዘባበቻ ሆነ ።

"ወንድሜ ሲሞት የሃያ ሰባት አመት ልጅ ነበር ። እኔም በዚያን ጊዜ የሃያ አራት አመት ልጅ ነበርሁኝ ። የወንድሜ ገዳዮች ሜካ የገቡት ወንድሜ እንደ ሞተ ነው ። አባትየው ፤ አቶ ፈንቴ መንገሻ ብቻ በልጅ ደም አልጠየቅም ብሎ በመንግስት በኩል ያለውን ጣጣ ጨርሶ ቤቱን ሳይለቅ ተቀምጧል ። በዛ ፈንቴ ደሞ በርበሬውን ይዞ ሲመለስ ተመንገድ ሰዎች ፤ 'ባንተ ሚስት ምክንያት የእኅትህ ልጆች ወረታው ተበጀን ገለው ሜካ ገብተዋል' ስላሉት ፤ አህያውን ሽጦ እንደ መናኝ በዚያው ቀረ ። ሚስቱም የኔን ወንድም የደበደቡት ለት እቧንም ብሏቷን ብረት አግለው (ጉባ) ስለተኮሷት እንደ ነቀርሳ ሆኖባቷ ብዙ ቀን ተንደቅድቃ ተንደቅድቃ ፤ አይሆኑ ሁና ሞተች ።

"ያባቴን አፅር ምንሽር የያዝሁት ወንድሜ እንደ ሞተ ነው ። የወንድሜን ደም ለመመለስ አሳብ አለኝ ። ግና ብቻዬን ስለሆንሁ ግራ ገብቶኛል ። እንዲሁ ተወላጆቼ ወጣ ገባ እያልሁ አንድ አመት ተቀመጥሁ ። ደም ባለመመለሴ የተነሳ እንኳንስ ሌላው ሰውና አባቴም ተሰው አልቆጥረኝ አለ ። በወጣሁ በገባሁ ቁጥር በነገር ይጎሽመኛል ፤ 'ወይኔ ተበጀ በለው! እንደ ልቤ የምንቀሳቀስ ቢሆን አሳይህ ነበር' ይለኛል ። እንዲህ የሚለው እግሩ ሰባራ በመሆኑ ነው ። እንደምታየው አገሩ ገደል ስለ ሆነ ተቆሻ ውስጥ ማር እቆርጣ

ሰሁ ሲል ገደል ገብቶ አንድ እግሩ ስለ ደቀቀ እንደ ልቡ መንቀሳቀስ አይችልም ።

"በእንዲህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ ተጎረቤታችን አንድ ሰው ሞቶ ተልቅሶው ላይ አልቃሽ ፡—

'ወረታው ተበጀ ምን ወንድም አለው ፤
እንደ አህያ ፊሳ ወድቆ የቀረው'

አለና አለቀሰ ።

"ምንሽሬን ይገፎ ስፎክር ግማሹ አሽሟጠጠኝ። ግማሹ ደሞ ብቻዬን በመሆኔ አዘነልኝ ። አባቴም በደም ፍላት ሲወራጭ ያገር ሽማግሌዎች አንቀው ያዙት ። አልቃሹንም ዳግመኛ እንደዚያ ያለ ሰውን የሚያነካካ ግጥም እንዳይገጥም ተቆጡት ።

"አገራችን መጥፎ ልማድ አለው ። የሞተበት ለተጎዳ ሌላው ባገር አያስቀምጥህም ። ስድቡ ፣ ሽሙጡ መከራ ነው ። ተሰው ጋር ባረባ ነገር የተጣላህ እንደሆን ፣ 'በመገ፡ርመሪያ የወንድምህን ደም መልስ ፤ የወንድምህ ገዳይ እኔ መሰለሁህ እንዴ!' ይልሃል ። አንዱ የሞተ እንደ ሆን ያለፈውን እያነሱ ማልቀስ ያለ ነው ። ደም ያልመለሰ እንኳንስ እሱና ዘር ማንዘሩ እንደ ተሰደበ ነው የሚኖረው ። ቤተክርስቲያን መሳሚያ ፣ ልቅሶ ማልቀሻ ያጣል ።

"ወደ ጫካ ስገባ ያሳደገሁት ውሻዬ ፣ ኮስትር ተከትሎኛል ። ተሆዱ ገደማ ትንሽ ነጭ አለበት እንጂ በተረፈ አጠቃቆሩ እንዝገ! ይመስላል ።

የዚህ እምነት መልክ ያለው ውሻ ባዳኝነቱ የታወቀ ነው ። አሳዬር ምንሽሬን አቋምጬ ይዤ ስራመድ በያሻም ፍላት ነው ። አስር ጊዜ በአእምሮዬ የሚመጣብኝ፣—

'ወረታው ተበጀ ምን ወንድም አለው ፤

እንደ አህያ ሬሳ ወድቆ የቀረው'

የሚለው ነው ።

''እንዲሁ ሜኪ ለሜኪ ስል ውዬ ማታ ስገባ አባቴ ተመደቡ ላይ ተቀምጦ ጥሬ መሳይ ይቆረጥማል ። እንደምን ዋላችሁ ስል መልስ አልሰጠኝም ። እናቴ ብቻ ፣ 'እንደምን ዋልህ ልጄ!' አለችኝ ። ሃዘን አጥንቷን ሰብሯታል ። ተሞተው ልጅዋ የበለጠ ለኔ ትመሽካለች ፤ ትደቃለች ። ቆሎ ብላ እንጀራ አቀረበችልኝ ።

''ለውሻውም ስጪው'' ስላት ፣ አባቴ ቀበል ብሎ ፣ 'አብረሽ አቅርቢላቸው! የውሻ ጓደኛ አበጅቷል ። እየ ነዶ መሞት!' አለ ።

'ምነው ዝም ብትል ፤ ምን አድርግ ነው የምትለው ? ጓደኛውን ፣ ወንድሙንማ ገለውብታል ። ይሆንም አትቸኩል' አለችው ፣ እናቴ እንባዋን እያፈሰሰች ። አባቴ ዳግመኛ አልተናገረም ። እኔም እርቦኝ የነበረው በነገር ሲወጋኝ ጊዜ ወስፋቴ ተዘጋ ። እጄን አባብሼ ፣ አንገቴን ደፍቼ ተቀመጥሁ ። ንግግር የሚባል ነገር የለም ። ቤቱን ዝምታ ዋጠው ። ቤተሰባችን ሰላም ያጣው ወንድሜ ተሞተ ወዲህ ነው ።

“ወገግ ሲል ኮሰትርን አስከትዬ ወደ ሜካዬ ሄደሁ ። መሸፈቴ በመንደራችን እንደ ተወራ ውሻ ዬም አብሮ መሸፈቱ ተሰምቷል ። ሙቼም የሰው ተረብ አይድረስብህ ነው ። የውሻን ጓደኛነት ግን የሚያውቅ ያውቀዋል ። ተኮስትር ጋር ብዙ ስራ ሰርተናል ።

“እኩለ ቀን ላይ ኮስትርን አስከትዬ ሜካ ለሜካ ስሹለከለክ አንዲት ሚዳቋ ዱር ውስጥ ተወ ትፋ አገኘን ። ጠመንጃዬን ስደግን ፈትለክ አ ለች። ኮስትርን ያዝ አለሁት ። እንደ ቀስት ነው የተወ ረወረው ። እየሮጥሁ ብቅ ስል ተመሬት ቀላቅሏ ታል ። ጉሮሮዋን አንቋት ያለ የሌለ ሃይሏን ትንፈ ራገጣለች ። ያባቴን ሙሉ ትጥቅ እንዳለ ነው የያ ዘሁት ። የዝናር ካራዬን ላጥ አድርጌ አንገቷን ሰየ ፍሁት ። ኮስትር ግዳይ መጣሉን ለማብሰር በኋላ እግሮቹ መሬት እየቆፈረ ሲያጉመተምት ድምጡ ያንበሳ ይመስል ነበር ። የጠመንጃዬን አፈሙዝ ደም ቀባሁት ። የገዳይ ጠመንጃ አፈሙዙ ደም ይቀባል ሲሉ እሰማ ነበር ። ሚዳቋዋን ጎተት አድ ርጌ ኮስትርን ደሙን እንዲጠጣ አዘዝሁት ። በልቡ ተንበልብሎ ተኛና በጉምጅታ አቀላጠፈው ። እኔም ደሙን ሳይ አንድ አይነት ኩራት ተሰማኝ ። ወዲ ያው ገፏፈፈሁና ፈርሱን አራግፌ ጨጓራውንና ጉበቱን ትኩሱን ላጥ ላጥ አደረገሁት ። የዚህን አይነት አበላል የፃገረኝ አባቴ ነው ። አራቱን እግ ሮች ነቅዬ ቡቶዳው ጠቅልዬ አስቀመጥሁና የቀረ ውን ተኮስትር ጋር ተካፍለን በላን ። መጎራረስ

ነው የቀረን ። ማታ ስገባ አባቱ ደስ ብሎት በፈግገታ ተቀበለኝ ። ”

‘ወጉም ፣ ደንቡም በመጀመሪያ ባውሬ ነው መለማመድ’ አለኝ ፣ ጠመንጃዬን እየተቀበለኝ ። እናቴ ግን ትንፍስ አላለችም ። አባቴ ጠመንጃዬን እያገላበጠ እያየ ፡—

‘እንዴት ነው ወደ ቀኝ ያደላ ነበር ፤ እራስ ምኮ ይሄዳል አላስቸገረህም?’ ሲል ጠየቀኝ ።

‘አላስቸገረኝም’አልሁት ።

‘ባንድ ጊዜ አልመህ ገደልሃት?!’ ጥያቄው የመደነቅ ነበር ።

‘ዛዲያ ለሚዳቋ ስንት ጊዜ ላልም’ አልሁት።

“ኮስትር የሚታዘበኝ ይመስል ዘወር ብዬ አየሁት ። ሆዱ ስለ ጠገበ ተቤቱ በራፍ ላይ ተጋ ድሚል ። ኮስትር በጣለው ግዳይ ካባቴ ጋር ስም ምንት ፈጠርንበት ። መዋሸቴ ግን ቅር አሰኘኝ ። ምን ላድርግ እኔ አይደለሁም ፣ ኮስትር ነው ብለው፣ ‘ካንተስ ውሻው ይሻላል’ እንደሚለኝ አይጠረጠ ርም ።

“እራት ስንበላ ፣ ‘ስጋዋ ሽንኩርት ነው ፤ ገና ልጅ ኖራለች ። ለመሆኑ ተምኗ ላይ ነው የመታ ሃትነ’ በማለት ጠየቀኝ ። ያላሰበሁበት ጥያቄ ስለ ሆነ መልሱ ተደናገረኝ ።

‘እባክህን ተወው ፤ እሱ መግደሉን እንጂ ተምኗ ላይ እንደመታት አላየም’ ብላ እናቴ ገላገለችኝ ።

'የለም ብልት አይቶ መምታት አለበት እንጂ። አለዚያማ ዋጋ የለውም' አለ አባቴ ።

'ብልት ምን ምን ነው?' አልሁት ።

'ዋናው ጭንቅላት ነው ። በተረፈ መሀል ደረቱን ታልሞ ልቡ ስሁለት ነው የሚከፈለው። ተዚህ ሌላ የመሞት እድል ቢገጥመውም ቶሎ ነፍሱ አይወጣም ። አውሬ ተሆነም ያበሳሻል ፤ ባለንጋራም ተሆነ ጦሉሱንይስጣል ። ለዚህ መድ ሃኒቱ ብልት አይቶ መምታት ነው ። አለዚያማ ሁሉም ተኳሽ ነው' በማለት አስረዳኝ ። በርግጥም አባቴ ቢኩራራ ይገባዋል ። ደህና ተኳሽ ነው ።

"አባቴ ከራት በኋላም ሁሉን ነገር ሲመክ ረኝ አመሸ ። ሌሊት ሲመሄድ ስነሳ አባቴም ፣ እና ቴም ተመኝታቸው ተነስተው በር ድረስ ሸኙኝ። የሌሊቱ ብርድ ስቃይ ነው ። የለበስኋት ነጠላ ተጨ ለማው ጋር እንድትመሳሰል ቅቤ የጠገበች ናት። 'እስቲ ተከናነበው ለብርዱ' ብላ እናቴ ወደ ራሴ አለበሰችኝ ። ጭንቅ ጥበብ ብኋታል ።

'ተዪው ይሂድ አታቁሚው' አለ አባቴ ፣ ወደ ኋላ እየቀረ ። ኮስትሮም ብርድ ይዞት ጠጉሩ ቆሟል።

"ኮስትር በገደላት ሚዳቋ የወንድነት ቀሚስ ስለ ለበስሁ አንድ ግዳይ ሳልጥል ወደ ቤት ላል መለስ ምያለሁ ። ባለ ደሞቹ ደሞ በቀላሉ የሚ ገኙ አይደሉም ። እርሃብ ሲጠናብኝ ጊዜ አንድ ያባቴ ዘመድ የሆነ እራስ ሚዳ ትዝ አለኝ ። ሽፍታ

ጨለማን ተገን በማድረግ ተዘመድ ፣ ተወዳጅ ቤት እየሄዱ እህል ውሀ መቅመስ የተለመደ ነገር ነው ። ማታ ወደ አጎቴ ቤት ሄደሁ ።

“ታጎቴ ጋር ሌሊቱን ሙሉ ስናወራ አደርን። አንድ አፍጥባቸው የተባለ ሽፍታ በነገላ በኩል ነበር ። ተሱ ጋር ወዳጅነት ስላለው ወደሱ ሊወስደኝ ወሰነ ። ጧት ኮስትርን ለማስቀረት ብዙ ጥረት አድርገን ነበር ፤ በጅ ሳይለን ቀረ ። እሱን እንደያዘን አመሻሽ ላይ ነገላ ገባን ። የሁለት ወገን ሽፍቶች ግጭት ፈጥረው ኖሮ እርቅ አድርገው ፤ አንድ በሬ ጥለው ሲቃበጡ ነው የደረስ ነው ።

“በአፍጥባቸው የሚመሩት ሽፍቶች ዘጠኝ ሲሆኑ ተተከዜ በኩል የመጡት ሽፍቶች ደሞ ሰባት ነበሩ ። የጠባቸው መነሾም ወደ ሰቆጣ የሚሄዱ ነጋዴዎች ያፍጥባቸውን ስም እየጠሩ ሳለ ፣ እነዚያኞቹ ሽፍቶች በመቀማታቸው የተነሳ ነው። የርቁ ዋና አላማም ወደ ሰቆጣ የሚሄድ ነጋዴም ሆነ መንገደኛ ያፍጥባቸውን ስም ተጠራ በክብር ሊያሰልፉ ፤ ተወደዚያ የሚመጣም ነጋዴ እንዲሁ የነዚያን ስም ተጠራ እነ አፍጥባቸው በክብር ሊሸኙ ሆኖ ነው ።

“አፍጥባቸው አጠር ያለና ጠይም ነው ። ታልተቆጣ በስተቀር እፊቱ ፈገግታ የማይለየው ፣ አይኖቹ ተዳር ወጥተው የተቀመጡ ነው የሚመስሉት ። አፍጥባቸው የተባለበት ምክንያት ሲቆጣ አይኖቹ ተጎልጉለው ስለሚወጡ ነው ። እውነተኛ ስሙ ግን እረታ ነበር ።

“በማግስቱ ጧት አጎቴ ሁሉን ነገር ተነገረው በኋላ ሁለት ጠገራ ብር ገጠ በረከት ሰጥቶት ተመለሰ ። እኛም ተተከዘ በኩል የመጡትን ሽፍቶች ለመሸኘት ሄድን ።

“ሽፍቶቹን ሸኝተን ስንመለስ ተከዜ በረሃ ላይ የተኩስ ልምምድ አደረግን ። የኔም መፈተኛ የዚያን እለት ሆነ ። ሁሉም የታዘዙትን ኢላማ ጥሩ ኢያደረጉ መቱ ። አንዱ ብቻ ሳተ ። አፍጥባቸው ክፉኛ ወረፈው ። በዚህ ጊዜ እኔ የሳትሁ እንደሆን ብዬ ፍርሃት ያዘኝ ።

‘አንተ ተኔ ጋር ነው የምትወዳደረው ። አባትህ ደህና ተኳሽ መሆናቸውን ሰምቻለሁ ። የዠግና ልጅ ዠግና ነውና አንተም ተኳሽ እንደምትሆን እርግጠኛ ነኝ’ አለኝ ፤ ተገጠጠው ገደል ላይ ነጩን ያሞራ ኩስ እየተመለከተ ፤ ‘ተመልከት የኔ ጥይት የት ላይ እንደምታርፍ’ አለኝ ፤ ግራ አይኑን እየጨፈነ ። ምላጭ ሲስብ መሃል ለመሃል በረገደው ! እውነትም የሽፍቶቹ አለቃ ሊሆን ይገባዋል አልሁ በሆዴ ።

‘አሁን ያንተ ተራ ነው ። ተዘጋጅ’ አለኝ ፤ ቀለሁን እያፈናጠረ ። ሰውነቴ መርበትበት ፤ ልቤ ተላይ ተላይ መምታት ያዘ ። በርከክ አልሁና አነጣጠርሁ ። ትንፋሼን ዋጥ አድርጌ ተኮስሁ ። ጥይቴ ግና ተኢላማው ራስ ሄደች ። በብሽቀት ሽምቅቅ አልሁኝ ። አፍጥባቸውም ፊቱ ልውጥ ሲል አየሁት ። እንግዳ በመሆኔ ነው መሰል እንደዚያኛው

ሽፍታ አልተቆጣኝም ። ጭፍሮች ግን በመሳቴ ደስ አላቸው ። አፍጥባቸው ተኳሽ ነህ ብሎ ተሉ ጋር ስላወዳደረኝ ቀንተው ነበር ።

'ጠመንጃህ ራስ ይሄዳል ፤ ትንሽ ወደ ቀኝም ያደላል ። እስቲ እንደ ገና ሞክር' አለኝ ። ይህን ነገር አባቴም ነግሮኝ ነበር ። እኔም ምስጢሩ አል ገባኝ ብሎ ተቸግሬለሁ ። ዝቅ ሳደርግ ግርጌ ይሄ ዳል ፤ ከፍ ሳደርግ ደግሞ ራስጌ ይሄዳል ። አጭር ምንሽር ጠባው አስቸጋሪ ነው ። ለዚህ ጥሩ ጠመ ንግሮ ረኝም እልቤን ነው ። አይነቀንቅም ። ታሉ በት ቦታ ልክክ ነው ። የሱ ሰሃ ጥይቱ አጥንት ታሳገኘ ለጉዳት አይሰጥም ። በመሳሪያ ጥራት ግን ምንሽር ተበልጅግና ተዲሞትፈር ቀጥሎ ደረጃ አለው ። እንዳወም አንዳንዶቹ ምንሽርን የሚያስ ንቅ የለም ፤ ሲመታ አንጀት አርስ ነው ይላሉ ። በልጅግን በለስ የለውም ፤ ዲሞትፈርን ደግሞ እርቀት አይሄድም ይሉታል ። ብቻ ሁሉም እንደ ልምዱ ነው።

"ተራስ ትንሽ ዝቅ ፣ ወደ ግራ ትንሽ እልፍ አድርጌ አለምሁና ስቤብ መሃል ለመሃል ስነጠ ቅሁት ። 'አሁን ጥሩ ነው! ተዚያው ላይ ድገመው!' አለኝ ፣ አፍጥባቸው በደስታ ጩሀ ።

"ተዚያው ላይ ደገመሁት ። ተዚያን እልቅ ዝምር አይነ ሞራዬ ተገፈፈ ። ከዮውንም ተወ ዳዳሪ የሌለኝ ተኳሽ ሆንሁኝ ።

"ውድድሩን ጨርሰን ተለ ሆን ። ይህ ሁሉ ሲሆን ኮስትር ታጠገቤ አይለይም ። አፍጥባቸውም

እኔን ብቻ ሳይሆን ኮስትሮንም ወደደው ። ሌሎቹ ሽፍቶች ግን በኔ ላይ ብርቱ ቅናት አደረባቸው

"መቼም የሽፍታ ኑሮ ታውሬ አይሻልም ። ተመንግስት ተሰውሮ ፣ ተበላንጋራ ሸሽቶ ነው ። ተሁሉም የከፋው ደሞ እስበስ አለመተማመኑ ነው ። ሽፍታ ምን ቢዋደድ ፊትና ኋላ እንኳን አይ ሄድም ። 'ኸርብና ሽፍታ ጓደኛውን አያምንም' የሚ ባለውም ለዚህ ነው ። አንዱ በገንዘብ ተገዝቶ የገዛ ጓደኛውን ሲገል ይችላል ። ሌላው ጓደኛው ተሱ የተሻለ ጠመንጃ ተያዘ ለጠመንጃው ሲል ይገለ ዋል ። ወይ ደሞ ተሱ የተሻለ ተኳሽ ተሆነ በቅናት ይገለዋል ። እንዲህ እየሆነ ባላንጋራ ተሚገለው ይልቅ እስበሱ የሚጋደለው ይበልጣል ።

"ሁሉን ነገር እየተለማመድሁ ታፍጥባቸው ጋር ሶስት ወር ተቀመጥሁ ። አንድ ቀን የወንድ ሜን ደም ሄጄ እንድመልስ ጠየቅሁት ። ፈቃደኛ ሆኖ ተሁለት ሽፍቶች ጋር ገለን እንድንመለስ ላከን።

"ተመንገድ ጠብ ፈጠርን ፤ 'ውሻ ይዘን ደም መመለስ አንችልምና ውሻህ መገደል አለበት' አሉኝ ።

'ቀየሚታችሁ በውሻው ተሆነ እንደ ደረስነ ተመላጆቹ እተወዋለሁ' ስላቸው :—

'ዶ·ህማ የባሰ መጥፎ ነው ። ውሻህ ተወላጆ ችህ ዘንዳ ተቃዩ አንተ መምጣትህ ስለሚታወቅ ባለ ደሞችህ ይጠነቀቃሉ ። ስለዚህም ውሻህ መገ ደል አለበት' ብለው ቆረጡ ።

'የወንድሜ ደም ሳይመለስ ይቅር እንጂ ውሻዬ አይገደልም' አለሁና እኔም ቆረጠሁ ። በዚሁ ምክንያት ተኳርፈን ሳንነጋገር ዋለን ።

"ጊዜው ድንግዝግዝ ብሎ ላይን ያዝ ማድረግ ዠምሯል ። ቆም ብለው የብቻቸው መመካከር ያዙ ። እኔን ሳይጨምሩ የብቻቸው የሚመካከሩበት ምክንያት ለምን ነው? አለሁና ተጠነቀቀሁ ። ቀድሞውንም ቢሆን ውሻውን እንግደለው ያሉት ለጠብ ማንሻ ብለው እንጂ ለመግደል ያሰቡት እኔን ነበር።

'እንግዲህ ውሻህን ልንገድለው ነውና እንዳትደረብ ግለጥ!' አሉኝ ፣ ጠመንጃቸውን እያቀባበሉ።

'ብትፈልጉ አሁኑኑ ተመለሱ እንጂ ውሻዬን አትግደሉብኝ ። በፈጠራችሁ!' ብዬ እስክን ውሻዬ እራጩ ታንዶ ጳጢኝ ስር ስወተፍ ፣ በሩምታ ተኮሱብኝ ። እንደ ተመታሁ ሁሉ አ...ብዬ ፀጥ አለሁ ። መቼም ቀልባቸው ያለው ተጠመንጃዬ ላይ ነው ። ተንደርድረው ሲመጡ አንደኛውን ደፋሁት። ተዚህ በኋላ ውሻዬን ይገፎ እግሬ አውጭኝ አልሁ ። ሁለተኛው እየተከታተለ ተኮሰብኝ ። ጨለማው ስላገዘኝ አልተገኘሁትም ።" '

## ሰባት

“ሌሊቱን ስገሰግስ አድሬ ተረፋዱ ላይ ተዘመዶቼ ዘንዳ ፥ መስቀች ደረስሁ ። ኮስትር ጅራቱን እየቆላ ተናትና አባቴ እግር ላይ በመጠም ጠም ናፍቆቱን ገለጠ ። እናቴ ሁኔታው አሳዘናትና ፥ ‘አንተም ፈርዶብህ’ አለች ፥ እንባዋ በጉንጮቿ እየፈሰሰ ። ተመንገድ የገጠመኝን ችግር ስነግራቸው ክው ብለው ደነገጡ ።

‘ምነው ልጄ ምነው አልታሰበ ደም ተዘፈቀህ? የራሳችንን ሳንወጣ! አይይ. . .’ አለ አባቴ ፥ በብርቱ እየተከዘ ። እናቴ ድምጧን አጥፍታ ቃለ ቅስ ጀመር ።

“እየውልህ ! ያላሰብነው ባላጋራ በማፍራታችን ሌሊቱን ስንዘጋጅ አድረን ንጋት ላይ ቃባቴ ጋር ጫካ ገባን ። ተብርዱ ጋር ቁርጥማቱም ፥ ክፉኛ ተፍተለተለ ። ጭራሽ መንቀሳቀስ አቃተው ። ጨለማው በውል አልገፈፈም ፤ ይባስ ብሎ ድን ጋይ አንቀፈወና በቁሙ ዘፍ አለና ወደቀ ። እሩጬ ተወደቀበት አነሳሁት ። ተዚህ በኋላ መራመድ አልቻለም ። ተጫካው ውስጥ አስተኝቼ ተውሻዬ ጋር እሱን መጠበቅ ሆነ ።

'አልሆንልኝም ልጄ' አለኝ ፣ በሽተኛ እግሩን መሰብሰብ ተስኖት 'እንዳው የደም ማባገር እሆ ናለሁ ብዬ እንጂ ለነፍሴ ፈርቼ አይደለም ። ተን ግዲህ ወዲያ እኔ ጫካ ገብቼ ። እረ ወዲያልኝ!' ሲል ክፉኛ ተማረረ ። ተዚያው ጫካ ውስጥ ሶስት ቀን ውለን አደርን ። የያዝነው የለት ስንቅም አለ ቀብን ። አውሬ ማደን ወይንም ወደ መንደር ሄዶ ምናምን መፈለግ የወግ ነው ። አባቴ ህመሙ እየጠናበት መጣ ። ድኩላ ወይንም ሚዳቋ ለማ ደን ስነሳ ኮስትር አብሮኝ ይነሳል ። አባቴን ብቻ ውን ጥየው ለመሄድ ደሞ ከበደኝ ። ተናደደሁና እዚሁ ቆይ ብዬ በሰደፍ ደቃሁት ። እሱም የዋዛ አይደል ዘሎ ተከመረብኝ ። ደግነቱ አጥብቆ አልነ ከሰኝም ። ሁለታችን ስንታገል አባቴ በመገረም ይስቅ ነበር ።

'የዚህን ውሻ መጨረሻውን አይቼ! ተወው ይሂድ ፣ እኔ እንደሆንሁ ምንም አልሆን አትስጋ' አለኝ ። መንገድ ስዠምር ያው አልቀረም ተከተ ለኝ ። ቀስ እያለን ፣ ግራም ቀኝም እያስተዋለን ትንሽ እንደ ሄደን አንዲት ድኩላ አገኘን ። ኮስ ትር ለመወርወር ወገቡን ሲሰብቅ አንቅ አደረገ ሁት ። ወደ መሬት ለጥ አለ ። ሁሉን ነገር ለም ዲል ፤ ያዝ ካላለሁት ነቅንቅ አይልም ። እሱና እኔ የምንጣላው ተኔ ተለይ ያለሁት እንደሆነ ነው ።

"ድኩላዋ ቅጠል እየቆነጣጠሰች ዠሮዎቿን አፅር ጊዜ ታፈግፋለች ። ተቋንጃዬ ሸብረክ ብዬ አስመሁባት ። ጥሩ ፁና ገባችልኝ ። ምላጭ ስስብ

አልተንቃነቀችም ፤ ተዚያው ላይ ኩርትም እንዳ ለች ቀረች ። ግሩም አመታት ነው ፤ ተወርቿ ላይ ነበር የመታኋት ። እኔ ያላየሁት ወንዱ ድኩላ ታጠገቧ ኖሮ ቁልቁል ሲሮጥ ኮስትር እሱን ተከ ትሎ ሮጠ ። እኔ ተወደቀችው ድኩላ ስደርስ ትን ፈራገጣለች ። የወገቤን ካራ ላጥ አድርጌ አንገቷን ባረከሁት ። ወዲያው ኮስትር እያለከለከ ደረሰ ።

"ጠመንጃዩን በወገቤ አንግቼ በትከሻዩ ተሸከመኋት ። ኮስትር ተሸክሙ የሚያግዝ ነገር አይደለም ። ደሙ እየተንጠባጠበ ልብሴን አበላ ሸብኝ ። ሸክሟም የዋዛ አይደለም ። እያንዘባዘበሁ ታባቴ ስደርስ የተኩስ ድምጥ ሰምቶ ስለነበር ዛፉን ተደግፎ በመቀመጥ ፣ በንቃት ሲጠባበቅ ነው የደረሰሁት ። ወስደሁና እፊቱ ላይ ጣልኋት ።

'ጠላትህ እንዲህ ዘፍ ይበል! የወንድምህን ደምም መልሰህ ለማየት ያብቃኝ' በማለት መረቀኝ። ወዲያው ገነጣጠልንና እንደ ተለመደው ጉበቷንና ጨጓራዋን ትኩሱን በላን ። የዚያን እለት ወደ ቤታችን ለመሄድ ወሰን ።

"ምሽት ላይ ስጋዋን በቆዳዋ ጠቅልለን አሰርንና እኔ ተሸክሜ ጉዞ ገርመርን' ። እንደ ምንም ተንኳተን ደረስን ። እናቴ አንደኛዋን በሀዘን ጭብ ጥብጥ ብላ አገኘናት ። እንደ ቀድሞዋ እኔን አላ ነጋገረችኝም ። ባባቴ ሀሙም ትንሽ ተከዛ ምግብ አቀረበችልንና ፣'በሉ ብሉና ቶሎ ቦታችሁን ያዙ' አለችን ።

'ምነው? ደሞ ምን ተፈጠረ? ደህናም አይደ ለሺ እንዴ?' ሲል አባቴ ጠየቃት ።

'ምን ደህንነት አለ ። አፍጥባቸው አጎታች ሁን ገሎት ሄደ' አለችን ። አባቴም ፣ እኔም ትን ፍስ አላልንም ። በጃችን የያዝነውን እንጀራ ተሞ ሰበ ላይ ጣል እያደረገን አንገታችንን ደፋን ። ያ—የዋህ አጎቴ እኔን ታፍጥባቸው ወስዶ በማስ ተዋወቁ የደም መመለሻ ሆነ ።

"አባቴ ህመሙ ስለ ጠናበት መንቀሳቀስ አልቻለም ። እኔ ኮስትርን ይዤ እኩለ ሌሊት ላይ ወደ ሜካዩ ሄደሁ ። አንድ እጣ ነፍሴን ተሁለት ባላንጋራዎች ጋር ተሰላለፈሁ ።

"ላንድ ሳምንት ያህል ወደ ቤት ሳልመለስ የወንድሜን ገዳዮች መፈለጌን ቀጠለሁ ። አክርማ በተባለው ሜካ አዘውትረው እንደሚውሉ ሰዎች ነግረውኛል ። ወደዚያው ስሄድ ተሙንገድ ነጩ ዝንጀሮ አገኘሁ ። በጥይት ለመግደል አሰበሁና የወንድሜ ገዳዮች ተቅርብ ታሉ ተኩሱን ይሰ ማሉ ብዬ በመስጋት በኮስትር እያባረርሁ ተገደሉ አፋፍ ደረስሁ ። መንጋው ዝንጀር ዳገቱን ሲዳፉ ኮስትር ተከትሎ በዳገቱ ተዳፋ ። እየሮጥሁ ታፋፍ ብቅ ስል ተሁለተኛው እርከን ላይ ኮስትር ይለ ፈልፋል ። ዘቅዝቄ ስመለከት አራት ግመሬ ይቧ ጨቀዋል ። ቁጭ አልሁና ስተኩስ አንደኛውን ግመሬ አገኘሁት ። የቀሩት ብትንትናቸው ወጣ ። የዝንጀሮው ጩኸትና ጫጫታ ገደሉን ሲናድ የደረሰ አስመሰለው ።

“ዳገቱን እየዘለለሁ በደረስ ውሻዬን እንጀቱ ተዘርግፎ አገኘሁት ። ቀና ሳደርገው ዝልፍልፍ አለብኝ ። ተዚህ በኋላ ነፍሴን አላወቀሁትም ። ጥይት ድረሽ እያለሁ ዝንጀሮ አባርር ገመር ። ግና አንድም አልገደለሁ ። ሶስት የምንሽር ጥይት መና ቀረ ። ተመልሼ ተውሻዬ ስሄድ ተዘቅዝቆ እንደ ወደቀ ነው ። እንጀቱን ዝንብ ወሮታል ። ታጠገቡ የመታሁት ግመሬ ለመሮጥ መሬት እየ ጋጠ ይልሞሰሞሳል ። አፈሙዝ አስነክሼ ጭንቅ ላቱን በተንሁት ። ትንሽ ንዴቴ በረደልኝ ።

“የዝንጀሮውን ቆዳ መግፈፉን ትቼ የውሻ ዬን ህይወት ለማትረፍ እንጀቱን ወደ ሆዱ መለ ስሁና በነጠላዬ ወገቡን ግጥም አድርጌ አስሬ ፣ እንደ በግ በትከሻዬ ተሸክሜ ያን ዳገት እየወደ ቀሁ እየተነሳሁ ይዤው ወጣሁና ተጥላ ስር አሳ ረፈሁት ። ተላይ ተላይ ትንፍስ ትንፍስ ይላል ። አይኖቹ ክፍት ግጥም ይላሉ ። ሰው ቢሆን ስንቱን በለፈለፈው ። ላቤን ጠራረግሁና ተሸክሜ መንገ ዴን ቀጠለሁ ። አሳቤ ነፍሱ ሳትወጣ ታባቴ ይዤ ለመድረስ ነው ። በወገሻኘቱ የተደነቀ ነው ። ግል ገሎች ሲሰበሩ እየጠገን ያድናል ። ቶሎ ይዤው ተደረስሁ እርግጠኛ ነኝ ሆዱን ሰፍቶ ያድነዋል ።

“እንዲት ያክርማ ወንዝ አለች ፤ ተሷ ልደርስ ቁልቁለቱን ስያያዝ የወንድሜን ገዳዮች ተማዶው ሲመጡ አየኋቸው ። እነሱ አላዩኝም ። አካሄዳቸው የጥድፊያ ነው ። የጥይት ድምጥ ስለ ሰሙ እኔን ፍለጋ ነው ። ቶሎ አለሁና ጫካ ውስጥ ገባሁ ።

ላንዳፍታው የወረረኝ ነገር ላብ አጠመቀኝ። ቀናኝም አልቀናኝ ዛሬ ነው አለሁና ኮስትሮን ተዛፍ ስር አስተኝቼ እየተጣደፈሁ ወደ መንገዱ ዳር ወጣሁ ። ወንዙን ተሻግረው ተቀናጋው ደር ሰዋል ። ትልቅየው ፊት ፊት ነው ። ሁለቱ ግራና ቀኝ ሁነው ተኳላ ናቸው ። አሁንም አረማመዳቸው የችኮላ ነው ። የሆነው ይሁን አለሁና ዱር ተከልዬ ጠበቀኋቸው ። እየቀረቡ ሲመጡ ልቤ በሲቃ ይመታ ዠመር ። ሰውነቴን አረጋጋሁና ተትልቅየው ላይ አለምሁበት ። ትንፋሼን ዋጥ አድርጌ ምላጭ ስስብ በደረቱ አስገባሁበት ። ወደ ሰማይ ጉኖ ነው መሬት ላይ ፍርጥ ያለው ። አልፎከረሁም ። ሁለቱ ወንድማማቾች ፎከሩና እንደ ተመቱ ሁሉ በያሉ በት ጥቅልል እያሉ ወደቁ ። አውቄባቸዋለሁ ፤ ፎከሬ ብቅ ስል ሊቀልቡኝ ነው ። ብዙ አድፍ ጠው ጠበቁኝ ፤ ደግሜም አልተኮስሁ ። የተመታው ትንሽ እንኳን ፍርግጥ አላለም ። ተመንገዱ ላይ በዠርባው ወድቆ ይታየኛል ። የውር የድንቡሱን አከታትለው ተኮሱ ። መልስ አልሰጠሁኝም ። ትንሽ አዳመጡና መሀከለኛው በደረቱ እየተሳበ ወደ ተመታው ሲሄድ ትንሽየው አልሞ ይጠባበቅ ዠመር ። ሁለቱም መሬት ስለ ያዙ አልተመቹ ኝም ። ሷተኩስ ያለ ጥርጥር እስታቸዋለሁ ። ተራሱ ቀና ሲያደርገው አንገቱ ዝንፍል ሲል አየ ሁት ። ነፍሱ ማለፏን አረጋገጠሁ ። አመቻችቶ አስተኛውና የወገቡን ዝናር ፈቶ ፣ ጠመንጃውን እየጎተተ የኋሊት ሲያንፏቅቅ አላስቻለኝም አከታ ትዬ ብልጭ ብልጭ ሰጠሁበት ። ቶከራ ብቻ ሆኑ ።

አሁንም ድምጤን አላሰማሁም ። ዬካርታየ ጥይት አልቆብኝ ሌላ ሳስገባ ትንሽየው አየኝ ። ተዚህ በኋላ እነሱ ሁለት ሆነው እኔ ብቻዬን ተኩስ ገጠምን ። እኔ እረጋ ብዬ እየጠበቅሁ ነው የምተኩሰው ። እነሱ ግን በደም ፍላት ነው የሚለቁት ። አንዱን እደግመዋለሁ ስል ሌላ ዘዴ ተጠቀሙብኝ ። ትንሽየው እየተኮሰ ፣ መሃከለኛው እንደ እባብ በልቡ እየተሳበ መጣብኝ ። እንደ በግ ግልገል ሊያንቀኝ ነው ። ትንሽየውን ጠበቅሁና የካርታውን ጥይት ጨርሶ ሌላ ካርታ ሲያስገባ ተተኛ ሁበት ተነስቼ ተፈተለክሁ ። ኮስትሮን ይዤ ለማምለጥ አልቻልሁም ። ብዙ እየተከታተሉ ተተኮሱብኝ በኋላ የወንድማቸውን ሬሳ ለማንሳት ሲሉ ተመለሱ ።

"እየገሰገስሁ ተቤት ስደርስ ጠሀይዋ ጠልቃ ነበር ። አባቴን ይገር ለመሸሽ ተበሩ ድረስ ሞከሩሁት ። ልውስውስ ብሎ አልሆነለትም ።

'አልሆነልኝም ልጄ ፤ አንተ አምልጥ ። ተንግዲህ ወዲያ እኔ ምን ልጨምር ። ሴትና ሽማግሌ ገለው ዝና ታገኙ ይግደሉኝ ። እንኳን የልጄ ደም መመለሱን አየሁ እንጂ ለኔ ሞትስ አታስብ' አለኝ ። ነገሩ ጥድፊያ ስለ ሆን ለመመካከር ጊዜ አላገኘንም ። እናትና አባቴን ጥየ ሸሸሁ ።

"አባቴ እንዳለው ሴትና ሽማግሌ ፣ ሀጣን የሚገድል እንደ ዠግና አይቆጠርም ። ሲላቅበት ነው የሚኖረው ። እኔ እንኳን የነሱን አባት ፣ አቶ

ፈንቴ መንገሻን ሁለት ቀን አግኝቼው ነበር ። አባቴ ነው ፥ 'አይሆንም ሽማግሌ ገለህ ቁራሽ እንጀራ ፣ እፍኝ ውሀ የሚሰጥህ የለም' ብሎ ስለ ተቆጣኝ የተወሁት ።

"ጭጊጊት ተራራ ተቀምጬ ያባቴን ቤት በጨረቃዋ ብርሃን ዘቅዝቄ ስመለከት ሁለት ጥይቶች ተከታትለው ሲተኮሱ ሰማሁ ። እርቅ ሳይቆይ ደሞ ያባቴ ቤት በሳት ጋየ ።"

# ስምንት

መለኩሴውን ተሰናብቻቸው ገዳሉን ስወጣ ምሽቱ ተቃርቦ ነበር ። በገዳሉ ስር የገዳሉ ጥላ እንደ ጨለማ ጠቁሮ ይታየኛል ። ፀሀይዋ ከምእ ራብ አድማስ ተወትፋ ሰማዩን አቅልታዋለች ። አካሄዴ ፈጠን ፈጠን ያለ ነበር ። እንደ ወጣሁ በመቅረቴ አከስቴ ከከፍተኛ ስጋት ላይ እንደምት ወድቅ ተረድቻለሁ ። ምን ሳድርግ ፤ ያልጠበኩት ታሪክ ገጠመኝ ። ካፋፉ ብቅ ብዬ አግድመቱን ስያያዝ ስጋቴ አልቀረም አከስቴና ሁለቱ አህቶቼ ሲመጡ አየኋቸው ። አካሄዳቸው የድንጋጤና የጭ ንቀት ነበር ።

"ምነው ልጄ? ምን አገኘህና ጥንቅር ብለህ የዋለህ?" አለችኝ ፣ በግራ ቀኝ እጇ ወገቧን ይዛ እየቆመች ።

"አንድ መነኩሴ አገኘሁና ከርሳቸው ጋር ስጫወት ዋልኩ" አልኳት ።

"አባ መሀሪ እንዳይሆኑ! መቼም እሳቸው ናቸው ለወጣ ለወረደው የሚናዘዙት ።"

"አዎን ፣ አባ መሀሪ ነኝ ብለውኛል ።"

"የሳቸው ታሪክማ ሲሰሙት ቢውሉ አይጠ ገብ ። አሳዛኝ ናቸው ። እኔማ ተበተስኪያን ቁመው

ሲሰብኩ ስሰማ በሰመመን ነው የምጓዘው'' በማለት ከንፈሯንም በሀዘን መጠጠችው ።

በማግስቱ ወደ አካለክርስቶስ ምን ምክንያት ፈጥሬ እንደምሄድ ተቸገርኩ ። አክስቴ ሁለተኛ ፈቅዳ እንደማትሰደኝ እርግጠኛ ነኝ ። ያባ መሀሪ ታሪክ ደግሞ ስቦኛል ። በዚያም ላይ እመጣለሁ ብዬ ቃል ገብቸላቼዋለሁ ። ቁርሴን ከበላሁ በኋላ አካባቢውን የምጎበኝ መስዬ ከግቢው ወጣሁና ወደ አካለክርስቶስ ሄድኩ ። ገደሉ እንደ መጀመሪያው አላስፈራኝም ። ቀስ ብዬ እርከን እርከኑን እየረገጥኩ ወረድኩ ። ከቤተክርስቲያኑ አጠገብ ስደርስ አባ መሀሪ ከጥዱ ዛፍ ስር ተቀምጠው አገኘኋቸው ። ገና ሲያዩኝ ከፍተኛ ደስታ ተሰማቸው ። ተመልሶ አይመጣም ብለው አስበው ኖሯል።

''እረ የቁም ነገረኛ ቤት ነው!'' አሉኝ ።

''እመጣለሁ ብየዎት የለም'' አልኳቸው ፤ እኔም ቁምነገረኛነቴን ለማረጋገጥ ።

''አንተስ ብለኸኛል ፤ እግዚአብሔር ያቆይህ!'' በማለት መረቁኝ ።

አቀማመጣችን እንዳለፈው ነው ። አንገታቸውን ዘንበል አድርገው ትንሽ ካሰቡ በኋላ ታሪካቸውን ጀመሩልኝ ።

''እየውልህ ፤ ያባቴ ቤት ነዶ ታለቀ በኋላ አቅጣጫዬን ወደ ደጋው አድርጌ እገሰግስ ገምር። ስንድድ የምታሰኪ ጨረቃ ነበረች ። አሁን ብቻ

ዩን ነኝ ፤ ኮስትር የለም ። ሲነጋጋ አቅራቢያ ታክ ሲቴ ፣ ታባቴ ትንሽ እህት አዲስ አንባ ደረስሁ ። በድንጋጤ እየተርበተበተች በሩን ከፈተችልኝ። አንድ ነገር አልጠየቀችኝም ፤ ተኔው ይምጣ ብላ እንጀራ አቅርባልኝ ቃጠገቤ ኩርትም ብላ ተቀመጠች ። የሆነውን ሁሉ ነገርኋት ።

'እሰይ! ስምህን አደስህ' አለችኝ ፣ ደም በመመ ለሴ ደስ ብሏት ። መልሳ ደሞ ያባቴ ነገር አሳሰ ባትና ፣ 'ያን ደካማ አባትህን አይግደሉት እንጂ። ቤት ተቃጥሎ ፣ ጥይት ተተኩሶ ፣ እረሱስ ገለውት ነው የሚሆን' እያለች ትጨነቅ ጀመር ።

'ውሻዩ ይተርፍ ብለሽው ? በነጠላዩ አሰ ሬው ነበር' ስላት እንደ መቆጣት ብላ :—

'ምኝ ነህ ልበል ልጄ! ለናትና ላባትህ መጨ ነቁን ትተህ ለውሻ!' በማለት በመገረም አገጯዋን ያዘች' ።

''ጎህ ቀደደ ። ወፎች መንጫጫት ጀምረዋል። በትካዜ ላይ እንዳለን ጥና ዉሪ ተጠራ ። አክስቴ እየተርገበገበች ወደ ውጪ ወጣች ። እኔ ገሮዎቼን አቋሜ አዳምጥ ጀመር ። አክስቴ ከውጪ ሁና ታለቅስ ጀመር ። እኔ እንዴት ብዬ አፌን ከፍቼ ላልቅስ? እንባዩን ብቻ አፈስ ገባሁ ። ጎረቤት ሳይ ሰበሰብ ቶሎ ገባችና ጓዳ ውስጥ መኝታ አዘጋ ጀችልኝና ገብቼ ኩርትም ብዬ ተቀመጥሁ ። ጎረ ቤቱ ሁሉ ተሰብስቦ ሲያስተዛዝናት አረፈደ ። እቃ የምታዘጋጂ እየመሰለች ጓዳ እየመጣች ፣ 'አይዞህ

ቻለው እንጂ መችስ ምን ይደረግ' ትለኝ ነበር ። የሚበላ ነገር ታዘጋጅችልኝ በኋላ ትቀብሩ ለ— ድረስ ወደ መስቀች ሄደች ።

"እኩለ ቀን ላይ ሀዘኑም ፣ የሌሊቱም ውርጭ፣ ብስጭቱም ተደራርቦ ውሃጥም ቅጥል አደረገኝ ። እተቀመጥሁበት ተነሳሁና ውሃ ስፈልግ ሰባራ ቅሉም ፣ ቆርቆርውም ተንኳኳብኝ ። ተሰው ጓዳ ውስጥ እቃ መፈለግ ችግር ነው ። መንጋ ከብት የገባበት አስመሰልሁት ። ተውጪ የሰው ድምጥ ስሰማ ጊዜ ፈራሁና ውሃውንም አግኝቼ ሳልጠጣ ተመልሼ ከመቀመጤ የቤቱ በር ተከፈተ ።

'ድመት ነው ውሻ ይህን ቤት የሚያንጓጓው?' እያለች ወደ ጓዳው መጣች ። ላንዳፍታው ፍርሀት ወረረኝ ። የት ልደበቅ? ጠመንጃዬን ተጭኜ ላይ ታቅፌ በፍርሀት አፍጥጬ ሳለ ብቅ አለች ። ነፍሷ ተስጋዋ ልትለይ ምንም አልቀራት ። የደረቀ እን ጨት ሆነች ። የኔዋ ገነት ነበረች" አሉና እን ገታቸውን ወደ ሙሬት ደፉ ።

አባ መሀሪ ካጎነበሱበት ቀና አሉና ፣ "እየ ውልህ ፤ ተልጅቷ ጋር ለቅጥበት ተፋጠጥን ። መመ ለስም አልቻለች ። አይኖቿ ተጠመንጃዬ ላይ ተተ ክለው ቀሩ ። ለግለግ ያሉች ፣ የጠይም ፍልቅልቅ ነበረች። ጡቶቿ ግንብር ግንብር ማለት ዠምረዋል። ነጠላ ነገር አልደረበችም ። የለበሰችው ቀሚስ የዘወትር ስለ ሆነ አጠር አድርጋ የሁሉም አይ ነት ጥለት ሳይቀር በተሻሮጎረጎረ መቀነት ታጥቃ

ዋለች ። እየቆየሁ ድኼንጋጤዬ ስለ ለቀቀኝ ፈገግታ አሳየኋት ። ትንሽ ተረጋጋች ።

'እይዞሽ! የጎረቤት ልጅ ነሽ?' ስል ጠየቅኋት። ቃል ሳትናገር አንገቷን በመነቅነቅ መሆንዋን ስት ገልጥልኝ ፣ 'እንግዳው እባክሽን ውሃ ስለ ጠማኝ ስጭኝ' አልኋት ። ታንድ አዘቅት ነገር እንደ ወጣች ሁሉ በረዥሙ ተነፈሰችና ቀስ ብላ ተመልሳ ወጥታ ሄደች ። ምን ያለች ልጅ ናት ውሃ ስጭኝ ብላት ዝም ብላ መሄድዋ ለምን ነው? ለሰው ነግራ ልታሲዘኝ? መቼም ፣ 'ያልጠረጠረ ተመነጠረ' ነውና ጠመንጃዬን አቀባብዬ ስጠባበቅ መጣች—በኮልባ ዋንጫ ጥሩ የገብስ ጠላ ይዛልኝ ። ዋንጫውን ስት ሰጠኝ እጇቿ እንደ መንቀጥቀጥ አሉ ። ውሃ ጥምይ ዞኝ ነበርና ባንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርጌ ጠጣሁት።

'በጣም ጠምቶህል ልድገምህ?' አለችኝ ፣ ገና መናገሯ ነበር ።

'ይበቃኛል ፤ እግዜር ይስጥሽ! ለመሆኑ የማ ነሽ ልጅ?'' ስል ጠየቅኋት ። አባቷን ስትነግረኝ ፣ 'አንችማ የኛው ነሽ' ስል በመዝናናት ፈገግ ዋለሁ ። ንግግር የለንም እንጂ አባቷን አውቃቸ ሳፍ መካፈት ጥሩ ነው ፤ እሷም ዝና ብላ በመቆም፥—

'የሞቱት ያንተ አባት ናቸው?' ስትል ጠየ ቀችኝ ።

'አዎን' አለኋት ።

'ጥቋር ደም መቃባት መጥፎ ነው ፤ ይህ ሁሉ ነገር የደረሰው በወንድምህ ሞት ምክንያት አይደል?'

'አዎን ፣ በሱ ሞት ምክንያት ነው ።'

'አንተን አላውቅህም እንጂ ወንድምህን አውቀው ነበር ። የዛሬ ሶስት አመት መሆኑ ነው መሰል ተድሬ ሳለ አክስታችሁን ሊጠይቅ መጥቶ ኖሮ የምላሹ እለት ተዳሱ ሲፎክርና ሲያቅራራ ለትንግርት ነበር ። አዬ ልጅ እያለ ያላደነቀው ሰው አልነበረም ። በኋላ ሰው ገደለው ሲባል በጣም አዘነሁ' በማለት ትንሽ ታነጋገረችኝ በኋላ ሄደች ።

''ገንት ማታ እራት ይዛልኝ መጣች ።

''ተዚህምኮ አለ ምን አሳሰበሽ' ስላት ፤

'ይህ ማሰብ አይደለም ። ደሞ እህል ውሃ ይነፈጋል ።'

'ስትመላለሽ ሰው ያየሽ እንደሆነ ብዬ ነው' አልኳት ፣ በመስጋት ።

'አይዞህ አትስጋ ፤ የመንደሩ ሰው ሁሉ አክ ሰትህን ተከትሎ ተልቅሶው ሄዷል ።'

''ተቀመጭ አልኳት ቁማ ስለነበር ። ቋንጃ ዋን አጠፍ አድርጋ ቁጢጥ አለች ። እኔ ስበላ እንጀራ እየቆረሰች በፊት በፊቴ ታደርግልኝ ነበር ። በልቼ ታብቃሁ በኋላ ወደ ቤቷ ስትሄድ ጥርጣሬ

ገባኝ ። ሙቁም ደም ያለበት ሰው እንኳንስ ሌላ ውንና የገዛ ጥላውንም አያምንም ። ተጓዳ ወጥቼ በጓሮ አጥር ስር ተወትፌ ውርጭ ሲቆቃኝ አደረ ። ጎህ ሲቀድ ተቤት ገብቼ ተዚያው ጓዳ ውስጥ ተቀመጥሁ ።

“ወደ ማታ ገደማ አክስቴ መጣች ። ልቅሶ ደራሹ ቤት ደጁን ስለ ሞላው እሷና እኔ ተገናኝ ተን መነጋገር አልቻልንም ። የኔን ጓዳ ውስጥ መኖር ማንም ሰው አያውቅም ።

“ማታ ሁሉም በየቤቱ ክትት ሲል ተጓዳ ወጣሁና እሳቱን አጥፍተን የሆነውን ሁሉ ነገረ ችኝ ። አባቴን በሁለት ጥይት ነው መተው የገደ ሉት ። እሬሳውን ቶሎ የሚያወጣው ሰጡ ጠፍቶ ግማሽ አካሉን እሳት በልቶታል አሉ ። እናቴ ሀዘኗን መከፈያ ቦታ አጥታ ትንሽ እህቷ አጋም ውሃ ወሰደቻት አለችኝ ። የኮስትርን ሁኔታ ስጠ ይቃት ፡—

‘ምነው ልጄ የውሻው ነገር ወዘወዘህ ። ታባትህ ሞት በለጠብህ? እናትህስ ቢሆን ተንግ ዲህ ወዲያ ሰው የምትሆን ይመስልሃል? የልጅዋን ሀዘን ሳትጨርስ የባሏ ሲጨመር ፤ ተሞቱት ያል ተሻለህ ያንተ ሁኔታ ፤ ሀዘን ተሰው ቤቱ እስበው እስቲ’ በማለት ተቆጣችኝ ። አክስቴ ለውሻዬ ቅንጣት ያህል አልተጨነቀችም ። እኔ ደሞ አባቴም አንድ ጊዜ ሞቷል ቁርጡን አውቄዋለሁ ። ደሙን መመለስ ነው ያለብኝ ። እናቴንም ምንም ሳደርግ

ሳት አልችልም ። ጎጆ አልቀልስላት በደም ተነክሬ ጫካ ገብቻለሁ ። ውሻዬን ግን የምረሳው ነገር አይደለም ። ወይ ሞቶ ቁርጡን አውቄው ቢሆን ኖሮ የህሊና እረፍት አገኝ ነበር ። እንዴት ብዬ ልርሳው? የሱን ጓደኛነት የኔን ያህል የሚያውቅ ልኝ አጣሁ ። አከስቴ እንደ ማንኛውም ውሻ ነው የቆጠረችው ። የኔ ውሻ ፣ ኮስትር ግን እንደ ውሻ ያለ አይደለም ። እሱ ተጎኔ ቃለ ድፍረት ይሰማኝ ነበር ። እንደ ሰው ቋንቋ ኖሮት ባያነጋግረኝም እንግባባ ነበር ። ዛዲያ እንዲህ ያለውን ጓደኛየን ፣ በንደዚያ ሁኔታ ቆስሎ ፤ አንጀቱ ወጥቶ ተዛፍ ስር አስተኝቼው ስጠፋ ሰው ቢሆን ምን ይለኝ? ፈጥሞ ሰላም አጣሁ ። በአእምሮዬ የሚመጣብኝ አውሬዎች ተሰብስበው ሲቧጩቁት ፤ አንጀቱን ሲጎትቱት ዋይ! ዋይ! እያለ ሲጮህ ፣ የኔ አንጀት እንደ ተጎተተ ሁሉ እንስፈሰፍ ዠመር ። እንዲሁ ስወድቅ ስነሳ አነጋሁ ።

“ጧት የውሻዬን ሁኔታ ቁርጡን ለማወቅ ወዲያውም እናቴን አጋም ውሃ ወርጂ ለማጥና ናት ስነሳ አከስቴ አንቃ ያዘችኝ ።

‘እስቲ እረጋ በል ነገሩ ይብረድ ፤ መች አጣ ሁትና ውሻ ፍለጋ ጫካ ለጫካ ልትል ነው’ በማ ሳት ማቁን፣ አወረደችብኝ ። የዚያን እለት ሳይሆ ንልኝ ቀረ ።

“በማግስቱ ከእናቴ ዘንዳ አንድ መላክተኛ መጣ ። ባለ ደሞቼ እናቱን ሲል ይመጣል ቢማለት

ተዚያ አካባቢ እንደሚጠብቁኝ በመታወቁ፡ ወደ ዚያ እንዳትሰደኝ ላክስቱም ጭምር አደራ በማለቷ ወደዚያ የመሄዱ ነገር አከተመ ። የውሻዬን ነገር በሆዴ ቻልሁት ።”

# ዘ ጠ ኝ

“የውሻዬ ነገር ሆድ ሆዴን እየበላው ያለ ወፍና ያለ ገነት በስተቀር ማንም ሰው ሳያየኝ ፥ ሌት ወጥቼ ሌት እየገባሁ ታከስቴ ጋር ተቀመ ጥሁ ። ተገነት ጋር መቀራረባችን እየጠበቀ መጣ ። አክስቴም እሷ ስትመጣ ፥ ተጫወቱ ትለንና ቤቱን ለኛ ብቻ ለቃልን ወደ መንደር ትሄዳለች ። መቼም ተሌላው ተሌላው ነገር አይበልጥምና አለማዊውን ሳነሳ እንዳትታዘበኝ ፥ ኑዛዜ ነው” አሉኝ ፥ ትንሽ ፈገግ ብለው ።

“እየውልህ ፤ ገነት ተፊት ለፊቴ ትቀመጥና ሳቅ እያለች ስታጫውተኝ መንፈሴ ሁሉ ይሸበር ላት ነበር ። ጥርሶቿን ስትገልጣቸው ያስደንግጉ ነበሯቸው ። ምን ጊዜም ቢሆን ባይኖቿ ሞልታ አታይም ። ሰረቅ አድርጋ ነው ፤ አስተያየቷ ጌጥኛ ነበረው ። ሌላው መልኳ እንግዳው ተሰው አይበ ልጥም ። አይኖቿና ጥርሶቿ ግን ለየ ነበሯቸው ። የጠይም ደማም ነበረች ። ውሻዬ ትዝ ሲለኝ የም ይዘውን የምጨብጠውን አጣና ብረር ብረር ይለ ኛል ። ገነት መጥታ ስታነጋግረኝ ሁሉንም እረሳና ስለሷ ብቻ አስባለሁ ። ነግቶ እስከማገኛት ነበር የምቸኩለው ። አንድ ቀን እንደ ሁልጊዜው ጓዳ ውስጥ ተቀምጠን ስንጫወት :—

'ማሟ ነው ተባሊሽ ዘንዳ የምትሄጅው?'ስል ጠየቅኋት ።

'የምን ባል? ፈትቸዋለሁኮ' አለችኝ ።

'ለምን ፈታሽው?'አልኋት ፡ ልደብቀው የማ ልችለው ደስታ በፊቴ ላይ እየታየ ።

'አልፈልገውም !እናቱ ጨቅጫቃ ናቸው ።'

'በናቱ ምክንያት ትንጂ እሱን ትወጅው ነበር?'

'ተሱ ጋር እንኳን ጠብ የለንም ። እናቱ ግን አይጣልብህ' አለች ፡ እንደ ማንገሽገሽ እያደረጋት ።

"ወንድሜ የሞተው የሰው ሚስት በመድፈሩ ምክንያት ስለ ሆነ ምን ብጎመዥላት ያ ነገር ስለ ሚያስፈራኝ ብዙ ጊዜ ስትዳራኝ እሽሽ ነበር ። የዚያን እለት ግን ተባኗ ለጭራሹ መፋታቷን ስት ነግረኝ ስጋቴ ሁሉ ለቀቀኝና ወደሷ ጠጋ ብዬ ክን ዴን ተትከሸዋ ላይ ጣል አደረግሁት ። ጠጋ ብላ ተቀመጠች ። ተዚያ በፊት ገላ ለገላ ተነካክተን ስለማናውቅ ለመተያየት እየተፋፈረን ትንፋሻችን ይፈጥን ነበር ። እኔማ ጭራሽ ልቤ ትር ትር እያለ ሰውነቴ ሁሉ ተንቀጠቀጠ ።

'ምነው ?' አለችኝ ።

'ምነው ?' አልኋት ፡ መልሼ ።

'ሰውነትህ ይንቀጠቀጣል ።'

'በረ...ደኝ ...መሰል' አልኳት ፣ አነጋገሬ ሁሉ ድንቅፍቅፍ እያለ ። አሁን እንደዚያ ያለ መልስ የሰጠኋት ለምን ይሆን ? ጠራራ ጠሀይ ነው ። አሷም ነገሬ ገብቷታል ።

'ተበረደህማ ላሟሙቅህ' ብላ እቅፍ አደረገ ችኝ ። ሰውነቷ ዛል ብሎ ተከንዴ ላይ ወከክ አለች። ተዚህ በኋላ ሃፍረት የሚባል ነገር አልሞከረንም። በእንዲህ ሁኔታ ፍቅራችን ጠና ።

"የኋላ ኋላ ውል አይረሳምና ያባቴን ደና ለመመለስ ተዘጋጀሁ ። ማታ ተገነት ጋር ተዚያ ችው ጓዳ ውስጥ ተሳስመን ተለያየን ። መቼም ያቺ ጓዳ የምትረሳ አይደለችም ፣ ሚጉላችን ነበረች ።

"ወገግ ሲል ጉዞ ዠመርሁ ። ጉዳይ ተቱባለው ቦታ ስደርስ ነጪ ዠንጀሮ አገኘሁ ። እሱም ጠላቴ ነው ፣ ውሻዬን ባይነክሱት ኖሮ ተኔ አይለይም ነበር ። አንድ ግመሬና አንዲት እመጫት ዠንጀሮ ተነባብረው ሲቃመሱ አየሁ ። ባንድ ጥይት ሁለ ቱንም ለማስቀረት ስተኩስ ያሰብሁት አልሆነም ። ግመሬው አመለጠኝ ። ተዚህ በኋላ አንዱ ባንዱ ላይ እየተነባበረ ይንጫጫ ዠመር ። እየሮጠሁ ተመታኋት ዠንጀሮ ስደርስ ትንፍስ ትንፍስ ትላ ለች ። ቡጫሌዋን (ግልገሏን) ዠንጀሮ ለማስለቀቅ ብሞክር ተላይዋላይ እንደ መዥገር ተጣብቃ እቃ ተችኝ ። ተናደድሁና ተዚያው ላይ በድንጋይ ቀጥ ቅጪ ገደልኳት ። የመዠመሪያውን የጭካኔ አገዳ ደል በዚያች የዠንጀሮ ቡጫሌ ዠመርሁ ።

“ሆዶ እናቴ ተመሄዶ በፊት ውሻዬ ወደ ቀረ በት ጫካ ነው የሄድሁት ። ምኞቴ ብዙ ነው ። ምነው ድኖ ባገኘሁት ። ሰው እንኳን የቆሰለ እን ደሆን ፣ ‘የውሻ ቁስል ያድርግልህ’ ይባላል ። በነጠ ላዬ አንጀቱን ወደ ሆዱ መልሼ አስሬለት ነበር ። ቁስሉ ጠግጎ ሊድንለት ይችላል ። መቼም ተዳነ ተዚያ ጫካ ውስጥ ብቻውን አይቀመጥ ። እንደ ምንም እንኳቶ ወደ መንደር ሳይሄድ አይቀርም ። ግና ቤቱ ተቃጥሎ ፤ ባዶ ባድማ ሲያገኝ የት ይደ ርሳል? ተጎረቤት የጌታ ያድር ይሆን? ወይንስ ባዶ ባድማ እንቆ እርሃብ ይገለው ይሆን? እኔስ ተጫ ካው ያጣሁት እንደሆን ወደ የት ነው የምፈልገው? ይህን እያሰብሁ ፣ ጫካውን ፣ ጉድባውን እያቆራረ ጥሁ ደረስሁ ። ግና የተመኘሁት ሁሉ ከንቱ ሆነ።

“እየውልህ ፤ ኮስትርን ሞቶ አገኘሁት ። ተጭ ንቅላቱ ዝምሮ የገዘርባው አጥንት አልተላቀቀም። አይኖቹ ወልቀው ፣ ጥርሶቹ ገጠው ሳያቸው አሳ ዘነኝ ። መቼም ልማድ ሆኖ የሚወዱት ውሻ ፣ ወይ ንም ሌላ እንስሳም ቢሆን ሲሞት ተማዘን በስተ ቀር አይለቀስም ። እኔም ያ ልማድ አስሮኝ ለኮስ ትር ጠብታ እንባ ሳይወጣኝ ቀረ ። አጥንቱን ለቃ ቅሜ በወገብ ካራዬ ቆፋፍሬ ቀበርሁት ። ይህንን በማድረጌ የሀሊና እረፍት አገኘሁ ።

“የውሻዬን ቁርጥ ታወቅሁ በኋላ ወደ እናቴ አጋም ውሃ ወረድሁ ። እህቷ ብትሆንም ቅሉ መከራ ተሸክሞ ተሰው ቤት ሀዘኑ ከሁሉም የከፋ

ነው። እናቴን ክፉኛ ጉስቁልቁል ብላ አገኘኋት ፥ እኔን ስታይ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

“እናቴን ለሶስት ቀናት ያህል ካነጋገርኳት

በኋላ ወደ መስቀች አቀናሁ። ያባቴን መቃብር ለማዬት አስቤ ሳለ ቀን ሰው ሊያየኝ ሆነ። ሌሊት ደሞ መቃብር ጠባቂ ሰይጣን ፈራሁ። ቀን ይብ ቀልለት ብዬ ተወሁት።

“ጫካ ውስጥ አድፍጬ ዋለሁና ማታ ታብ ልጃችን ቤት ገባሁ። ያባቴን ደም ለመመለስ የመጣሁ መሆኔን ስነግረው ፤—

‘በዋዛ የምታገኛቸው አይደሉም። ተአፍጥ ባቸው ሄደው ተቀላቅለዋል’ አለኝ።

‘ግዴለም ፥ እነሱ ቢቀላቀሉ አባትየውን እገ ለዋለሁ!’ አልሁት።

‘ሽማግሌ ሰው ገለህ እርባና የለውም ይቅር ብህ’ በማለት መከረኝ።

‘የኔ አባት የጠጣ ወይንስ የዝንጀር ሽማግሌ ሆኖ ነው የገደሉት? እንዳውም አባትየውን ነው የምገለው’ ብዬ ቈረጥሁ። በማግስቱ ጫካ ዋለ ሁና ጭልምልም ሲል ወደ አቶ ፈንቴ መንገሻ ቤት አመራሁ። ውሾቹ ገና ተሩቅ ጠመዱኝ። ቤቷ ውሻማ ባቴን ዘርፋው ነበር። እንደማይሆን ሳውቀው ተመለስሁ። በሚቀጥለው ቀንም እንዲሁ ውሾቹ እላስጠጋኝ አሉ። እሱም ተማምኖ የተቀ

መጠው በውሾቹ ነው ። እነሱ ሲጮሁ እሱ በታ ውን ይይዛል ። የውሻን ጥቅም ሳውቀው ለማስነ ቃት ታልሆነ በስተቀር አይገኘኝም ።

"ታበልጃችን ቤት ወጣ ገባ እያልሁ ስጠባ በቅ አንድ ቀን ምሽት የበልግ ዝናብ ዘነበ ። ጫን ያለ ዝናብ ነበር ። ውሾች ዝናብ ሲሆን ጥግ ፈልገው ቁልጥም ብለው ነው የሚተኙት ። ግፋ ቢል ተተኙበት ሁነው ቡፍ ቡፍ ነው የሚሉት ። ጥሩ አጋጣሚ ነበር ። በዋናው በር መግባቱን ተውሁና በጓሮ በኩል አጥር ቀድጄ ገባሁ ። እንደ እባብ እየተሳብሁ ጭል ጭል እያለኝ በምቹንደው እሳት አንድ አይኔን ጨፍኜ ስመለከት ተላይ በኩል እግሮቹን አንፈራጦ ተቀምጧል ። ምላጭ ስስብ ሆድ እቃውን ዘረገፍሁት ፤ የኮስትር ጌታ! ብዬ ፎከርሁ ። ስፎክር በውሻዬ ፤ በኮስትር ነው ። የኔን አባት እሳት እንደበላው ሁሉ የነሱንም አባት ትምድጃው ዳር ነው የደፋሁት ። ተቤቱም እሳት ለቀቅሁበት ። የቤቱ ቃጠሎ ፈገግን ብዙ አገር ሸኘኝ ። ወደ አጋም ውሃ ወርጄ የናቴን የእህቷን ባል እንዳይገድሉት ጥንቃቄ እንዲያደርግ ነግሬው ወደ አዲስ አንባ ዘለቅሁ ።

"ቁልፍ አምባ እተባለው ቦታ ስደርስ ተሰ ፋጣ የመጣ የጨው ነጋዴ እየተግተለተለ ሲሄድ ደረስሁ ። ብዛታቸው አስር ናቸው ። ቀድሜ ቦታ ያዝሁና ለጥይት መግዣ ገንዘብ እንዲሰጡኝ ጠየ ቅኋቸው ። ዘጠኙ እያመሙ ሲሰጡኝ አንዱ እንቢ

ብሎ ጀረጀረ ። ለካስ ቦንቧ ዴቦ ኖሯል ። ሲያበላ ሸኝ ነበር ፤ ቀደመሁት ።

“እየውልህ ፤ የዚያን እለት የዘረፈሁት ገንዘብ አስራ አምስት ጠገራ ብርና ሃያ ነጭ ሽልንግ ነበር ። ተዚህ በኋላ የሰው ገንዘብ እንደ ማር ይጥመኝ ገሠመር ። ማታ ላከስቴ ሁለት ጠገራ ብርና አምስት ነጭ ሽልንግ ሰጠኋት ።

‘ህእ… እህንጊዜ ተሰው ላይ ቀምተህ ነው የሚሆን ። እኔ ነግሬሃለሁ ፤ እራበህም ጠማህም እኔኑ አስቸግር እንጂ ተሰው ንክች ብለህ ትደርስና አደራህን ልጄ !’ ስትል አስጠነቀቀችኝ ። አንገቴን ደፍቼ አዳመጥኋት እንጂ መልስ አልሰጠኋትም ። መምጣቴን ለገነት ነግራት ኖሮ መጣች ። እስከ ማገኛት ድረስ ቸኩዬ ነበር ። አደሡ ሞቅ ያለ ቀቤ ተቀብታለች ። እቅፍ አድርጌ እያገላበጠሁ ሳመኋት ። እሷም ሳመችኝ ። ተዚያው ጓዳ ውስጥ ተቀምጠን ስንጫወት አከስቴ ፤‘እግዚኦ ! እግዚኦ!’ እያለች ወደኛ መጣች ። ‘ሰቆጣ ጨው ለማምጣት የሄዱ ነጋዴዎች ነበሩ ። አንዱን ተመንገድ ሽፍታ ገደለው አሉ ። እሬሳው አሁን ዘለቀ’ አለችን።

‘የኔም አጎት ፤ የናቴ ትንሽ ወንድም ተባርዝባ አብሮ ሄዶ ነበር’ አለች ፤ ገነት በድንጋጤ ተተቀመጠችበት ፡ እየተነሳች ። እኔም ክው ብዬ ደነገጥሁ ። አከስቴና ገነት እየተጣደፉ ተቤት ወጥተው ሄዱ ። ተውጪ ሰው ይንጫጫል ። እራቅ ብሎ

ደሞ ጡርንባ ሲነፋ ይሰማኛል ። ሆዱን ባርባር አለኝ ። አክስቴ እየሮጠች መጣችና ፣ ‹‹ አንተነህ አይደል ነጋደውን የገደልከው ?›› ስትል በጭንቀት ጠየቀችኝ ።

'አይ ፣ አይደለሁም ! አይደለሁም !' አልኳት ፣ እራሴን እየነቀነቅሁ ።

'አረሱስ አንተነህ ፣ መች አጣሁትና' ጭንቅ ፣ ጥብብ ፣ ብክንክን እያለች ስትመለስ ተከተልኳት ።

'ተዚያው ሆን እንጂ ያ.ሞ !' ስትል ከፋኝ አመናጨቀችኝ ።

'መያዙኮ ነው ፣ ላምልጥ እንጂ ።

'ድርስ መች አጣሁትና... እንግዳውማ ያን ብርና ሽልንግ ተዩት አገኘኸው ! በል አሁን ሹል ክና ሂድልኝ !' አለችኝ ። ተቧ ተንጥቁ ቁልቁል ስዳቱ ጨለማው ላይን ያዝ አድርጓል ። ወደየት እንደምሄድ ግራ ግብት አለኝ ። ተዚያ ባለደሞቹ እንደሚጠብቁኝ ባውቅም ሌላ መሄጃ የለኝም ። እናቴ ወዳለችበት እጋም ወሃ ነበር ። ብቻዩን በጨለማ ጉዞ ፣ ያውም ነፍስ ገሎ አይጣል ፣ አይድረስ ነው ። በየሄድሁበት ጥቁር ደም ተቃባሁ ። በሩቁ ቆብ እየደጋገመ ሲጮህ ይሰማኛል ። ጨለማውም ጥቅጥቅ እያለ ሄደ ። እንቅፋት ተወጋሁ ወዲህ ያላ ጋኛል ። ነፋስ በሹር ግንደ ያፏጫል ። ይሁ ሁሉ እንዳኛው የገደለሁት ነጋደ የነነት እንት እንዳይ ሆን ነው የፈራሁት ።››

# አ ስ ር

“እየውልህ ፤ አጋም ውሃ ተናቴ ጋር ስቀመጥ የገነት ነገር ሆድ ሆዴን ይበላኝ ዠመር ። ግና ምን አደርጋታለሁ ፤ የተበጠሰ ክር ነው ። ዳግመኛ ወደዚያ እንዴት ብዬ እሄዳለሁ ። ያን ነጋዴ የገደልሁበትን ቀን እረገምሁ ። ቀን ተቀምጬ ፥ ሌሊት ተኝቼ የማስበው ስለሷው ነው ። ስረቅ አድርጋ ስታየኝ ጥርሶቿ የሚገለጡት ፤ ስታጫውተኝ ቆይታ የምትሄደው ሁሉ ይመጣብኝ ዠመር ። ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ደስታ ሰጥታኝ ነበር ። የቧው ነገር እያብከነከነኝ ሳለ ባለ ደሞቹ ደሞ እንደሚፈልጉኝ ተነገረኝ ። የምሄድበት ቅጣንባሩ ጠፋኝ ።

“ያባቴ ወዳጅ የሆኑ አቶ ሞገስ ማሩ የሚባሉ ጠሜ ሚካኤል ነበሩ ። ልጃቸው አስታጥቄ ሞገስ ነፍስ ገሎ ዞጋ ተገባ ቆይቷል ። ባፍላው እንደ ገደለ ተኛ ዘንድ ወደ መንፈቅ ተቀምጦ ነበር ። አባቱ ሊወስዱት የመጡ ጊዜ ፥ ‘ተበጃ ልጅችህ ነፍስ ገለው ብድሩን ለመመለስ ያብቃኝ አልልሀም ። ይህ እርግማን ነው ። መቼም ባገራችን እንደ ጥቁር ደም የሚያስፈራ ነገር የለም ። ይህን ባትሲጋ ልጅን ክውን አድርገህ ይዘህ ተሞት አዳነህልኝ ። የልጅን ነገር አውቀዋለሁና ልጅችህን መጥፎ ነገር አይንካብህ!’ ብለው አባቴን የመረ

ቁት ትገ! አለኝ ። ለናቴ ስነግራት እሷ ጭምር ወደዚያ እንድሄድ መከረችኝ ።

“የመከራ ቆራጣ የቀራትን እናቴን ተሰናብ ቻት ወደ አባባ ሞገስ ጠሜ ሚካኤል ሄደሁ ። የዚያን ጊዜ የተናገሩትን ቃል ዘንግተው አላስጠ ጋህም ይሉኝ ይሆን፤ ወይንስ ደስ ብሏቸው ይቀበ ሉኝ፤ እያለሁ መድረስ አይቀርም ደረስሁ ።

“እንደ ስጋቴ ሳይሆን አባባ ሞገስ እንባ አውጥተው በማልቀስ ተቀበሉኝ ። ‘አባትህ ትናንት ፈርሶ እኔ ቁሜ እየሄድሁ መጠጊያ ታጣለህ!’ በማለት አዘኑ ፤ የደረሰብኝን መንከራተት ስነግ ራቸው ፣ ‘ዛሬም እንኳን መጣህ ። እንዳው ግን የክርስቶስ ነገር ይገርማል ። አባትህ የዋለልኝን ውለታ በበጎ ነገር እንድመልሰው እንጂ እንደ መጥፎ አድራጊ ቂናውን በቂና አልነበረም’ ሲሉ በብርቱ አዘኑ ።

“እየውልህ ፤ ታባባ ሞገስ ጥቂት ቀኖች ተተ ቀመጠሁ በኋላ ለጠጥታውም ለማንኛውም ነገር ልጃቸው ፣ አስታጥቂ ሞገስ ያለበት ስለሚሻል ወደሱ ይዘውኝ ሄዱ ። ቤቱ የተሰራችው ዞጋ ተወ ንዙ ዳር ሲሆን ባቅራቢያው ሌላ መንደር የለም ። እራቅ ብለው ወንዙን በመከተል ጥቂት መንደ ሮች ይታያሉ ። አብዛኞቹ ነፍስ ገለው ምህረት ተደርጎላቸው ለመንግስት እየገበሩ ፣ ተባለ ደሞቻ ቸው ሸሽተው ያሉ ናቸው ። አስታጥቂ ሞገስም እንዲሁ ምህረት ተደርጎለት ለመንግስት እየገ በረ ተባለ ደሞቹ ሸሽቶ ነው ተዚያ የሄደው ።

“የወንዙን ውሃ ጠልፎ በመስኖ ያለማው ሰንኮር አገዳ ፣ ቀይና ነጭ ሽንኩርት ፣ ቃሪያና ዱባው ሌሊኛ ነው ። ተጨዉ በስተቀር የሌለ ቅመማ ቅመም የለም ። የወንዙ ዳር ለዳር ተላይ እስከ ታች በልምላሜ የከበረ ነው ። በቤቱ ጥግ ለጥግም አራት ያህል ቀፎዎች አሉ ። ንቦች ሲያ ተመትሙ ይሰማሉ ። ጠብደል ጠብደል ሁለት ውሾችም አሉት ። በተረፈ ሌላ የንሰሳ ዘሰር የለም ።

“ሚስቱ ቅላቷ የሰም እንጎቻ ትመስላለች ። የሰውነቷ ልስላሴ ቢነኳት የምትፈርጥ አይነት ነው ። ጥርሶቿ ዘርዘር ብለው ፈገግታ አይለያቸ ውም ። እሷን ሳይ ልቤ ወደ ገነት ኮበለለ ። አስ ታጥቄ ሞገስ ደሞ አጠር ብሎ ጠየም ያለ ነው ። በድሜም ተኔ ጠና ይላል ። ጠመንጃው አጭር አልቤን ናት ። በምንሽሬ ይቀና ይሆን? የሚል ስጋት አደረብኝ ። አባባ ሞገስ ሁለት ቀን ውለው አድረው ተመካከሩን በኋላ ወዳገራቸው ተመለሱ ።

“አስታጥቄና እኔ ተግባብተን ስምና ወርቅ ለመሆን በቃን ። እንደ ስጋቴም በምንሽሬ ሳይቀና ቀረ ። እሱ አሲቃ ሆነ ። ሚስቱ ብዙነሽም እኔን ለማስደሰት የማታደርገው ነገር የለም ። እኔ ግን ሌትና ቀን የማስበው ስለ ገነት ነው ። በጎኑ ያልተኛ የቁም በሽተኛ ሆንሁኝ ። አስታጥቄ ሞገስ ቀሽንት ሲነፋ መሰል የለውም ። እሱ መንፋት ሲዝምር ልቤ ዳንኪራ ይጠታል ። እንደ ፉጭ ትም ፣ እንደ እንጉርጉሮም ይሞካከረኛል ። አንዳ ንድ ጊዜም ሳላስበው ቁጣ ቁጣ ይለኛል ። ይህን

እግርና እጅ ያጣ ባህሪየን ያውና ባባቴና በወን ድሜ ሞት ሆድ የባሰኝ እየመሰላቸው ፥'እባክህ እነሱን እርሳቸው ። አንተ አዘንህና ተመልሰው አይመጡ' ይሉኛል ። የሚበላ ፥ የሚጠጣ ተርፎ የፍቅር እርሃብተኛ ፥ የፍቅር ጥማተኛ ሆንሁኝ ። ይህን ነገር ሳስታጥቄም ሆነ ለብዙነሽ አላጫወ ትኳቸውም ። አንድ ቀን ተምሳ ላይ እንጀራው አልበላኝ ብሎ ባፌ ሲንከራተት ባልና ሚስቱ አዩኝና ተጠቃቀሱብኝ ።

'መሀሪ ፥ አንተን በማግኘታችን በጣም ደስ ብሎን ነበር ። ዛዲያ በደስታችን መሀከል አንገትህን ስትደፋ እኛ እናዝናለን ። በፊት ባባት ህና በወንድምህ ሞት ምክንያት መስሎን ነበር ። አሁን ግን ሌላ ሆኖ ነው ያገኘነው ። የለም ተኛ የደበ ቀኸን ምስጢር አለህ ። መቼም ቢሆን አብረን እስከኖረን ድረስ ክፉውንም ፥ ደጉንም አብረን መካፈል አለብን ። እናም የምታስብበትን ንገረንና እንወቀው ። እረ ነገሬን ለናንተ አላላውቅም የም ትል ተሆነም አብሮ መኖሩም አያስፈልግ' ሲል አስታጥቄ በቀየሚታ ተናገረ ።

'እኔም አስቀይሜህ ተሆነ ተናገር!' አለች ፥ ብዙነሽም ፥ መቼም ጥርሶቿ አይገጣሙ ሳቅ ብላ ።

'አንች ምን ብለሽ ታስቀይሚኛለሽ?'

'እንጃ! ዛዲያ ለምን ነው የብቻህ የምታስ ቀው? እንጉርጉሮህ ሁሉ የፍቅር አይሉት የሀዘን ቅጣንባሩ የጠፋ ነው ።'

'ኢላውቅበት ብዬ ይሆናል እንጂ ነገሩስ የፍቅር ነበር' አልኳቸው ፤ በፈገግታ አንገቴን እየ ደፋሁ ።

'ቀልዱን ተወውና ቁም ነገሩን ንገረን' አለ ፤ አስታጥቄ ግንባሩን እንደ ቋጠረ ።

'እረ ቀልድ አይደለም ፤ ታንዝቴ ነው' አል ሁና እንድም ሳላስቀር ዝርዝር አድርጌ ነገርኳ ቸው ።

'ይህ ነው የብቻህ ሲያሳስብህ የነበረው? ብስል ስትመስለኝ ለካስ ሞኝ ኖረሃል ። እስከዛሬ ነግረኸኝ ቢሆን ኖሮ ተጅህ ገብታ ነበር ። አሁ ንማ አግብታ ይሆናል ። መቼም እስካሁን ቦዝና የምትቀመጥ አይመስለኝም?' ሲል የባሰ ጭንቀት ለቀቀብኝ ። ቀጠል አድርጎም ፤ 'ብቻ አንተና እሷ ጥኑ ፍቅር ታላችሁና የገደልኸው ነጋዴ አጎቷ ታልሆነ ባል ብታገባም እናገኛታለን' አለኝ ።

'እሷና እኔስ ጥኑ ፍቅር ነበረን' አልሁት በመ ተከዝ ።

'እንግዳው ተሰምኑ ጎጆ ቀልስን እናመጣታ ለን ። አንድ ብለህ እንዳታስብ' አለኝ ። ተዚህ በኋላ እንደ ምንም ተጣድፈን አንዲት ጎጆ ሰራን ። ተዚያም የት እንዳለች አረጋግጠው ለመ መለስ በቅድሚያ እኔ ሄደሁ ። ”

# አስራ አንድ

“መቼም ቢሆን ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ ነውና በመንገድ ስሄድ የምመኘው የገደልሁት ነጋዴ የገነት አኅት እንዳይሆንና ባል ሳታገባ እንዳገኛት ነበር ። እንዲህ እንዲህ ያለው አሳብ እያንገላታኝ ከብቶች ሲገባቡ አዲስ አንባ ገባሁ ። አክስቴ ተሰማይ የወረደሁ ነው የመሰላት ። አገ ላብጣ ተሳመችኝ በኋላ ተመቀመጤ እየተጣደፈች እንጀራ አቀረበችልኝ ።

‘ለመሆኑ እልም ብለህ የጠፋኸው ለምን ነው?’ ስትል ጠየቀችኝ ።

‘በዚያ ነጋዴ ሞት ምክንያት ተደናግጬ ወደዚህ መምጣቱን ፈራሁ’ አልኋት ።

‘የገነት አኅት መስሎህ ነው? አይደለም ። ወደ ላይ ወደ ደጋው ሆኖ ነው የተገኘው ። እንዳው ግን ልጀ ለገንዘብ ብለህ ነፍስ ታጠፋ? ያውም አልሮ ሃጂ መንገደኛ ። የራስህን ደም መቼ ተወጣኸውና ። ያለፈውማ አልፏል እስቲ ለወደፊቱ አደብ ግዛ’ በማለት ወረደችብኝ ።

“ብቻ የገነት አኅት አለመሆኑን ስትነግረኝ ውስጡን ደስታ ፈንቅሎኛል ።

‘ለመሆኑ ገነት አለች?’ ስል ጠየቀኋት ።

'ገንትማ. . .' ብላ ለመናገር ያሰበችውን መልሳ ያዝ እደረገችው ። ተዚህ ላይ አንድ ነገር እንዳለ ተረዳሁ ። ፊቴ ቅጭም አለ ።

'ምን ታደርግልሃለች?' ስትል ትኩር ብላ እያየችኝ ጠየቀችኝ ።

'ማድረግማ ምን ታደርግልኛለች ። እንዳው ግን ጥሩ ልጅ ነበረች ፤ እንዴነሽ ብላት ።'

'እም... እንዴነሽ ልትላት' አለችኝ ፤ እራሷን በመገረም አይነት እየነቀነቀች ። ቀጠል አድርጋ ፤ 'እሷማ ባል አግብታለች' ስትለኝ ፤ ጭንቅላቴን በዱላ የተመታሁ ያህል ተሰማኝ ። ምንም ትንፍስ ሳልል አንገቴን ደፍቼ ቆየሁ ።

'ለሷ ነው አንገትህን የደፋኸው? በል አርፈህ ተቀመጥ ። የዚያን ጊዜምኮ የፈቀድሁት ልሂድ ልሂድ እያለህ ልብህ ስለ ተሰቀለ እንድትቆይ ብዬ እንጂ የማላውቅ እንዳይመስልህ ። ገንትን ታንጀትህ አውጣት ። ወንድምህ በምን እንደ ሞተ አጣኸውና ነው' በማለት ተቆጣችኝ ።

'ወንድሜ የሞተው የሰው ሚስት በመድፈሩ ነው ። እኔ ግን የሰው ሚስት አልደፈርሁም ፤ ገንት ባሏን ፊታ የተቀመጠች ናት ። እሷንም ቢሆን ላገባት እንጂ ለማባለግ አይደለም' አልኳት ፤ አንገቴን ደፋ አድርጌ ።

'በሞትሁት! ገንትን አግብተህ ትዳር ልትይዝ ነው?' በማለት በመገረም አገጭዋን ያዘች ።

'ለምን ነው እሷን አግብቸ ትዳር የማልይዘው፣ እሳምሬ እይዛለሁ እንጂ ።'

'የት ሁነህ ነው ትዳር የምትይዘው፣ ተዚህ ተኔ ጓዳ ውስጥ ነው፣ ወይንስ ታባትህ ባድማ ላይ፣ በደም የተነከረህ መሆንህን እረሳኸው ፣ ወይንስ ታወርህ ልበል፣ በመገናኛ መሪያ ነገር አቻህ አይደለችም ። እሷ የጌታ ልጅ ናት ። እንዳው የሚ ሆንስ ቢሆን አባቷ በጅ የሚሉ ይመስልሃል፣ ማን ተሰው ደም ይዘፈቃል '።

'የጌታ ልጅ ናት ላልሽው እኔና እሷ ተተፈ ቃቀደን የናትና ያባቷ ጌትነት እንዳው ነው ። እኛም ቢሆን ሰርተን እናገኛለን ። የት ይዘሀት ትኖራለህ ላልሽኝም ዞጋ ተገባሁ ማን ይነካኛል።'

'ሆይ ጉድ! ዞጋስ ቢሆን የመንግስት አገር መስሎኝ፣ ተዚያ ዳኛ የለም ያለህ ማነው፣ ያስ ባይሆን ባለ ደሞችህ ያስቀምጡሃል፣ አሁንማ ምን አጨቃጨቀን ፤ አግብታለች ።'

'ወደየት ነው ያገባችው፣'

'እንጃ! የት እንዳገባች አገሩን አላውቀውም' ስትል ድፍን ያለ መልስ ሰጠችኝ ። ተዚህ በኋላ የምታወራኝ ወሬ ሁሉ አልጥመኝ አለ ። ተዚያው ጓዳ ውስጥ አንጣጥፉልኝ ስትኛ ታጠገቤ ቆም ብላ ፥ 'እንግዲህ ነገውኑ ትመለስህ መሄድ አለ ብህ ። መዋል ማደር የለብህም ። የገደልኸው ነጋዴ ዘመዶችም እያጠያየቁ ስለሆነ ዳግመኛ ወደዚህ

እንዳትመጣ ። እንኳን መዋደቂያህን አወቀሁት እንጂ ናፍቆትስ አይገድለኝም’ አለችኝ ።

‘ነገ፣ እንኳን ውዬ ሳላነጋግርሽ?’ አለኋት ፤ የተጨበጠ ነገር ሳልይዝ መመለሱ ጨነቀኝና ።

‘የለም ይቅርብኝ ። ያንድ ቀን ማነጋገር አይ ጠቅመኝም ። ተኖረህ ብዙ ቀን የምንጫወትበት ወደ ፊት ይኖራል ። መቼም እንዲህ ብለን አን ቀር’ አለችኝ ። ተዚህ በኋላ እንቅልፍ የሚባል ነገር ባይኔ አልዞረም ። አንድ እልባት ሳልይዝ መመለሱ አሳሰበኝ ። ሌላ ሰው መጠየቅ አልችልም ። ብውል ባድር ግን አንድ ውጤት አገኝ ነበር ። ወይ እራሷ ሳታስበው ትነግረኛለች ። ስለዚህም ምን ምክንያት ፈጥሬ ልዋል ልደር? እያለሁ ስጨ ነቅ አንድ ነገር አሰብሁኝ ።

‘‘የግሬን አውራጣት እንቅፋት መቶኝ ነበር ። ቁስሉ እንኳን ይህን ያህል አልነበረም ። መግል መያዝ ስለ ዠመረ ትንሽ ይጠዘጥዘኛል ። እሱ ጥሩ ሰበብ እንደሚሆነኝ አመነሁ ። ወገግ ሲል ምግብ አዘጋጅታ ፣ ‘በል ተነሳ ጉረስና ሳይነጋ ሂድ’ አለችኝ ። ተወደ ራሴ ቀና አልሁና የግሬን አውራጣት ይገፎ አቃስት ዠመር ።

‘ምነው? እንቅፋት መቶህ ነበር?’ ብላ እጄን አስለቅቃ ለማየት አውራጣቴን ያዝ ስታደርገኝ

‘አረረረ . . .! ነካሽብኝ!’ ብዬ እግሬን መን ጭቂያት ተወራጨሁ ።

'ውይ! በሞተሁት! ልጄን ነካሁብህ?' ብላ ደነገጠች ። ትንሽ ተንፈራገጠሁና እውራጣቴን ጨብጬ በረዥሙ ተነፈስሁ ።

'ተንሰፈሰፍህ አይደል ፣ ልጄ ። ዛዲያ እንዴት ይሻላል?' አለች ፣ ጉዞው መሰናከሉ ነው ብላ ።

'እረ የሚያንቀሳቅሰኝ ነገር አይደለም ።'

'እንዲህ እየሆንህማ እንዴት አድርጌ እሰድ ሃለሁ ። የጣት ቁስል መጥፎ ነው ። ተቁስሉ ይልቅ ፍርንትቱ አይጣል ።'

'እንዱ የገደለኝ ፍርንትቱ አይደል ።'

'በሏ ስብ እለምንልህና ተኳኩሰህ በጨርቅ እስር ታደረገሽው ለነገው ምንም አይልህ' አለ ችኝ ። ተዚህ በኋላ ያቀረበችልኝን እንጀራ በትኩስ ሽሮዬ ልጬ ለጥ አለሁኝ ። አንዳንድ ጊዜ ወደ ጓዳ ብቅ ስትል አቃስታለሁ ።

"ተረፋዱ ላይ ፣ 'እስቲ ወደ መንደር ሄጄ ስብ ልፈልግልህ ። አደራህን ተሱ ቅስቅስ እንዳ ትል' ብላኝ ነጠላዋን ተከናንባ ወጣች ። ትንሽ ቆየሁና እንዳ ወጥቼ በበሩ ቀዳዳ አሾልቄ ወደነ ገነት ግቢ ስመለከት በዬት በኩል እንደ መጣች ሳላያት አክስቴ ከተፍ አለች ። ብሞት በወደድሁ።"

'እንዳትንቀሳቀስ ብየህ ለምን ነው የወጣሽው ? ተዚህ ተጠግተህ ምን ታያለህ?'

'እ... እ... እረ ደመነፍሴን ደንግጬ ነው የተነሳሁት' አልኋት ፣ እየተርበተበተሁ ።

'ምን አየህ ? ሰው መጣ እንዴ ?' አለችኝ ፡ ደንገጥ ብላ ።

'ቡናን ለመክፈት ሲታገል ጊዜ የምን ሰው ነው ብዬ ደንግጬ ቶሎ ስወጣ ወደል ውሻ ሆኖ አገኘሁት ።'

'በስማም! እኔስ ሰው አየህ ብዬ ነፍሴ የለም። ጥቁር ውሻ ነው ? በቀደም ሲጤን ደፍቶት ነበር እሱ ነው የሚሆን ?'

'አዎን ፡ ጥቁር ውሻ ነው ።'

'ቆይማ ጠብቄ ጭንቅላቱን ነውየምለው ። በል ግባና ተኳኩሰህ እስር አድርገው አለችኝ ። ድንገት በመጣልኝ መልስ እየተገረምሁ ገብቼ ተመቀመጤ የወይራ ጉማጅ ይዛ መጣች ። የጫ ፉን ፍም ሳየው መልካም እንጥረኛ ያጋለው ብረት ይመስላል ።

'በል እንካ ተኩሰው ፤ የፍየል ስብ ነው እን ክት ነው የሚያደርገው' ብላ ታጠገቤ በርከክ አለች ። በመዝመሪያ ስቡን ታውራጣቴ ደረጋደ ምሁና በፍሙ ስለው እየተንቻቻ ሲቀልጥ ሽታው ዓዳሙን አወደው ። ቁስሉ እንዳመመኝ ሁሉ ፤

"እሁ...! እ...!" እያልሁ ተቁነጠነጥሁ ።

'አይዞህ ቻል አድርገው! አሁን እንደዚህ ተኩሰህ እስር ያደረገኸው እንደ ሆነ ለዝቦልህ ይድርና ነገ ዘና ብለህ ትሄዳለህ ።'

'ሂጅ ተዚህ አይሽተትሽ! አልኋት፣ አፍጥጣ ስትቀመጥ ጊዜ ።

'በል ደህና አድርገህ ተኩሰው ። እውነትም ክርፋቱ እቴ!' ብላ ተጓዳ ወጣች ። ጎንበስ ብዬ አየኋትና መተኮሱን ትቼ ባመጣችልኝ ትልታይ ጨርቅ ግጥም አድርጌ አስሬ ጋደም አልሁ ፤ ትንሽ ዓይታ ተመልሳ መጣችና ፣ 'እንዬት ሆንህ? ተሻለህ?' አለችኝ ።

'ትንሽ ይሻለኛል ።'

'አሁን ነው የሚሻልህ ። የፍየል ሞራ ፍቱን አይደል' አለችኝ ። በንዲህ ሁኔታ ዋልሁ ፤ አመሸሁ ። የሴሊቱ ነገርም እንደ ምንም ይነጋል ። ተዚያስ በኋላ ? ሂድ ማለቷ የማይቀር ነው ። የመሄዱን ነገር ሳስብ አሞቴ ፍስስ ይላል ። ሊነጋጋ አቅራቢያ መወራጨትና ማቃሰት ጀመርሁ ። ሰምታኝ ኖሮ ቀሚሷን እየጎተተች መጣችና ፣ 'አመመህ እንዴ ፣ ልጄ ? እስቲ ቀስ በል ዛዲያ ውጪኮ ይሰማል' አለችኝ ፣ እንደ መስጋት ብላ ።

'ቢያመኝ እንጂ ወድጄን ነው!' በማለት እንደ መንጫነጭ አልሁ ።

'ዛዲያ ቻል አድርገው እንጂ ። መማል ሊይዝ እየሰበሰበ ነው ። በዚህ አይነት ዛሬም ላያስሄድህ ነው?'

'እንዴት አድርጎ ንቀሳቅሰኛል ።'

‘በል ዋል ብለህ ትተኩሰዋለህ ። አሁን ቻል አድርገው’ ብላኝ መለስ አለች ። ተዚህ በኋላ ትን ፍሽ አላለሁም ። ጧት እንደ ነገሩ ሞቅ ሞቅ አድ ርጌ አሰረሁት ። እኩለ ቀን ላይ ወሃ ልቅዳ ብላ ወንዝ ወረደች ። እንደ ልማዴ ተጓዳ ወጣሁና በበሩ ቀዳዳ እመለከት ገሮመር ። ምንም ነገር አልታየኝ ሲል ጊዜ ደሞ እንዳትይዘኝ ሰጋሁና መለስ ብዬ ወደ ጓዳዬ ሳመራ ፤ ‘እማማ ልኬ ! የሎም እንዴ?’ የሚል ድምጥ ሰማሁ ። ልቤ ተሁለት ተሰ ነጠቀች ። መለስ ብዬ ሳይ ገነት ናት ። ተቆም ሁበት በደስታ ፍርክስ አልሁ ። ተበሩ አጠገብ ደረሰ አለችና ፤ ‘የሎም መሰል ?’ ብላ ለመመለስ ስት ቃጣ :—

‘ገነት! ገነት!’ ስል ጠራኋት ፤ ወደ በሩ እየ ተጠጋሁ ።

‘ማነህ ?’ አለች ፤ ወደ ውስጥ እየተመለከተች

‘እኔነኝ ፤ መሀሪ ነኝ ።’

‘መሀሪ!’ አለች ፤ በመገረም ወደኔ ስትመጣ። በሩን ከፍታ ስትገባ ተቃቀፈን ። እየደጋገመን ፤ እየ ደጋገመን ተሳስመን ታበቃን በኋላ በሩን መለስ አድርገን ወደ ጓዳ ገባን ።

‘አንተ ለምን ነው እንዲህ እልም ብለህ የጠ ፋኸው ?’ አለችኝ ፤ እንደ ተቀመጥነ ።

‘ወደ ታች ወደ ቆላው አገር ስለ ራቀሁ ወደ ዚህ ለመምጣት አልተመቸኝም ።’

'ምነው እንደዚህ ከሳህ ዛዲያ ልጄ?' አለችኝ። 'ያንች ናፍቆት ነዋ!' አልኳት።

'ቀጣፊ! በናፍቅህ ነው እንደዚህ አልም ብለህ የጠፋኸው? ለመሆን መቼ ነው የመጣኸው'

'ትትናት ወዲያ።'

'አንተስ እውነትም ናፍቀሃል እቴ! ዛዲያ ለምን ነው ያላከህብኝ? እማማ ልኬስ ለምን ነው ያልነገሩኝ? ትናትም አግኝቻቸው ነበር' በማለት በቅሬታ ተናገረች።

'እረ እሷስ እንዳውም አግብታለች ነበር ያለችኝ። እውነት አግብተሻል?' ስል ጠየቅኋት።

'ዛዲያስ! ምላሽ ተመልሼ መምጣቴ መስሎኝ' አለችኝ፣ ሳቅ ብላ በዚያው ጌጥኛ እስተያየቷ እያየችኝ።

'እረ እውነት?'

'እውነትስ ተዚህ ቀደም አሳገባሁም። አጭ ታው ግን እናት አባቴን መቆሚያ መቀመጫ አሳ ጥቷቸዋል። እነሱም ባል እያማረጡ ናቸው። መቼም ለኔ የሚበጅ አይመጣ' አለችኝ፣ እንደ መተከዝ ብላ።

'እኔማ ቤት ሰርቼ ልወስድሽ ነበር የመጣሁት።'

'ዛዲያ አሁንስ ቢሆን ይዘኸኝ የማትሄድ። አየህ፣ እማማ ልኬ እንኳን አግብታለች ያሉህ

አንድ ቀን ምነው መሀሪ በመጣ ይዞኝ ይጠፋ ነበር፡ ስላለኳቸው ነው ። እኔ በፊትም ቢሆን አልበ ነበር’ አለችኝ ።

‘ዛሬያ መች ይገርሽ ልጥፋ?’ አልኳት ፥ ተተቀ መጠሁበት እያቁነጠነጠኝ ።

‘ለምን ዛሬ ማታ ይዘኸኝ አትጠፋም? ተኛ ቤት ወዲያ ታለው ግራር ዛፍ ብትጠብቀኝ እመ ጣለሁ ።’

‘በይ እንግዲህ ልብስ ምን አትበይ ። አሁን ቶሎ ሂጅ አክስቴ ሳትመጣ ።’

‘የምን ልብስ ፥ ነፍሴን ብቻ ይገፍ ነው የም መጣው’ ብላኝ ተንዳው ወጣ ስትል አክስቴ የውሃ እቃዋን እያንጎባለለች ከች ። እኔ ድምጿን ስሰማ ተጠቅልዬ ለጥ ።

‘እማማ ልኬ ለምን ነው የመሀሪን መምጣት ያልነገሩኝ?’ ስትል ገነት ቀድማ ተቆጣች ።

‘ወገኛ ! ወግ ጠራቂ! በይ አውርጅኝ ይልቅ!’ ስትል አክስቴ በፈንታዋ ተቆጣች ።

‘እውነት ተቀይሜዎታለሁ እማማ ልኬ’ አለች፥ የውሃ እቃዋን ታወረደቻት በኋላ ።

‘እረ ውጭልኝ እባክሽ እቴ! መጋጣ!’ በማ ለት ተቆጣቻት ። ገነት ወጥታ ተሄደች በኋላ ፥ ‘እብድ የሆነች ልጅ ! እስቲ የዘጋሁትን ቤት ከፍታ ትግባ! ሌላም ቢሆን ይኸው ነው’ ፥ እያለች ወደኔ

መጣች ። ተጠቅልዬ ዝም ስል ጊዜ ፣ 'ቀጣፊ! አሁን እንቅልፍ ወስዶህ ነው?' አለችኝ ።

'እረ እሰማለሁ' አልኳት ፣ የተሸፈንሁትን ጨርቅ ገለጥ እያደረገሁ ።

'ገንትን አገኘሃት አይደል? ነፍስህ ገባች!' አለችኝ ፣ አግብታለች ብላ ስለ ዋሸችኝ እንደ ማፈር ብላ ።

'አገኘኋት' አልኳት ፣ ደስ ያላለኝ መስዬ ችላ በማለት ።

'ምን ምን አወራችሁ?' ስትል ጠየቀችኝ ።

'ምንም አላወራን ። የኔን ደህንነት ጠየቀችኝ ፤ ደህና ነኝ አልኳት ። በቃ ይኸው ነው ።'

'ሌላ ምንም አላወራችሁ? እስቲ ሙች በለኝ!'

'ሙች! አሁን ተነገረሁሽ ሌላ አላወራንም' ብዬ ኮስተር አልሁኝ ።

'እኔ ነግሬሃለሁ! ተዚች ልጅ ዳግመኛ ዝር ትልና! ወንድምህ የሚነግሩትን ሰምቶ ቢሆን ኖሮ ይኸ ሁሉ ነገር አይደርስም ነበር' በማለት አስጠ ንቅቃኝ ተመለሰች ።

''ጠሀይዋ ልትጠልቅ ያለች መሆኗ ይታወቀኛል ። ቤቱ የምሽት ጥላ አርፎበታል ። አክስቴን ጠራሁና ፣ 'እንዳልሽው ይኸ የፍየል ሞራ ፍቱን መድሀኒት ነው ። እንክት አደረገው' አልኳት ።

'እየውልህ ፣ እየሰበሰበ ነው ፤ አሁን ይሻል ል አላልሁም' አለችኝ ፣ ደስ ብሏት ።

'ጨርቁን ልፍታው' ስላት ።

'ተወው ተዚያው እርትም ይበል ።'

'እንግዲህ ተተሻለኝ ዛሬ ማታ ልሂድ ። አን ችንም አስቸግረሁሽ ።'

'ትሄድ?'

'አዎን ፣ ተተሻለኝ ብሄድ ነው የሚሻለው ። እንዳልሽው መዋል ማደሩ ጥሩ አይደለም ።'

'ዛዲያ በሌሊት ብትሄድ አይሻልም? የማታ መንገድ ጥሩ አይደለም ።'

'ግዴለሽም ። ለኔ የሚሻለኝ የማታው መን ገድ ነው ። የሌሊቱ የሆነ እንደሆነ አጉል ቦታ ላይ ይነጋብኛል ። የማታው ግን ቢነጋም ተቆላው ላይ ሬሰሆነ ተቢያ በኋላ በቀዝቃዛ ገሰግሼ እደር ሳለሁ ። ወዲያውም ጨረታ አለች ።'

'በልበቲ' አለችኝ ፣ ትር እያላት ። ማታ ያቀረ በችልኝን እንጀራ ግጥም አድርጌ በልቼ በላዩ ሁለት ፈሌ የገብስ ጠላዬን ቻልሼ ፣ አከስቴን ተሰናብቼ ቹልክ አልሁኝ—ተገኑት ለመድረስ. . ."

# አ ስ ራ ሁ ለ ት

“እየውልህ ፤ እየገሰገስሁ ተግራሩ ዛፍ ስደርስ ምንም ነገር የለም ። የግራሩ ዛፍ ዘርፈፍ ብሎ በነፋስ እየተገፋ ወዲህ ወዝ ፡ ወዲያ ወዝ እያለ ያረግዳል ። ጉቶ መስዬ በመቀመጥ የገነትን መምጣት በጉጉት እጠባበቅ ጀመር ።

“ዙሪያውን ቀበሮ መንጫጫት ያዘ ። ገነት ዘገየች ። ሴት ልጅ ጨለም ካለ በኋላ ወደ ደጅ ለመውጣት ትፈራለች ። ፈርታ ይሆን? ወይንስ እኔ ዘግይቼ መጥታ አጥታኝ ተመልሳ? እያልሁ እጨነቅ ጀመር ። ተተቀመጥሁበት ተነሳሁና ወደም ትመጣበት በኩል እየተመለከትሁ ስንቆራጠጥ ተወደ ኋላዬ በግራሩ ጀርባ እህህ. . .የሚል ድምፅ ሰማሁ ። መለስ ስል እንጨት የተሸከመ ሰው ነው ። እንደ መደንገጥ አልሁና አይነምድር የምወጣ መስዬ ቶሎ ተቀመጥሁ ።

‘ማነህ?’ አለኝ ፤ ቆም ብሎ ።

‘እኔነኝ’ አልሁት ፤ ድምጤን ጎርነን አድርጌ ።

‘ማን እኔ?’ አለኝ ፤ መልሶ ።

“ተዚህ በኋላ መልስ አልሰጠሁትም ። ትንሽ ቆም ብሎ አየና አልፎ ሄደ ። ሰውየው ተሄደ

በኋላ ተነሳሁና ተወደ ወደህ እንጎራደድ ዠመር። የተበርሞ ሜሜታዎ አየጨመረ ሄደ ። በዚያው ልክ የመንደር ውሻው ጩኸት በርክቷል ። ትንሽ ቆይቶ ደሞ ዥብ መጮሁ የማይቀር ነው ። መቼም ዥብ እየጮኸ ደፍራ እንደማትወጣ የታወቀ ነገር ነው ። መሬት ጠበበችኝ ። ምንሽሬን ዘቅዝቄ አንግቼ ጮቤ ስረግጥ ተወደ ፊት ለፊቴ እየሮጠች ስትመጣ አየኋት ። ወደኔ አጠገብ ስትቃረብ እንዳትደነግጥ እህህ...የሚል ድምጥ አሰማኋት ። የስራ ልብሷን አለወጠችም ! እርጌ ነጠላ ብቻ ደረብ አድርጋለች ።

'ነፋሱ ገደለህ አይደል' አለችኝ ፤ ታጠገቤ ስትደርስ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ።

'እረ እኔስ ደህና ነኝ ። ስትዘገዪ ጊዜ ጨንቆኝ ነበር' አልኋትና ጉዟችንን ዠመርን ።

"ቀዝቃዛ ነፋስ ሹሹ . . . ይላል ። ጨረቃዋ ዘግየት ብላ ነበር የወጣችው ። የሚወዷትን ልጅ በጨረቃ ይዞ መኮብለልን የመሰለ የለም ። ድካም የሚባል ነገር አልሞከራትም ። ተቆላው ላይ ስን ደርስ ነጋብን ። ጨረቃዋም አብራኝ አነጋች ።

"ጥር ወር ነበር ፤ ሌላው መኸር ተከቷል ። ሽንብራ ብቻ አልፎ አልፎ ማሳውን አረንጓዴ አልብሶታል ። ተጎዳናው ዳር ያገኘነው ሽንብራ ላያያዙ ለጉድ ነበር ። እባብ በላዩ ላይ ያስሄዳል ። መቼም እሸት አይታለፍ ፤ ገነት ቁማ አካባቢውን እየተመለከተች እኔ ገባሁና እመነግለው ዠመር ።

ይበቃኛን ያህል ተነቀለሁ በኋላ ጥቅጥቅ ታለ ጫካ ውስጥ ገባን ። ተዚያው ጫካ ውስጥ ወይን የሆነ ምንጭ አለ ። ምንጩን ተዚያ በፊት መኖሩን አውቅ ነበር ። የሸንብራው ሚጫራ እንዳይ ለበልበን ውሃ ነከርንና ተያያዝነው ።

“ተጠባብ ጓዳ ውስጥ ፣ አክስቴ አየችን አላየችን ፣ ገንት ተጠራች አልተጠራች እያለን የተጨነቅነውን ያህል አሁን እልም ታለ ጫካ ውስጥ የሸንብራ እሸት ይዘን ፣ ወይን የሆነ ምንጭ ተንተርሰን ፣ ተሰው ዘር ኢርቀን ፣ የብቻችን ተደሰትን ። አይኖቿ መቼም የጎድን ለማየት ነው የተፈጠሩት ። ተዚያ ጫካ ውስጥ እንኳን ባይኖቿ ሞልታ አታየኝም ። አፋራም ጥርሶቿም በሙሉ አይገለጡ ፣ በከፊል ሽፍረክ ይላሉ ። የፍቅርን ማህሌት ቁመን ዋልነው ። ምነው ዘለአለም እንደዚያ ሆነን በኖርን ።

“ተጫካው ውስጥ ውለን ስው ክትት ፣ አእዋፍ ስፍር ፣ አራዊት ከየጎሬአቸው ብቅ ብቅ ሲሉ ጉዟችንን ዠመርን ። እኩለ ሌሊት ላይ ታባባ ሞገስ ጠሜ ሚካኤል ደረስን ።

‘ጥሩ ነው ። ሚስት ታገባህ አናትህ ይረጋል ። አስታጥቄ አደብ የገዛው ብዙንሽን ታገባ ወዲህ ነው ። መቼም ደም ያለበት ሰው ትጥቅ ባያስፈታም ልብ ገዝቷል’ አሉኝ ፣ አባባ ሞገስ ተተቀመጥን በኋላ ። ገንት ልብሷ አሮጌ ስለሆነ እንዳ መሳቀቅ ስላለች ተኔ አጠገብ ጭብጥ ብላ ነው የተቀመጠችው ።

‘እይዞሽ! ዘና ብለሽ ተቀመጭ የኔ ልጅ ። ይሸም ያባትሽ ቤት ማለት ነው’ አሏት ። ማንኛውም መስተንግዶ ተተደረገልን በኋላ ምኝታ ተዘጋጅቶልን ተኛን ።

“በማግስቱ ተጎረቤት ሽማኔዎች ስለ ነበሩ በሶስት ጠገራ ብር ኩታና ቀሚስ ገዛሁላት ። ልብሱ ሲሰፋላት የዚያን እለት ውላን በማግስቱ ዞጋ ገባን ። እስታጥቄና ብዙነሽ ማመን አቃታቸው ። ነገሩ ሁሉ ቀና በመሆኑ በጣም ደስ አላቸው ። መስተንግዶው ተኸጎደጎደ ። ተምሳ በኋላ ትኩስ ማር ፣ ሸንኮር አገዳው ሁሉም ቢየይኑቱ ቀረበ ። የብዙነሽ ፈገግታ እራሱ ሳይበሉ ያጠግባል ። ገነት ያልጠበቀችው ነገር ገጠማትና ፡ ‘ይህማ አለም አይደል እንዴ ፤ ምን ሽፍትነት ነው ጌትነት እንጂ’ አለችኝ ፤ በመገረም ወደ ጎሮዬ ጠጋ ብላ ። በዚህ አይነት የሙሽርነት ጊዜያችንን አሳለፈን ።

ማ“ቀዬ የሚያደምቅ የልጆች ጫዋታ ባንሰም ቀያችንን እኛው እናደምቀው ነበር—እ፡በሳችን የፍቅር ሸማ ተላብሰን ። በስራ ቀን እኛ ወንዶቹ ፣ የቦዩን ውሃ እየመራን አትክልቱን ስናጠጣና ስንኮተኩት እንውላለን ። በበአል ቀን ደሞ ተመሃል ቀያችን ትልቅ የችብሀ ዛፍ አለ ። ተዚያ ጥላ ስር እንቀመጥና መጫወት ነው ።

“ሙቼም እስታጥቄ ሞገስ ዋሽንት ሲነፉ ተጫካ ነብር ፣ ተዛፍ ወፍ ያወርዳል ። ወዲያ ወስዶ ወዲህ ሲመልሰው ለሰመመን ነው የሚሰጠው ።

የዞጋ ውሃ ራሱ ተዋሽንቱ ጋር በማበር ጅጅ. . . ሺሺ. . .ሲል መላ አከላት በደስታ ይዋኛል ። ገንትና ብዙነሽ የዋሽንቱን ስብር ተከትለው እየ ተቀባበሉ ፣ 'ጉብልዬ' የተሰኘውን የዘመኑን ዘፈን ያንቆረቁሩታል ።

'ጉብልዬ! ጉብልዬ!

እመጣልሃለሁ አንተን ተከትዬ!'

"እጣታችውን ጭምር እያጮሁ አንገታችውን መታ መታ ሲያደርጉት እኔም ተቀብዬ ፤

'ጉብል! ጉብልዬ!

እመጣልሻለሁ አንቺን ተከትዬ' እላለሁ ።

"አስታጥቄ ሞገስ እጣቶቹን ተራ እያገባ ያነሳቸዋል፤ይጥላቸዋል ። ማንቂርቱም አብሮ ከፍና ዝቅ ሲል የዋሽንቱ ድምጥ ይቀጥናል ፤ ይወፍ ራል ፤ ያጥራል ፤ ይረዝማል ፤ ወሮቹ ይዘምራሉ ፤ የዞጋ ውሃ ያለ ማቋረጥ ይፈሳል ። እንዲህ ነበር የኛ አለም—በዚያን ጊዜ ።

"እንዲህ ስንል እንውልና ወደ ማታ አስታ ጥቄና እኔ ወደ ወንዙ ስንወርድ ሴቶቹ ደሞ የቤት ስራቸውን ያከናውናሉ ። የወንዙን ዳር ለዳር ተከት ለን ስንሄድ የወንዝ እዋራዎች ባንድ ላይ ስብሰብ ብለው ፣ ወይንም በጥንድ በጥንድ ሆነው እያሽ ካኩ ፤ ሲዳሩ እናገኛችዋለን ። ነጫጭ ፣ ጥቋቁር ፣ ነጭና ጥቁር ፣ እግርና አንገተ ረዥም ፣ አፋቸው

ጎራዴ የመሰለ ፣ ባለ ጉትያዎች ፣ ብቻ ዓይነታቸው ብዙ ነው ፤ ቁጥር አያልቅም ። ሁሉም በየወገናቸው ሆነው ፣ በቋንቋቸው ፍቅርን ይጫወታሉ ።

"ወደ ውሃው ቀረብ ስንል ደግሞ የውሀ እናቶች ይፍለቀለቃሉ ፤ አሳዎች ብቅ ጥልቅ ይላሉ ፤ እንቁራሪቶች ቁርር…ቁርር…እያሉ ሲጮሁ ያስደስታሉ ። ተደስታ ውለን ፤ ተደስታ አምሽተን ተቀናን ድኩላ ወይንም ሚዳቋ ገለን ፤ አለዚያም አሳ አጥምደን እንገባለን ።

"መቼም ቢሆን ቢኑራችን በኩል የገጠመን ደስታ እስከ አልነበረውም ። ሰርተን አንደክም ፣ ተጫውተን አንሰለች ፣ ፍቅራችን አይቀንስ ፤ ጎረቤታችን የዞጋ ውሃ መልኩን እየለወጠ ያስደስተናል።

"የዞጋ ውሃ ምን ጊዜም ቢሆን ሶስት አይነት መልክ አለው ። ተሰኔ ወር ገምሮ እስከ ነሀሴ ወር መጨረሻ ድረስ ድፍርስ ነው ። አፍ እስከ ደገፉ ይሞላና ይደነፋል ። አረፋሰሱ ተገና ተራራ ይነሳና ተላይ ተዶጋው ይቃሎ እየተባለ ይጠራል ። ዶጋውን አገር አቋርጦ ወደ ጠሀይ መውጫ ይፈሳል ። ተቃች ተቆላው ሲደርስ ዞጋ በመባል ይታወቃል ። ወደ ጠሀይ መውጫ ወደ ላስታ ጥግ ሲደርስ ወደ ግራ ይታጠፍና እተከዜ ወንዝ ይጨመራል።

"ተመስከረም እስከ ጥር ድረስ ደሞ ውሃው ኩልል ብሎ ይጠራና የውሃ እናቶችና አሳዎች ሲቧርቁ ማየት እንዴት ደስ ይላል ።

"ተየካቲት እስከ ግንቦት መዠመሪያ ደሞ ውሃው ቀስ በቀስ እየቀጠነ ፣ እየመነመነ ፣ አረንጓዴ እየለበሰ ፣ ድምጡ እየደከመ ይሄዳል ። ውሃ ለብሶ የነበረው ድንጋይ ውሃው ሲሸሸው በጠሀይ ይቀረናና ሽማ መስሎ ይነጣል ። ግንቦት ማለቂያ ላይ በበልጉ ዝናብ ውሃው አረንጓዴውን መግፈፍ ፣ መልኩን መቀየር ይዠምራል ። በንዲህ ሁኔታ ክረምቱ ይገባል ። ዛዲያ ሁሉም በወቅቱ ደስ ይል ነበር ።

"እየውልህ ፤ በንደዚህ ያለ ሁኔታ ደስ ብሎን ሳለ ፣ እናቴንም ተዛሬ ነገ አመጣታለሁ እያልሁ ሳስብ መቼም ለጥሩ ኑሮ ሳንከ አይጠፋውምና በኑሯችን ላይ ሳንከ ተፈጠረ ። "

# አስራ ሶስት

ያባ መሀሪ ታሪክ በቀላሉ የሚያልቅ ነገር አይደለም ። ለሶስተኛ ጊዜ በማግስቱ ልመለስ ቀጠሮ ሰጥቻቸው ሄድኩ ።

"የት ጠፍተህ ውለህ ነው ልጄ? ያገርህ ጫካና ገደል እንደ ሆነ ታይቶ አይጠገብም" አለችኝ ፣ አክስቴ ከቤት ስደርስ ። ካባ መሀሪ ሄጄ ነው አላልኋትም ።

በማግስቱ ቁርሴን በልቼ ወደ አባ መ... ገሰገስኩ ። ገደሉን—አሁንማ ለምጄው—ያለምንም ፍርሃት እወርደው ጀመር ።

"የሰው አእምሮው እንጂ ትልቅ የሚያሰኘው እድሜው አይደለም" አሉ ፣ አባ መሀሪ ሰላምታ ተለዋውጠን ከተቀመጥን በኋላ ።

"እንዴት ?" አልኋቸው ።

"እንዳው ያንተ ነገር እየገረመኝ እንጂ የልጅ አዋቂ ። ለስንቱ አረጋዊ ስነግር እንኳን ጉዳዩን ተቁም ነገር ቆጥሮ የሚያዳምጠኝ የለም ። አንተ ዛዲያ በቁም ነገር እየተመላለስህ እንደ መልካም የንፍስ አባት ኑዛዜዩን ስትቀበለኝ በጣም ነው ደስ ያለኝ።

እንዳው ጣድቋን ተሳይ የተሳከህ እንጂ እውነትስ …” ብለው ንግግራቸውን መደምደሚያ ያጡ ለት ይመስል በጅምሩ ተውት ።

አባ መሀሪ የሻከረ ጉሮሯቸውን ጠራርገውና ዋናውን ታሪካቸውን ከቆሙበት ቀጠሉልኝ ።

“እየውልህ ፤ ባለ ደሞቹ እኔን ማግኘት ቢያቅታቸው አጋም ውሃ ወርደው ያከሰቱን ባል ገደሉት ። እናቴን በማስጠጋቱ ሞት ፈረዱበት ። እኛም ተዘጋጀንና ደሙን ለመመለስ ወደ መስቀች ሄድን፡፡ያቶ ፈንቴ መንገሻ አጎት የሆኑ መምሬ ደሱ የተባሉ ካህን ነበሩ ። የቅርብ ዘመድ ያገኘነው እሳቸውን ነው ። መቼም እስከ ሰባት ትውልድ እየቆጠሩ መግደል የተለመደ ሆኗል ። የሳቸውስ ዝምድና ተሶስት ቤት አይበልጥም ።

“እለቱ ያመቱ መዳህኒአለም ፣ መጋቢት ሃያ ሰባት ነበር ። ህዝቡ ተቤተ ክርስቲያን መመለስ ይዟል ። ተመንገድ አድፍጠን ጠበቅናቸው ። ቄስ ምረቴ ተተባሉት ጋር መጡ ። በርኖሳቸውን ለብሰው ፣ እረኝርም ጥምጥማቸው በሩቁ ይታያል ። ሁለቱም በዋቃታ ነው የሚያወሩት ። ተኛ አጠገብ ሲደርሱ እስታጥቄ አድፍጠ እየተጠባበቀ እኔ ተዱሩ ውስጥ መኸርለጥ ብዬ ስወጣ ሁለቱም ካህናት መሬት ተከፍታ ብትውጣቸው በወደዱት ። እናዝገቤ ለመግደሏ ቀስ ብዬ በርጋታ ጠመንጃዬን ዘቅዝቅቄ ወደነሱ ስሄድ መምሬ ደሱ ፈትለክ አሉ ። ቄስ ምረቴም ወደ ኋላ ተመልሰው ሽቅብ እሮጡ ። በርከከብዬ ስትኩስ ሳተኋቸው ።

'ሳተሃቸው!' አለ ፣ አስታጥቄ ሞገስ ተዱሩ ውስጥ እየወጣ ። ተቋንጃው ሽብርክ ብሎ ተኮሰ። እሱም ሳታቸው ። 'እንዲህ ነችና! ይህ አስማታም ቄስ!' ብሎ ቀለሁን አፈናጥሮ ሴላ ሲያቀባብል መንገዱን ሰብረው ተዱር ውስጥ ሲገቡ ጥምጥማቸ ውን ያጋም እሾህ ያዘባቸውና ለማስለቀቅ ቆም ሲሉ በብብታቸው መታኋቸው ። እንደ መንገዳገድ ብለው ሲወድቁ ጥምጥማቸው ተሾሁ ላይ ተንጠ ልጥሎ ቀረ ። እየሮጥን ስንደርስ ነፍሳቸው ገና አል ወጣም ።

'አንት አስማታም ቄስ!' አለና አስታጥቄ ባንድ ጥይት ደገማቸው ።

''አሯሯጣቸው ትዝ ይለኛል ። የበርኖሳቸው በግራ በኩል ተትከሻቸው ላይ ያህያ ኀሮ መስሎ የቆመው ዝላ ዝላ እያለ ጥምጥማቸው እስቲበር ድረስ ነበር የሮጡት ። ዛዲያ በዚህ የተነሳ እረ ኞች ምን ብለው ዘፈኑ መሰለህ፦

'መሀሪ መጣ አይኑን አፍጥጦ ፤

ሆይ መሸሽጊያ ትንሽ ቁጥቋጦ ።

እግሬ አውጭኝ ሲሉ መምሬ ደሱ ፤

በረኸም ጥምጥም ጫካ ሲጥሉ ፣

መሀረኚ እያሉ ጠሎት ቢያደርሱ ፤

አልማራቸውም ጨካኝ ነው እሱ ።'

‘እነሱም ከአፍጥባቸው ጋር በነገላ ሆነው ፤ እኔም ከአስታጥቄ ሞገስ ጋር ዞጋ ሆኜ እንፎካከር ጀመር ፤ በመሃከሉ እናቴ ታማ ሞተች ። ለኔ መሪር ሀዘን ቢሆንብኝም ለሷ ትልቅ እረፍት ነበር ። እኔን እርግዛ ሴት ተቀን እህህ... ስትል አረፈች ።

“ባለ ደሞቼ አፍጥባቸውን ይዘው እኛን ለማጥፋት ሲዝቱ ሚቹ አጎቴ እኔን ወደ አፍጥባቸው ወስዶኝ ባለ እርቅ እያደረጉ ከደረስነው ሽፍቶች ጋር ጠባቸው አገርሽቶ ተኩስ ገጥመው አፍጥባቸውና መሀከለኛው ባለ ደሜ ሞቱ ። እየውልህ ፤ ‘ለጠላቴ ጠላት ስጥልኝ’ የሚባለው እንዲህ ያለው ነው ። ተንግዲህ ወዲያ አንድ ላንድ ነን ። ከፈለገም ፊት ለፊትም ቢሆን ግድ የለኝም እያልሁ ስፎክር ሰንበት ብሎ ሌላ ወሬ ተሰማ ።

“ባለ ደሜ መስቀች መጥቶ እኔ ጋር አስታርቁኝ እያለ ያገር ሽማግሌዎችን ያስቸግራል አሉ። ጸውነትም ምልዶቹ በአባባ ሞገስ በኩል ደረሰኝ። ሁለት ሶስት ጊዜ ያህል ሽማግሌዎች ተተመላለሱ በኋላ ዋናው እርቅ መስቀች መዳህኒአለም ላይ እንዲሆን ተወሰነ ።

“በኔ በኩል ነገረ ሬጅ ሆነው የተረቡት አባባ ሞገስ ናቸው ። በሱ በኩል ደሞ አንድ ዘመዱ የሆን ነበሩ ። ቄስ ምረቴ ተተቀመጡበት ተነሱና ፤ ‘ዘመዶቼ ፤ ወንድሞቻችን በማይረባ ነገር ተነሳስተው ይህን ያህል ደም በከንቱ ተፋሰሱ ። በመጥሀፉም ቢሆን የተደነገገው አንድ ወንድ ላንዲት ሴት ፣ አንዲት ሴት ላንድ ወንድ ነበር ። ነገር ግን እንዳንድ

እግዚአብሄር ሲፈጥራቸው አመንዝራ ይሆኑና የወገናቸውን ሚስት ወይንም ባል ይጋራሉ ። በወንድሞቻችንም ላይ የደረሰው ችግር ይህን የመሰለ ነው ። "

'የሌላውን ቆንጆ ሚስት አሻግሮ ከማየት የራስን ሚስት ቢያበጃጅዋት ፣ ቢመቿት ያማረች፣ የቆነጀች ትሆናለች ። ነገር ግን የተበደለው ወንድ ወይንም ሴት ይህን ከማድረግ ልቦናቸው ይታወራል ። የሚመኙት የውጪውን እንጂ የቤታቸውን ተቁም ነገር አይቆጥሩትም ። በንሯቸው በኩልም ሰላም የለም ። ቤታቸው የንዝንዝና የጭቅጭቅ ቤት ይሆናል ። እሷም ሌላ ስትፈልግ ፣ እሱም ሌላ ሲያስብ የሞቀ ትዳራቸው ይፈርሳል ። ወይንም እንደ ወንድሞቻችን በከንቱ ደም ይፈሳል ። ሲፈጠሩ የተመረቁ ባልና ሚስት እነሱ ተደስተው ሌላውንም ያስደስታሉ ። የተረገሙት ግን እነሱ ተረግመው ሌላውን ያስረግማሉ ። በነውር ስራ የጎደፉ ምን ጊዜም ቢሆን ነውረኞች ናቸውና ። መቼም ቢሆን ወንድ ልጅ በሚስቱ መቅናት ያለ ነው ። ግማሽ አካሉ ናትና ይገባዋል ። ሚስትም ብትሆን በበሏ ብትቅና አግባብ አላት ። ይሁን እንጂ ባል በሚስቱ ላይ ማመንዘር ፣ ሚስት በባሏ ላይ መሄድ የቆሸሸና ያደፈ ተግባር ነው ። እንዲህ ያለው እርካሽ ስራ ነው ወንድሞቻችንን ለልቂት ያበቃቸው ። እኔ ራሴ ያይን ምስክር ነኝ ። የስጋ ዝምድና ሳይኖረን በመቅረቱ ተሞት ልተርፍ ቻልኩ ። መምሬ ዶሉ ግን የስጋ ዝምድና ሀረግ ጎትቷቸው ለስም

በማይበቃ ሞት ሞቱ ። ሁላችሁም እንደምታውቋቸው መምሬ ደሱ የተከበሩና ቅህትና ያላቸው፣አዛውንት ካህን ነበሩ ። ይልቁንም ይህን የመሰለ አጠያፊ ስራ አጥብቀው ይቃወሙ ነበር ። ዛዲያ በንዲህ አይነት ሞት መሞታቸው የሚያሳዝን ጉዳይ ነው። ስራ ለሰሪው ቢሆን ጥሩ ነበር ። ነገር ግን ለሀጣን የወረደ ለጣድቃን ነውና ያንዱ መጥፎ ስራ ለሌላው ይተርፋል ። ይህም በመሆኑ የብዙዎቹ ቤት ተዘግቷል ።

'ልጆቼ፤ያለፈ አልፏል፤እስቲ ለወደፊቱ ልብ ግዙ ። እናንተ እንኳን ለዘር ትረፉ' ብለው ብዙ ተተናገሩ በኋላ ሌሎቹም ሽማግሌዎች እንዲሁ ተራ በተራ ተናግረው ሲጨርሱ የሁለታችንም ጠመንጃ ተጋድሞ ፣ ስእለ መስቀል ቀርቦ በክፉ ላንፈላለግ ተማምለን የርቁ ፍጣሜ ሆነ ።

"ተባለ ደሜ ጋር ተታረቅሁ በኋላ የሰላም ኑሮ መኖር ዠመርን ። የዘጋ ውሃ የደጋውን ቦረቦር ተሸክሞ በመምጣት ላይ ነው ። ጨረቻውን በክፉል ማልበስ ይዟል ። ሰኔ ወር መገርመሪያ ነበር።ክረምቱ መጣሁ መጣሁ እያለ ያስገመግማል ። ባገራችን ክረምት ሳይገባ ፣ ውሃ ሳይሞላ ዘመድ ይጠየቃል ። ተዚህ በኋላ በጥቢ እንገናኝ ይባላል ። ጥቢ የሚሉት መስከረምን ነው ። በዚህ የተነሳም የነት ዘመዶቿን ናፈቀች ።

"ቀደም ሲል ያልጠየቀችኝን ተባለ ደሜ ጋር ተታረቅሁ ገሞሮ ዘመዶቿን ሄደን ምህረት

እንድንጠይቅ ጢት ማታ ጨቀጨቀችኝ ። እኔ ደሞ ምንም እንኳን ተባለ ደሜ ጋር ብታረቅ በመንግ ስት በኩል ገና ምህረት ስላልተደረገልኝ መዘዋወ ሩን ፈርቻለሁ ። ወደ ደጋውም የገደለሁት ነጋዴ ዘመዶች እያጠያየቁ ስለሆነ ወደ አዲስ አንባ መሄዱ አስፈርቶኛል ። ገነት መሸም ፣ ነጋም ውጥር አድ ርጋ ስትይዘኝ ጊዜ አስታጥቄ ሞገስ ፣ 'አየህ ተገ ነት አባት ጋር መታረቁ ትልቅ ጥቅም አለው ። በመንግስት በኩል ያለውን ጣጣ እሳቸው ሊጨ ርሱት ይችላሉ ። ወዲያውምኮ ልጃቸውን አገባህ እንጂ አልገደለህም' በማለት አደፋፈረኝ ። እሽ ብለው ይታረቁን ይሆን ? ወይንስ እንቢ ብለው ልጃቸውን ነጥቀው እኔን ያስሩኝ ይሆን ? ይህን የመ ሰለው አሳብ እያስጨነቀኝ ገነትን ይዤ ወደ አዲስ አንባ ሄደሁ ።"

## አስራ አራት

‘‘መጥፎውንም ፣ ደጉንም እያሰብን መድረስ አይቀርም አዲስ አንባ ደረስን ። ወደኔ አክስት ቤት ነበር የሄድነው ። በኛ የተነሳ የደረሰባት ስቃይ ክፍተኛ ቢሆንም፣ ስቃ ተቀበለችን ። ማታ ፤ ‘በናንተ የተነሳ የደረሰብኝን መከራ እሱ የላይኛው ጌታ ይፍረደው ። አባትሽ አስደፈርሽኝ ብለው ባገር መቀ መጫ አሳጥተውኝ ፣ ባለቤቴ ቢሞትም ክብሬን ጠብቄ የተቀመጠሁትን ሴት እንደ ጋለሞታ ዝቅ አድር ገው ጩሰው ፊት አዋረዱኝ ። ብቻ ተላይ ቤት አገ ኘዋለሁ’ አለች ፣ አክስቴ እንደ እንባ ተናነቃትና አይኖችዋን በቀሚሷ እጅጌ እየጠራረገች የደረሰባ ትን ሁሉ ስታወራን ፣ ገነትና እኔ ትንፍስ ሳንል እንገታችንን ደፍተን አዳመጥናት ።

‘‘በማግስቱ አክስቴ ቤተክርስቲያን ሄዳ የግ ራዝማች ተፈራ እሸቴን የንስሃ አባት ይዛ መጣች ። ቄሱ በመዠመሪያ እኛን ታነጋገሩ’ በኋላ ወደ ግራ ዝማች ተፈራ እሸቴ ቤት ሄዱ ። ‘እናንተን እሽ ብለው በማሩልኝ እንጂ እኔን የበደሉኝን ባላስታ ወስሁት’ እያለች ስትጨነቅ ቄሱ መጡ ።

‘ወይዘሮ ልኬ የለም ግራ በቀኝ ጎንም ነው የተነሱ ። እንደ ፈራነው ሳይሆን ነገሩ በሰላም አለቀ’ አሉ ፣ ወደ ቤት እየገቡ ።

ገሏን ። ወዲያው የፍየል ሙክት ተጥሎ ጎረቤቱ ሁሉ ተጠርቶ ቅልጥ ያለ ግብግር ሆነ ። ማታ ተራት ላይ ባፍ ባፌ ሲያጎርሱኝ ልቤ በደስታ እየዋኘ ላብ በግንባሬ ይንቆረቆር ነበር ። መብሉም ፤ መጠጡም ሳያቋረጥ ሲናኝ አምሽቶ ተጋባዡ ሁሉ በየቤቱ ተሄደ በኋላ እሳቸውና እኔ ጭውውት ያዘን ።

'አይዞህ እንግዲህ ወዲያ የሚያሰጋህ ነገር የለም ። በመንግስት በኩል ያለውን እኔ እጨርሰ ዋለሁ ። አሁን ነው ምህረት የማሰጥህ' ሲሉኝ ብድግ ብዬ ጫማቸውን ሳምሁ ። ንግግራቸውን በመ ቀጠል፡ 'እንዳውም ተዚያ በረሃ ተወንዝ ዳር እንደ ጋኔል አትቀመጡም ። ተዚሁ ተኔ አጠገብ ቤታ ችሁን ሰርታችሁ ትቀመጣላችሁ።' አሁንም ተነስቼ ጫማቸውን ሳምሁኝ ።

'እስከ ግማሽ ሌሊት ድረስ ተተቃበጥን በኋላ መኝታ ተሰጥቶን ተኛን ። መጠጡም ፤ ደስታውም ተደራርቦ እሳብ ደህና ሁኝ ስላለን ጋደም ተማለ ታችን እንቅልፍ ጣለን ። ምን ጊዜ እንደ ነጋ አላ ውቅነውም ። የሚጣፍጥ እንቅልፍ ይዞን ሳለ አንድ አሽከር መጥቶ ቀሰቀሰን ። ሁለታችንም ተንቅልፋ ችን እየባነን ስንነሳ ወፎች እየተንጫጩ ነው ። አሽከሩ ፤ ገንትን ፤ 'ነይ ትባያለሽ' ብሏት ተመለሰ። ተንቅልፏ በመጽረጧ እየተነጫነጨች ልብሷን ለብሳ ወጣች ለሥራ ተፈልጋ ይሆናል አለሁና እኔ ተመ ልሼ ተኛሁ ። የጧት ተንቅልፍ መጥፎ ነው ወዲ ያው ይዞኝ ጭልጥ አለ ። ተንቅልፌ የነቃሁት ጠመንጃዬ በሰው እጅ ተገባ በኋላ ነበር ።

# አስራ አምስት

“ያ ሁሉ የድግስ ጋጋታ ፣ ያ ሁሉ የተቀደሰ ቃል ሳይውል ሳያድር በግማሽ ሌሊት ከንቱ ሆነ። የማታው ደስታዬ ወደ ስቃይ ተለወጠ ። ባፍ ባፌ ባጎረሱበት እጃቸው በጥፊ ይጠፈጥፉኝ ገመር ።

“ባላሰበሁትና ባልጠረጠሁት ሁኔታ ልጃቸ ውን ወደ እልፍኛቸው ጠርተው እኔን ባሽከሮቻ ቸው አሳፈሩኝ ። ይህ ወንድነት ሳይሆን ከሀዲነት ነው ። ጥፊው ፣ እርግጫው ለጠላቴ አይስጠው ።— ሲሰርቅ እንደ ተያዘ ሌባ ቀጠቀጡኝ ። አሽከሮቻ ቸው እየደበደቡኝ የነሱ በትር አልጠቅማቸው ብሎ ያለ የሌለ ሃይላቸውን ይወግጡኝ ነበር ። በኋላማ ተረታሁና በደም ተጨማልቄ ወደቅሁኝ ። ተደጅ አውጥተው እጆቼን የኋሊት በገመድ ሲያ ስሩኝ አክስቴ ደረሰች ።

‘በፈጠረዎት ጌታ ! አንድ እሱ ብቻ ነው የቀረው ፤ ለዘር እንኳን ይትረፍ !’ ብላ ተግራቸው ላይ ወደቀች ።

‘ያስደፈርሽኝ እንሶሽ አሁን ደሞ ትቀላም ጃለሽ ! ለዘር ይትረፍ የምትዪው የኔን ልጅ አግ ብቶ ሲወልድ !’ አሉና በጥፊ መንጋጭላዋን ሲያ ቃጥሏት ወደቀች ። ተወደቀችበት እየተንገዳገደች

ስትነሳ ባፏ ደም ተፋች ። የፊት ጥርሶቿ የላይ ኞቹ ሁለቱ አምርመውረው ለመፀውለቅ የመዘመዘ ነበሩ ፤ እነሱ እረገፉ ።

“የፊጥኝ ታስሬ ታብቃሁ በኋላ በቅሏቸውን አስጭነው ፤ ሁለት አሽከሮቻቸውን በማስከተል ፤ ጠመንጃዬንና እንግቴን አሲዘው ወደ ነፋስ መውጫ ይዘውኝ ሄዱ ።

“በዘመኑ ሽፍታ አድኖ የያዘ ሰው የሽፍታው መሳሪያ ሊያገኙ ይፈቀድለት ነበር ። በዚህም የተ ነሳ የኔ ምንሽር እስከነ እንግቴ ተፈቀደላቸው ። ብቻ እሳቸው አታለው ፤ ተቤታቸው እስተኝተው ያዙኝ እንጂ እንደ ገማግኖች ሁሉ አድነው አይደ ለም የያዙኝ ። ነፋስ መውጫ ጥቂት ቀኖች እንደ ተቀመጥሁ ወደ ጎንደር ተልኬ ባታ ወህኒ ቤት ገባሁኝ ። በክርክር አንድ አመት እንደ ተቀመ ጥሁ የስቅላት ሞት ተፈረደብኝ ።

“ወንጀሉን ተፈጠመበት ፤ ታገሩ ላይ እንዲ ሰቀል ተባልሁ ። እንደኔው የስቅላት ሞት የተፈ ረደባቸው አንድ ቄስ ነበሩ ።እሳቸውም አገራቸው ሆራንባ አውናሬጋይ ስለሆነ ተኔው ጋር ሀጂ ሆኑ ። በመሀራ (በዘኬ) የተነሳ ታንድ መነኩሴ ጋር ተጣ ልተው ተተኛበት በመቋሚያ ቀጥቅጠው በመግ ደላቸው የተነሳ የግፍ አገዳደል ተብሎ ነው የስ ቅላት ሞት የተፈረደባቸው ።

“ተቄሱ ጋር ተቆራኝተን ፤ ባራት ቡሊሶች እየተጠበቀን ፤ በካሚወን ተጭነን ወደ ጋይንት ስን

ወሰድ አዲስ ዘመን ላይ ስንደርስ ካሚዉኑ ተበላሽ ። እስቲሰራ ድረስ አዳር ተዘጋጀው ሆነ ።

“ሞትን በራስ ተሸክሞ ፣ አይን እያየ ፣ገርሮ እየሰማ ወደ መቃብር መነዳት ተስቃይ ሁሉ የከፋ ስቃይ ነው ። ቄሱን ተቅማጥ ያዋከባቸው ገርመር ። በሰንሰለት እንደ ተቆራኘን መመላለስ ያዘን ። እኔ በፊት ፍዝዝ ብዬ በገመድ እንዴት አድርገው እንደሚሰቅሉኝ ነበር የማስበው ። ቄሱ ምልልስ ሲያበዙ ጊዜ አንድ ነገር አሰበሁ ። ቢሰኒም ባይሳካም ልሞክረው አልሁና እኔም ተቅማጥ ያዘኝ አለሁኝ። በመገርመሪያ አራቱም ቡሊሶች ነበሩ በአንድ ላይ ይዘውን የሚወጡት ።በኋላ ምልልሱም ጠና እኛም እየተዳከምን ሄደን ።በተለይ እኔ ተቄሱ ብሼ ልው ስውስ አልሁ ። ሁኔታችንን አዩና ሁለት ሁለት በመሆን ተራ ገቡ ።

“እኩለ ሌሊት ላይ ቄሱ ትንሽ ቃገሰላቸው ። እኔ ግን ባሰብኝ ። ቄሱ ተቆመላቸው በኋላ ተኔ ጋር እየሄዱ መገተሩ ስለ ሰለቻቸው የብቻቸው እንዲያስሯቸው ለመኑ ። የተቆራኘንበት ሰንሰለት ተፈቶ እሳቸው ቃሰሩበት ። እኔም ጋዶም ባልሁ ቁጥር እጅና እግሬ እየቃሰረ ነበር ።

“ሶስት ጊዜ ያህል ስመላለስ ሁሉቱም ቡሊሶች ነበሩ ይዘውኝ የሚወጡት ።ኋላ አንደኛው ተቀነሰ ። ጨረቃ ነበረች ።ግና በደመና ስለ ተከበበች ብርሃኗ ደብዘዝ ያለ ነበር ። እኔ ተቀምጬ አምጣለሁ ።የሚወጣኝ ነገር ስለሌለ በደረቁ እን

ጣጣለሁ ። በሊሉ ጠመንጃውን በብብቴ ይዞ ተፈት
ለፈው ተገትሯል ። ቀና እያለሁ መላልሼ አየሁት ፤
ሰውነቱ፡ ዛል ብሎ የድካም ምልክት ይታይበታል ።
ቁምጣ ሱሪዬን እንደ ተቀመጠሁ ታጠቅሁና እጄ
ላይ የመጠነውን ድንጋይ አመቻችቼ በመያዝ
እንደ ወስፈንጠር ተወርውሬ መሃል ደረቱን አደ
ረቅሁት ። እንደ በሬ አጓርቶ ነው ፍርጥ ያለው ።
ጠመንጃውን ነጥቄ መሮጥ የነበረብኝ መሆኑን
ያስታወስሁት ብዙ ተራቅሁ በኋላ ነበር ። ጥይት
ሲንዲዲ ይሰማኛል ። ጨረቃዋ ወዲያውኑ ተደመናው
ውስጥ ወጣች ። ቁልቁለት ሲሆን እሮጣለሁ ፤
አግድመት ላይ ደሞ እገሰግሳለሁ ። አቀበት ሲገጥመኝ
ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ እስቲል ድረስ እሄዳለሁ ።
እንዲህ እያለሁ ሌት ተቀን አወዛውገር በሶስተኛ ቀኔ
ጋይንት ገባሁ ። በቀጥታ የሄድሁት ዞጋ ቱን
አስታጥቄ ሞገስ ነበር ። እኩለ ቀን ላይ ነው
የደረስሁት ።

“አስታጥቄና ብዙነሽ ተችብሀው ዛፍ ስር
ተቀምጠው ህጣን ልጅ እያጫወቱ ይሳሳቃሉ ።
በመዠመሪያ ያዩኝ ውሾቹ ነበሩ ። ጉግግ...ብለው
መጡብኝ ። ቆራርጠው ጣሉኝ ብዬ ፤ ‘ተው ! እኔ
ነኝ ቡቼ !’ ስላቸው ጅራታቸውን እየቆሉ ተግሬ
ላይ ተጠመጠሙ ። እየውልህ ፤ ታመት በላይ ተቀ
ምጬ ስመሷሰ አላጠፉኝም ። አስታጥቄና ብዙነሽ
ያዩኝ ውሾቹ ወደኔ እየጮሁ ሲመጡ ነበር ። አስ
ታጥቄ ሞገስ ጠመንጃውን ተመቅጥበት አንስቶ
ቦታ ለመያዝ ከጅሎት ነበር ። ውሾቹ እግሬ ላይ

ሊጠመጠሙ ፈዞ ቀረ። ውሾቹ ግራና ቀኝ ከበ ውኝ ወደነሱ ስሄድ፡—

‘እውነት መሀሪ ተበጀ ነህ ?! ወይንስ አም ሳያ ?’ አለ፡ አስታጥቄ ወደኔ እየመጣ።

‘አምሳያው ነኝ እንጂ መሀሪማ የስቅላት ሞት ተፈርዶበታል ። አልሰማችሁም እንዴ ?’ አል ሁት፡ የደስታ ፈገግታ ፊቴን አድምቆት ። ተቃቅ ፈን ስንሳሳም ሰውነቱ ሁሉ ይንቀጠቀጥ ነበር ። እሱን ለቅቄ ብዙነሽን ስስማት እሷም እንዲሁ የደስታ ድንጋጤ ይዟት መናገር አቅቷት ነበር ። እነሱን ስሜ ታብቃሁ በኋላ ተመሬት የተቀመ ጠውን ህጣን አንስቼ ሳመሁት ። የማላውቀው ሰው ሳመኝ ብሎ አለቀሰ ። ልጁን ለናቱ ሰጥቼ ተያይዘን ወደ ቤት ገባን ።

“አስታጥቄና ብዙነሽ ወንድ ልጅ ወልደው ቆዩኝ ። የስድስት ወር ልጅ ነበረ ። በኑሯቸው በኩ ልም ደስ ብሏቸው ነው የሚኖሩት ። ጥሪትም አፍ ርተዋል ። አንድ በሬና አንዲት ላም፡ አንድ አህያ ገዝተዋል ። ጥቂት ፍየሎችና ዶሮዎችም አርብተ ዋል ። ቀርሃቸውም ታራት ወደ ስድስት ክፍ ብለ ዋል ። የሚታረስ በሬ፡ የሚታለብ ላም፡ የሚጫን አህያ፡ የሚታረድ ጠቦት፡ ሲያምር ትኩስ ማር ትንሮ ሲቆረጥ፡ ታትክልት በታ ሄዶ የሚፈልጉ ትን ያትክልት አይነት ቀጠፍ፡ ቀጠፍ አድርጎ ሲገ ቡት፡ ወንድ ልጅ ሲወለድ፡ ተዚህ የበለጠ ኑሮ፡ ተዚህ የበለጠ ቅዳር፡ ተዚህ የበለጠ አለም ምን

ሊገኝ ? እየውልህ ፤ እነ አስታጥቄ ሞገስን እንዲህ ያሉ ባለጠጎች ሆነው ነው ያገኘኋቸው ። እኛና ገንት ብንኖርም ልጅ ወልደን እንደነሱ የጥሪት ጌታ እንሆን ነበር ።...”

# አስራ ስድስት

"ታስሬም ሳለ የልብ ቁስል የሆነችኝ ፣ ተዚያ ተደረስሁ በኋላም በሽታ የሆነችኝ ገነት ነበረች ። አስታጥቄ ሞገስ በወሬ የሰማውን አጫወተኝ።

"ገነት እኔ የተያዝሁ እለት ተልፍኝ ውስጥ ተዘግቶባት ስታለቅስ ነው የዋለችው አሉ ። እስከ ብዙ ቀን ድረስም አልረሳኝ ብላ አስቸግራ ነበር ። ተስፋዋን የቆረጠችው ወደ ጎንደር ተተወሰድሁ በኋላ ነው ። ኋላም እዚያው አቅራቢያ ዳሯት።

"እባቷ ፣ ግራዝማች ተፈራ እሽ·ቴ እረኸዎ አልቤናቸውን ላግቻቸው ፣ ለገነት ባል ሰጥተው እሳቸው የያዙት የኔን አጭር ምንሽር ነው ።አከ ስቱ እኔን የያዙን እለት በጥፊ ሲመቷት ጥርሶቿ ስለ ወለቁ በዚሁ ሳቢያ ታማ ሳለ ባፏ ምታት ስለ መታት ብዙ ቀን ታማ ሞተች ። ይህን የመሰ ለውን ነገር ስሰማ ሊበርድልኝ የማይችል ንዴት ያዘኝ ። እኒህን ክፉ ሰው ለመግደል ቆረጠሁ ።

"መቼም እግር እስቲነቃ ድረስ ቢኬድ እንደ አስታጥቄ ሞገስ ያለ ጓደኛ አይገኝም ። እንግደል ስለው ትንሽ እንኳን አላንገራገረኝም ። 'ለወዳጄ ማር ለጠላቴ ኮሶ' የሚባለው እንደሱ ያለው ሰው ነው ።

“ተመንገድ እምልጪ መምጣቴን ሰምተው ጥንቃቄ ሳያደርጉ ዞጋ በገባሁ በሶስተኛው ቀን ፣ ድካሜ እንኳን ሳይለቀኝ ግራዝማች ተፈራ እሸቴን ለመግደል ወደ አዲስ አንባ ወጣን ። መሳሪያችን አንድ ነው ፣ ያስታጥቄ ሞገስ ጠመንጃ ብቻ ። ማታ ወደ ግቢው ለመግባት ሳይሆንልን ቀረ ። ውሾቹ አላስጠጉንም ፤ እንዲሁ አጥር ስንዞር አድረን ጧት አንድ ዘዴ አገኘን ። ሉዲ የሚባል ያገልጋያቸው ልጅ ከብት እረኛ ነበር ፤ ምኝ ቢጤ ስለ ሆነ እሱን ብንጠይቀው የት እንደሚውሉ ይነግረናል አልንና ክብቶች ወደተሰማሩበት ሄደን ። እኔን ስለሚያውቀኝ ጠመንጃውን ይዤ ፣ ጎሬ ውስጥ አደፈጥሁ ። እስታጥቄ ተሩቅ አገር የመጣ ዘመድ መስሎ ሲጠይቀው የዚያኑ እለት ማለዳ ወደ ነፋስ መውጫ የሄዱ መሆናቸውን ነገረው ። ተዚህ በኋላ ይቃሉ ወንዝ ወርደን ጎደብን ። የዚያን እለት ሳይመጡ ቀሩ ።

“በማግስቱ በሩቅ ባበቅሎ ሆና የሚመጣ ሰው ስናይ ሲቃ ሲይዘን ሲደርስ ሌላ ይሆናል ። እንዲሁ ስንል ዋለን ። በሌላ መንገድ ሄደው ይሆን እያልን ስንሰጋ ወደ ማታ ገደማ በጥርጃ በቅሏቸው እየተሽረበረቡ ሲመጡ እየናቸው ። የምንሆነውን አጣን ። የኔኑ ምንሽር ገሊታ የተባለው አገልጋያቸው ተሸክሞ ፊት ፊት ኩስ ኩስ ይላል ። ገሊታ የዚያን እለት ተቀጠቀጡኝ አሽከሮቻቸው አንዱ ነበር ። ዋጋቢኛ ወጠምሻ ስለሆነ ጠመንጃውን በዋዛ የሚነጠቀን አይደለም ። ስለዚህም በመዝመሪያ እሱን ለመግደል ወሰን ።

"ተወንዙ ውስጥ ሲገቡ በቅሎዋ ውሃ መጠ
ጣት አምርራት ቆመች ። ግራዝማች ተፈራ በግሮ
ቃቸው ኮለኮሏት ። እንደ መሄድ ብላ የኋላ እግሮ
ቿን ሽብረክ በማድረግ ፣ ጭራዋን ብድግ አድርጋ
ሽንቷን መሽናት ያዘች ። ገለታ ወንዙን ጨርሶ
ለመሻገር ሲቃረብ አስታጥቄ ሞገስ በሽንጡ ለቀ
ቀበት ። ተምዘግዝጎ ታለቱ ድንጋይ ላይ ተፈጠ
ፈጠ ። ይህን ጊዜ ግራዝማች ተፈራ እሼቴ ተበቅ
ሏቸው ለመውረድ ሲቃጡ እሳቸውንም መታ
ቸው ።በኮርቻው ትንሸራተው ፣ ተውሃው ላይ ወደቁ።
በቅሎዋ ጎፍታ ያገሯን አቅጣጫ በመያዝ ፈረጠ
ጠች ። ገለታ ተወደቀበት እየተንገዛገዘ ሲነሳ በደ
ረቱ ደገመው ። ጠመንጃውን ለቆ የንግሊላ ወደቀ ።
ይህን ጊዜ ታደፈጥንበት ወጣን ። እየሮጠሁ ሄጄ
ጠመንጃዬን ተጄ አገባሁ ። አገላብጬ ሳመኋት ።
ቃታውን ስከፍተው ጥይት አልተቀባበለም ። አገር
አማን ብለው ኖሯል ። አቀባብለሁና ወደ ገለታ
ስጠጋ ነፍሱ አልፋለች ።ተወገቡ ላይ ዝናሩን
ፈትቼ ወደ ግራዝማች ተፈራ ተመለስሁ ። አስታ
ጥቄ ታጠገባቸው ቁሞ ያናግዛቸዋል ። እኔ ስደ
ርስ ፣ 'ይህን ሰው ያውቁታል ?' ሲል ጠየቃቸው ።
ግመን እቃታቸውና አይናቸቸውን በሙሉ አፍ
ጥጠው አስተዋሉኝና፡—

'በየት አድርገህ መጣህ ?' አሉኝ ።

እስዎ ፣ ነፋስ መውጫ ወስደው ጥስ ብመ
ሆን ምህረት አሉጥተውኝ ፣ ጎንደር ወርጄ የምህረ

ቱን ቀላጤ (ደብዳቤ) ጽገር መምጣቴ ነው' አል ኋቸው ። ተዚህ በኋላ አንድ ቃል አልተናገሩም ።

"መቼም ቢሆን ጠላትን እናዞ ምህረት መስጠትን የመሰለ ነገር የለም ። ታላቅነት ፣ ታጋሽነት ነው ። ግና ግራዝማች ተፈራ እሽቴ ምሳሌ የሌላቸው ከሀዲ በመሆናቸው ምህረት የሚደረግላቸው አይደሉም ። ለኒህ ሲያምኗቸው ለማይታመኑ ፣ የተናገሩትን ቃል መልሰው ለሚበሉ ክፉ ሰው ተገቢውን ቅጣት መስጠት ያስፈልጋል ። አንድ ሞት ሳይ ሆን ሁለት ሶስት ሞት ። ነገር ግን ስቃዩ ይበዛ እንደ ሆነ እንጂ ሞት ምንጊዜም ቢሆን ያው አንድ ነው ። ስለዚህም ግራዝማች ተፈራ እሽቴን ለከሀ ዲዎች ሁሉ መቀጣጫ እንዲሆኑ በሁለት ጥይት ደግመናቸው እየፎከረንና እያቅራራን ወደ አገራ ችን ስንወርድ ገነት የምትሆነው ሁኔታ ባይነ ህሊናዬ ወለል ብሎ ታየኝ ..."

# አስራ ሰባት

“ግራዝማች ተፈራ እሸቴን ገለን ተመንገድ ምንም አይነት መሰናክል ሳይገጥመን ዞጋ ገባን ። ሰውየው የታወቁ ስለሆኑ መንግስት ተከታትሎ እንደሚያጠፋን ስለተገነዘብን የገባን እለት ማታ ቁርማንቁራችንን ጠቅልለን ወደ አባባ ሞገስ ፣ ጣሜ ሚካኤል ዘለቅን ። መቼም ሰድብ አይገድልም እንጂ የገነትን አባት በመግደላችን ማቱን አወረዱብን ። ብዙነሽን ተዚያ ጥለን በሌሊት ወደ ዞጋ ተመለስን ። እውነትም ከነፍስ መውጫ ጦር ታዞ ቤታችን ተቃጠለ ። አትክልታችንም እንዳልነበር ሆኖ ወደመ ።

“ግራዝማች ተፈራን ተገደልን ወዲህ በጋይንት የታወቅን ሽፍቶች ሆን ። በፊት እንደ ተራ ሽፍታ ነበር የምንቆጠረው ። አሁን ግን የገነንን በመሆናችን በመንግስት በኩልም ክትትሉ ጠነከረብን ። እኛም ፣ ተቆላው ታዩ ስንባል ተደጋው ፤ ተደጋው ናቸው ስንባል ተቆላው እያለን አስጨንቀን ያዘን ። መቼም ግራዝማች ተፈራን በመግደላችን ትንሽ ትልቁ ነው የፈረደው ። በየሸንጎው ሌላ ወሬ አልነበረም ። ተማስታውሰው ጥቂቱ ፡—

እንደ ጨዎች ሁሉ ይቅርታ አድርገው ፤
ትልቅ ሙክት ጥለው ጎረቤቱን ጠርተው ፤
ሲበላ ሲጠጣ ሲደሰቱ አምሽተው ፤
የክብር መኝታ ላማቻቸው ሰጥተው ፤
ተነጋ በኋላ የፍጥኝ አስሩት ልጃቸውን ጠርተው።
ለካስ መላ ኖሯል ያ ሁሉ ድለላ ፤
ጥዋውን አየነው ታንድ አመት በኋላ ።
እንዲህ ያለም የለ የተፈረደ ሞት ፤
ሟቹ ወደ ኋላ ገዳዩ ወደፊት ።
ሰዎች ተጠንቀቁ በናንተም እንዳይደርስ ፤
ጥሩ አይደለምና ታምኖ ቃልን ማፍረስ'

እየተባለ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይዘፈን ነበር ።

"የትም ዙረን ዙረን ጨለማን ለብሰን ታባባ ሞገስ ቤት ነው ማረፊያችን ። ስድብና ቁጣቸውን ተምንም ሳንቆጥር በልተን ጠጥተን ተለሊቱ ላይ ወይ ወደ ደጋው እንወጣለን ፤ ወይ ወደ ቆላው እንወርዳለን ። ልጅህን ታስወጣለህ ታስገባለህ ብለው የመንግስት ሹማምቶች ጧት መጥተው ይሰፍሩባቸዋል ።መገላገያውንም ፤ ሙክቱንም ይሉና ተስራት ይድናሉ ። ሁልጊዜ ሹም እንደቀለቡ ነው ።

"አንድ ቀን ምሽት አባባ ሞገስ ፤'መቼም የሚነግሯችሁንስ አትሰሙም ።እስቲ ወደ ደጋው

እንዳትወጡ ። የዚያች ልጅ ባል' አሉ ፣ አመልካች ጣታቸውን ወደ በሩ ቀስረው ። ገንትን ማለታቸው ነበር ፡ 'የዚያች ልጅ ባል መኸሬን ከትቼ ያማቴን ደም እመልሳለሁ እያለ ደፍ ደፍ ይላል አሉ ። ስለዚህም ወደ ዶጋው አገር እንዳትወጡ ። ተዚያው ተቆላው ብትሆኑ ነው የሚሻለው' በማለት አስ ጠነቀቁን ።

"እየውልህ ፤ ተዚያ በፊት የገንትን ባል ለመግደል አሳብ አልነበረንም ። አባባ ሞገስ እኛን ለመግደል አሳብ እንዳለው ሲነግሩን ሳያጠፉን ማጥፋት ያለብን መሆኑን ወዲያውኑ ተገነዘብነው ። ተለሲቱ ላይ አባባ ሞገስ ቃሌን አጥፈው ሄዱ እንዳይሉን ወደ ቆላው መመለሳችን ነው ብለና ቸው ወደ ዶጋው አቀናን ።

"አዲስ አንባ የደረስነው ተረፋዱ ላይ ነበር ። እረኞችን ስንጠይቅ አውድማ የጣለ መሆኑን ነገ ሩን ። በቀን ቦታውን ታረጋገጥን በኋላ ተዱር ውስጥ ተኝተን ውለን ጭልምልም ሲል ጉዞ ዠመረን ። እሩቅ ብለን ስንመለከት ያውድማው እሳት ቦግ ቦግ እያለ ይነዳል ። ውሻ በብላው አንጋዳ እያሳ በረን ተቃረብን ። ተእሳቱ ዳር ተቀምጦ ወዲያ ወዲህ ባይኖቹ ይቃኝና ጠላ ይጎነጫል ። መልሶ እየተዘዋወረ ያያል ። አይኖቹ ታንድ ቦታ አይ ረጉም ። በልባችን እየተሳብን ቱስሩ ስንደርስ አየን ። ፎከሮ ተጎኑ ያጋደመውን ጠመንጃ ብድግ ሲያደርግ ፣ 'የኮስትር ጌታ !' ብዬ ምላጭ ስስብ ተጉልበቱ ላይ ቀለጠመሁት ። ታጠገቡ ትልቅ

ድንጋይ ነበር ፤ ከብለል ብሎ ተዚያ ተጠጋ ። ደህና ዠግና ኖሯል ፤ አላስጠጋንም ። በረኸሮም አል ቤን ገትሮ ያዘን ። አንድ ጊዜ እንዳውም አስታ ጥቂ ሞገስን አበላሽቶት ነበር ። ጨርሰነው ፤ ጠመ ንጃውን ማርከን ለመሄድ ነበር አልተቻለንም ። ተኩሱ እንደ ተሰማ ደሞ ያገሬው ህዝብ ተመንደር መንደር ፤ ተንጥ ንጥ እየተቀባበለ እሪታን ያቀል ጠው ዠመር ። ህዝቡ ከበባ አድርጎ መውጫ በማ ሳጣት እንዳይዠን አልንና ይሞት ይድን ቁርጡን ሳናውቀው ጥለነው ሸሸን ። ''

# አስራ ስምንት

“በቆላው አገር ለሁለት ወር ያህል ቆይተን ወደ አባባ ሞገስ ጠሜ ሚካኤል ወጣን ። ማታ ፣ ‘እናንተ መቼም የምንግራችሁን አልሰማ ብላች ኋል ። ባለፈው ወደ ቆላው መውረዳችን ነው ብላችሁኝ የዚያችን ልጅ ባል ገደላችሁት ። ደም ብታበዙ ምን ያደርግላችኋል’ በማለት ተቆጡ ።

‘ሞተ እንዴ ?!’ አልኳቸው ።

‘ሞተ ፣ ጉልበቱን ኖሮ የመታችሁት መቅኔው ፈሶ ክፉኛ ተሰቃይቶ ሞተ አሉ ። እኔም በስተር ጅና ፈርዶብኝ በናንተ የተነሳ ዳኛ መከራዬን ያሳየኛል ። በሌላ በኩልም የደም መመለሻ እንዳ ልሆን እያልሁ ትጥቄን አልፈታ ፣ መሳሪያ ጨብጠ ሌሊት አልተኛ ፣ ቀን ስራ አልሰራ እንደ ባንንሁ አለሁ ። ተኔ ኑሮ ይልቅ እንደናንተው ለይቶለት ጫካ የገባ ይሻላል’ ሲሉ ተማረሩ ።

“ያባባ ሞገስ ቁጣ እየበረታ በመሄዱ ስለ ተባቀቅን ክረምቱ ተመግባቱ በፊት ተሰኔው ላይ አንድ ጊዜ ዘልቀን ክረምቱን በቆላው አገር አሳ ለፍን ። መስከረም ተጠባም ባንዘልቅ ቆይተን ጥቅምት ማለቅያ ላይ ሄደን ። አባባ ሞገስ ያለወ ትሯቸው በደስታ ተቀበሉን ። ቤተሰቡ በሙሉ

እኛን ሲያይ ደስታ ብቻ ሆነ ። የብዙነሽ ደስታማ አይነሳ ። ጠፍተን በመከረማችን ምክንያት እልን እንጂ ሌላ ነገር አላሰብንም ነበር ።

'ምነው በደህናችሁ ነው እልም ብላችሁ የጠፋችሁት ? ባጠያይቅም የደረሳችሁበት ጠፋ' አሉ ፤ አባባ ሞገስ ተተቀመጥነ በኋላ ።

'በደህናችን ነው ። አንተን ደሞ እንዳናስጠይቅህ ብለን ነው' አላቸው እስታጥቄ ።

'ትንግዲህ ወዲያማ ምኑን እጠየቀዋለሁ ? ነገሩ ሁሉ ቶርሽ ሆነ !' አሉ ፊታቸው ሁሉ በደስታ እንደ ተዋጠ ። እስታጥቄና እኔ ግራ በመጋባት ተያየን ።

'የምስራች ! ምህረት ተደረገላችሁ !' ሲሉን ይባሱን ግራ በመጋባት የምንናገረውን አጥተን አይኖቻችንን ወደሳቸው አፍጥጠን ዝም አለን ።

'ምነው ዝም አላችሁሳ ?' አሉን ።

'የምንለውኮ ጨንቆን ነው' አላቸው እስታጥቄ።

'ትንግዲህ ወዲያማ ምን ያስጨንቃችኋል መደሰት ነው እንጂ' አሉን ። ተዚህ በኋላ እየተነሳን ጫማቸውን ሳመን ።

'እንዳው ለመሆኑ እንዴት ተብሎ ነው ምህረት የተደረገልን'?' ሲል እስታጥቄ ጠየቃቸው ።

'ባዋጅ ነው ምህረት የተደረገላችሁ ። ባለፈው ሳምንት መንግስት እስር ቤት ላሉ እንዳንድ እስ

ረኞችና ነፍስ ገለው ጫካ ለገቡ ምህረት ሰጠ ፡፡ በቀደም ተዚያው ነፋስ መውጫ ነበረሁ ፡፡ ያው ራጃው ገኘ በዱር በገደል ያለህ ሽፍታ ግባ ፤ ተባለ ደምህ ጋር እየታረቅህ በሰላም ሰርተህ ኑር ፤ ብለው የመንግስትን ቃል ባዋጅ አስነገሩ' በማለት ተረኩልን ፡፡ በማግስቱ ነፋስ መውጫ ይዘውን ሄዱና ታውራጃው ገኘ አቀረቡን ፡፡ ያውራጃው ገኘ ብዙ የወቀሳና የማስጠንቀቂያ ንግግር ተተ ናገሩ በኋላ አባባ ሞገስ ለሁለታችንም ዋስና ተያዥ ሁነውን ምህረት ተደርጎልን በደስታ እየፈነጠዘን ተመለስን ፡፡

"እየውልህ ፤ ተነ አባባ ሞገስ ትንሽ ቀን ተተቀመጠን በኋላ በመዝመሪያ እኔና አስታጥቄ ወርደን ሰቀላ ነገር ቀልሰን ብዙነሽን ወሰድን ፡፡ ተዚህ በኋላ የሁለታችንንም ቤቶች ሰርተን ጨረ ስን ፡፡ ያትክልት ቦታችንንም አበጃጀነው ፡፡ ሁሉ ንም ወደ ቀድሞ ቦታው መለስነው ፡፡ ቀያችን የቀ ድሞ ለዛዋን አገኘች ፡፡ እንዲህ የሰላም ኑሮ መኖር ስንገርመር ገነት ትዝ አለችን ፡፡

# አስራ ዘጠኝ

“እየውልህ ፤ መቼም እኔ እንኳን የሰላም
ኑሮ መኖር ስጀምርና እንዳውም የገነት ነገር አይ
ሆንልኝም ። አጠያይቀን እንዳረጋገጥነው ገነት
ባሏ እንደ ሞተ ወደ እናቷ መጥታ ሳለ እናቷ
ደሞ ታመው ሞተባት ። ይህ የተደራረበ ሀዘን አን
በሳቁቧት ተዚያው ታቦቷ ቤት ተቀምጣለች ።
አሽከሮቹም እየጣሏት በየሰው ቤት ሄዱ ። ምን
ሉዲ እንኳን የጌታ አደረ ። የገለታ እናት ብቻ
ባልቴት በመሆናቸው ተሷው ጋር ነው ያሉት ።
ገነት ባዶ ባድማ አንቃ ሀዘን አንገቷን ሰብሯት
ተቀምጣለች ። ባል እንኳን እንዳታገባ የሸፍታ
ሚስት ተብላ የሚደፍራት አጣች ። በዚህ ላይ
ባሏ ሲሞት የሁለት ወር ነፍሰ ጡር ስለነበረች
አሁን ወንድ ልጅ ወልዳ ችግር ያንበሳቁላታል ።
ይህን የመሰለ አሳዛኝ ወሬ ስሰማ እራሴን መግ
ዛት አቃተኝና ላመጣት ቆረጠሁ ።

“እኔና አስታጥቄ ልናመጣት ስንሄድ ብዙ
ነው ሟንቀታችን ። እሽ ብላ ትመጣ ይሆን ? ወይንስ
እንደ ጠላት ታያን ? መቼም አባቷን የገደ
ልናቸውና ለሞታቸው መነሻው በሷና በኔ መፈ
ቃቀር ምክንያት ለኑሯችን ጠንቅ በመሆናቸ
ውና እኔን አሳልፈው በመስጠታቸው ነው ። ስለዚ

ሀም ገነት እንደ ጠላት ልትቆጥረን አይገባትም ። እንዳውም እናት አባቷ ሞተው ቤተ ፈት ሆና ፣ ቤተሰቡ ሁሉ ጥሏት ሄዶ ፣ ተባዶ ባድማ ተቀምጣ ስታገዘን እኛ ድርስ ስንልላት ደስ ሲላት ይገባል እያለን ነበር ።

"መጥፎውንም ፣ ደጉንም እያሰበን ዶሮ መስ ፈር ሲዝምር ደረስን ። ለማንኛውም ይጨልም አልንና ተዘ.ያው ቀረብ ብለን አመሸን ። ሰውም ከፍቱም ክትት ሲል ወደ ግራዝማች ተፈራ እሸቴ ግቢ ገባን ። አሽከሮቹ ብቻ ሳይሆኑ ውሾቹም ለጌታ አድረው አገኘናቸው ። ያለምንም እንቅ ፋት ሰተት ብለን ወደ እልፍኙ ስናመራ የሀ ጣን ልቅሶ ሰማን ። ቀጥሎ የገነትን ድምጥ ልጅዋን ስታባብል ሰማናት ። በሩ ገርበብ ብሏል። አን ዲት ባልቴት ተወደ ጓሮ በኩል ግብር ውሃ ወጥ ተው ዘገም እያሉ መጡ ። የገለታ እናት መሆ ናቸው ነው ። ጥግ ይዘን አሳለፍናቸውና ሲገቡ ተከትለን ጥልቅ አለን ። ገነት ልጅዋን መሬት ላይ ጥላ ተፈናጥራ ተነሳች ። ባልቴቷ ባሉበት ደር ቀው ቀሩ ። ጥቁረታቸው ወደ አመድነት ተለ ወጠ ። የያዙትን ቶፋ በቁማቸው ሲለቁት መሬት ላይ ተከሰከሰ ። እኛ ጠመንጃችንን ዘቅዝቀን እንግ ተን በፈገግታ ዝም ብለን ቆመን ። አሁን ታሁን ትስመናለች ወይንም ታናግረናለች ብንል አይ ኖቿየ ጎድን ማየታቸውን ትተው ወደኛ አፍጥጣ ዝም ብላ ቆመች ። ሀጣኑ ወደሷ እየዳኸ ያለቅሳል።

'ገነት አትስሚንም እንዴ?' ብዬ ወደሷ ስጠጋ።

'እንዳትጠጋኝ!' በማለት ፈንጠር አለች ።

'ባጠፋሁት ሁሉ ይቅር በይኝ' ብዬ እጅዋን ያዝ ሳደርጋት :-

'ልቀቀኝ!' ብላ እምዝገዘገችኝ ። በዚህ ጊዜ ቁጣዬ ብልጭ አለብኝና አይኖቼን ሳፈጥ ፤ 'ወግድ ተዋት!' አለና አስታጥቄ እኔን ገፋ አድርጎ ፣ 'ገንት መቼም ያለፈ አልፏል ። ለሞተ ነገር መጠጠት አይገባሽም ። ምህረት አድርጊልን ልንወስድሽ ነው የመጣነው' ሲላት ፤

'ገላችሁ እሬሳዬን መውሰድ ትችላላችሁ!' አለችው ። ተዚህ በኋላ ልመናችንን ትተን እኔ ተመሬት ህፃኑን ሳነሳ አስታጥቄ ደሞ ገንትን ፣'እንግዲህ በክብር ብትሄጅ ይሻልሻል!' አላት ፣ ኮስተር ብሎ ።

'ግደሉኝ! ግደሉኝ እንጂ አልሄድም!' አለች ፣ እየተወራጨች ። ወደ ገሮዋ አስጠጋና ወደ ሰማይ አንድ ጥይት አጮኸባት ። እንኳን እሷ ህፃኑም ሲያለቅስ የነበረ ጭጭ አለ ። ባልቴቷ አይኔ አይይ ብለው በጆቻቸው ፊታቸውን ሽፍን አድርገው በመዝጊያው ስር ሽጉጥ አሉ ።

'ምራ!' አላት አስታጥቄ ፣ አይኖቹን አፍጦ ። ትንፍስ አላለችም ፤ መሰስ ብላ ወጣች ። ያጥሩን በር ስንወጣ የመንደሩ ሰው፣'የምን ተኩስ ነው?' እያሉ እሽሽሹ ሲጠያየቅ እኛ ተሰወረን ።

"ግማሽ ጨረቃ ነበረች ። ገንት ፊት ፊት ቅሰግራለች ። ህፃኑ ተደረቴ ላይ እንዳለ እንቅ

ልፍ ይዞት ሄደ ። የጥይቱ ድንጋጤ አሁንም አሁንም ያባንነዋል ። ሰውነቱ ስለ ዛለ ዝቁጥቁጥ እያለ ላያያዝ ስላስቸገረኝ አስር ጊዜ ከፍ ዝቅ አደርገዋለሁ ።

'አስታጥቄ ልጁ ተኝቷል በደንብ አስይዘኝ' አለሁት ፤ ቆም እያለሁ ። 'ተኛ እንዴ ?' ብሎ ሊያሲዘኝ ሲል፡—

'አምጣ ልጄን !' ብላ ገነት መንጬቀችኝ ። በዚህ ጊዜ ህጣኑ ተንቅልፉ ነቃና ያስቅስ ጀመር ።

'አይዞህ ማሙሽ !' እያለ በነጠላዋ አሳዘላት ። አንቀልባዋን እረስተንዋል ። ልጁን እንዳይበርደው ብዬ እኔ በኮት ሁኜ ነጠላዬን ሲደርብላት፣—

'ያንተን ልብስ አልፈልግም !' ብላ አውልቃ ወረወረችው ። ሳቅ ብዬ ነጠላዬን አንስቼ ለበስሁ ።

"እኩለ ሌሊት ላይ ጨረቃዋ ጥላን ጠፋች ። ተዚህ በኋላ እየተደናቀፍን ጉዟችን የጉንዳን ጉዞ ሆነ ። ወደ ገነት ጠጋ እልና ፤ 'በዚህ ነዩ እሱ እሾህ ነው 'ብዬ' እጅዋን ያዝ ሳደርጋት፣—

'አትንካኝ ብየሃለሁ!' ትልና ትወራጫለች። እኔን የጎዳሁ እየመሰላት አትሂጅ ባለኋት ስትሂድ እሾህ ይወጋታል ። ወይንም እንቅፋት ይመታታል። አስታጥቄ ደገፍ ሲያደርጋት እሱን አትናገረውም። እንዲህ እያለን ተብርሃን ደረስን ።

"እስኮብልያት ሳለ ተኝተንበት በዋልነው ጫካ ስናልፍ ፤ 'ገነት ያን ጫካ ታስታውሽዋለሽ?'

ስላት ሳመል ያህል መለስ ብላ አይታ መንገዷን ቀጠለች ። ፊቷም አልተፈታ ። ጥረቴ እንድታናግረኝ ነበር ፤ አልሆነም ።

‘‘እየውልህ ፤ እኩለ ቀን ላይ ተቤታችን ደረስን ። ብዙነሽ እየተርገበገበች አቀፈቻት ። እሷንም እንደኛ ታኮርፋት ይሆን ስንል ሳመቻት ። ብቻ ብዙነሽ አስሩን ስትለፈልፍ ገነት አንድ ቃል አልተናገረችም ።

‘‘ማታ የነ አስታጥቄ ሞገስ ልጅ ጓደኛ በማግኘቱ ተደስቶ ቤቱ ጠቦት ይቧርቃል ። የገነት ልጅ እንግዳ በመሆኑ ተናቱ ጉያ ለመውጣት አልፈለገም ። የልጁ ጫዋታ ይስበውና ትንሽ ወጣ ይልና ሳቅ ብሎ መልሶ ወደናቱ ጉያ ሽጉጥ ይላል። ገነት ሳት ብሏት አንድ ጊዜ እንኳን ሳትናገር የመኝታ ሰአት ደረሰ ። ወደ ቤት ቀድሜ በመሄድ መኝታችንን አንጣጥፌ ተመልሼ ሂጂ እንሂድ ስላት፣—

‘አልሄድም ፤ ተዚሁ እተኛለሁ’ አለችኝ ።

‘‘አንጀቴ ቁርጥ አለ ። የልቧ ይድረስ ብዬ ግትር አላልሁም ። መለስ ብዬ ሂጄ ተኛሁ ። እንቅልፍ የሚባል ነገር አልሞከረኝም ። የሌሊቱ መርዘም ፣ የጨለማው ክብደት ፣ የቁንጫው ብዛት፣ ያልጋው ጉርባጤ እንዳው በፊት ያልተሰማኝ ሁሉ ያንለት አሰቃየኝ ። ቁስና መነኩሰ ያቃቱ ባልና ሚስት አልጋ ያስታርቃቸው ነበር ። የቀኑ ተስፋዬ እመኝታ ላይ እንወቃቀሳለን ነበር ።ባይ

ሆነ ቀረ ። መንጋት አይቀርም ስወድቅ ስነሳ ነጋ። ጧት ብዙነሽ ለኔና ላስታጥቄ ቁርስ አቅርባልን በልተን ስናበቃ ፣ 'በሉ እንግዲህ ዘወር ዘወር ብላ ችሁ ተመለሱ ! ስራ እንስራበት ቤቱን ለቀቅ አድ ርጉልን' አለችን ። እንዳለችን ተቤት ወጥተን ወደ ወንዙ ወረድን ።

"ተቀኑ ላይ ወደ ቤት ስንመለስ ገነት ተዚ ያው ተነ አስታጥቄ ቤት ናት ። ህጣኑ ተገንግኖ ወጥቶ ተግገኑ (ከወለሉ) ተልጁ ጋር ይጫወታል። እሷም ወደ ምድጃው ቀረብ ብላ የተጣደ ድስት ታማስላለች ። እንደ ተቀመጥን ብዙነሽ ለኛ ብቻ ምሳ አቀረበች ።

'ምነው እናንተ አትበሉም እንዴ ?' አላት አስታጥቄ ።

'እናንተ ብሉ ! እኛ ምኑንም ምኑንም ስንል ነው የዋልነው' አለችው ብዙነሽ ።

'የምን ምኑም ምኑም ነው ? ቲጣ ወይንም ገንፎ አትይንም' አለ አስታጥቄ ፈገግ ብሎ ።

'አዎን ፣ ገንፎ በቅቤ !' አለችው ፣ ብዙነሽ ዘርዛራ ጥርሶቿን ገለጥ አድርጋ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ገነት ትንፍስ አላለችም ። እኔም የሷ የተጋባብኝ ይመስል ቀዘጋሁ ።

"ማታ እራት በልተን ስናበቃ እንሂድ ሳል ላት ወጥቼ ተቤቱ ገብቼ ተኛሁ ። ለምን ነው እን ዲህ መጨከኗ ! እያለሁ ሳስብ ፣ 'እንቅልፍ ወሰ ደህ እንዴ መሀሪ ?' አለኝ ፣ አስታጥቄ ተበሩ ቆሞ።

‘እ/ረ አልወሰደኝም ፤ አለሁኝ’ እለሁት ፣ ተራቤ ቀና እያልሁ ።

‘በሩን ከፈተው’ አለኝ ። ታልጋዬ ወርጂ በሩን ስከፍተው ገነት ልጅዋን ታቅፋ ተጓላው ቁማ ለች ። ‘በይ ግቢ’ አለና እሷ እንደ ገባች ፣‘በሉ ደህና እደሩ!’ ብሎ መለስ አለ ። እኔ በሩን ዘግቼ ስመለስ ታልጋው ወጥታ ልብሷን ሳታወልቅ ፊቷን ወደ ግድግዳው በማዞር ተጠቅልላ ተኛች ። ጋቢ ዬን ጫን አድርጌ ቀስ ብዬ ተጠጋኋት ። ለማቀፍ ግን አልደፈረሁም ። ቁንጫ የበላኝ እየመሰለሁ እንደ መገላበጥ እልና በጉልበቴም ፣ በክርኔም እጎሻሽማት ገርመር ። እንቅልፍ የወሰዳት መሰላ፣ ትንፋሿን ዋጥ አድርጋ ለጥ አለች ። ስፈራ ስቸር እጇን በሽንጧ አሳለፈሁት ። ትመነጭቀኛለች ስል ዝም አለችኝ ። ህጣኑ ተደረቷ ልጥፍ ብሎ ጡቷን ይመጠምጣል ። ሳዋዛት ቆየሁና ወደኔ ጠጋ ሳደርጋት ልጁ ጡቱን ለቀቀና ሁጭጭ አለ።

‘እንካ!’ ብላ ጡቷን አስያዘችው ። እንቅ ልፍ እስቲወስደው ድረስ ዝም ብዬ ቆየሁና ዳሰስ ሳደርገው ጡቷን ለቆ ኩርሽ ብሏል ። እንደ መሰ ራሸት አለሁና ፣ ‘ገነት ዞሪና እቀፊኝ እንጂ’ ብዬ ወደኔ ለማዞር ገልበጥ ሳደርጋት፣—

‘እርፈህ ትተኛ እንደሆነ እርፈህ ተኛ! አለ ቧለዚያ አልጋህን ለቅቄልህ ተግገኑ ወርጄ እተኛ ለሁ!’ ስትለኝ ፣ ሰሜቴ ሁሉ ሙሽሽ አለ ። ትንሽ እንኳን አላንገራገረኋትም ፤ ፊቴን እዞሬ ተጠቅ ልዬ ተኛሁ ። ዥርባና ዥርባ እንደሆነ ነጋ ።

'ጫት አስታጥቂ ሞገስ ፣ እንዴት ነው እርቅ አደረጋችሁ?' ሲል ጠየቀኝ ።

'ኧረ የለም ። እንዳትነካኝ አለችኝ ። ያለፍ ላጎቷ መታገሉ እርባና የለውም ብዬ ተውኳት' ስለው :—

'ፈሪ! ሴቶች ምን ጊዜም ቢሆን መግደርደራ ቸው የማይቀር ነው ። እንደ ምንም ብለህ ... ብቻ እንዳለኸው በግድ መታገሉ ጥሩ አይደለም ። እንኳን ታገስህ' አለኝ ። ወደ አትክልቱ ሄደን ተዚ ያው አርፍደን ስንመለስ ገነት ተቤት ድስት ጥዳ አገ ኘኋት ። መቼም ቢሆን ወንድ ተወደ ደጅ ሲመጣ በር ተከፍቶ ሲቆየው ደስ ይለዋል ። ስለዚህም እጅግ አድርጎ ደስ አለኝ ። ድስት ጥዳ ወጥ መስ ራቷም የመልካም ነገር ምልክት ነው። ልጅዋም ታጠ ገቧ ተቀምጦ ይጫወታል ።

'ማሙሽ' ብዬ ልታቀፈው ጎንበስ' ስል፡—

'ልጄን አትንካ !' ብላ አፈፍ አደረገችው ። ደስ ብሎት የነበረው ፊቴ መልሶ ሽምቅቅ አለ። ባድራጎቷ እያዘንሁ ተመደቡ ላይ ተቀመጠሁ ። ምሳ ለኔ ብቻ አቅርባ ፈንጠር ብላ ተቀመጠች ።

''ነይ እንጂ አብረን እንብላ አልኳት ። መል ስም አልሰጠችኝ ። እሷ ተቀምጣ እኔ ብቻዬን መብላቱ ደስ አላለኝ ስላለ ሁለት ጊዜ ያህል ጎራርሼ እጇን አባበስሁ ።

"እየውልህ ፤ ፍቅርና መተሳሰብ ተሌለ የሚ ወዷት ሚስትም ብትሆን አባ ጩጓሬ መስላ መታ የቷ የማይቀር ነው ። የቀድሞዋ ገነት አልመሰ ለኝ አለች ። ሰውነቴ ስለ ተሳቀቃት እጅግ አደርጊ ፈራኋት ። አብሮ ባንድ አልጋ መገዳደሙ የሚያ ስማማን መስሎኝ ነበር ፤ አልሆነም ። ለካስ ፍቅርና መተሳሰቡ ኖሯል የሚቀድመው ። ሰውነትም የሚሞቀው ፍቅር ሲኖር ነው ።ተበረዶ በልጣ ቀዘቀዘችኝ ። እኔ ምን ያህል ቀዝቅገሮት ይሆን ? ለጥሩ ባልና ሚስት ልብሳቸው ፣ተብርድ የሚከል ላቸው ፍቅር እንጂ ጨርቅ አይደለም ።

"ተገነት ጋር ሰላም አጣን ። ያስታጥቂ ዋሽ ንትም ልቧን አልከፍተው አለ ። ጧት ማታ ማል ቀስ ፣ መነጫነጭ ሆነ ስራዋ ። የብዙነሽ ምክር ፣ ያስታጥቂ ቂጣ ፣ የኔም አንገት ደፍቶ ማበን ጨርሶ አላስታገሳትም ። ቢጨንቀን አስታጥቂና እኔ ድንጋይ ተሸክመን ተግሯ ላይ ወድቀን ባለፈው ሁሉ ይቅር እንድትለን ለመናት ። ፈጥሞ ልቧ አልሻረም ።ኢስር ጊዜ ፣ 'ወይኔ ሴት መሆኔ!' ነው ። ይህ ሁሉ ሲሆን አንድ ነገር አልናገራትም ። ወጥቼ ወደ ደጅ እሄዳለሁ ። ወይንም ተጠቅልዬ እተኛለሁ ።

"እየውልህ ፤ ገነት እጅግ አድርጋ ሀዘን አበ ዛች ። ብስጭቷ ጎዶቷ ተመጠን አለፈ ። እኔም የማደርገው ነገር ጨነቀኝ ። ባልና ሚስት ችግራ ቸውን ሲወያዩ ፣ ብሶታቸውን ሲካፈሉ ፣ ደስታቸ ውን ደስታ ሲያደርጉ ነው ወጉ ። እኛ ግን እንደ

ዚህ አልሆንም ። የነሪያ እንተያየለ ጊዜ በተለያዩ
ከንፈሯን መንከስ ፣ ጊዜ እንተለን ያፍኔ መተየት
ዘገ ሆነ ። ውዩ ሰባ እያተሰተተበ ነው ። ሃሳ
ሆኖም ትን አያናግራትም ። እንደዚያ በሙ ያለት
ገዳይ ጋር አብሮ ይኖራል ነ' ተሰና በባ በሳ
መቃጠል ። በዚህ በኑል እማባበ አለት ። ሃሳቤም
ቢሻው ። አባቷን ገድሏ እሱና ጊዜ ባሉና ማለት
ሆነን በሰላም አብረን የመኖራችን ነገሩም
አልታይህ አለኝ ። የራት ሌባ ወያኔል እያለኝ ።
ምነው ሰዉ ሰንል ያን ጊዜ ስመንጃዋን ባያ ነሃ
ቀን አባቷን ሳንገድል በተወለደበት ቀን ። እያሰ
ጠጠት ገባኝ ። ማን ምን ያውቃል ! እንደዚ ጊዜ
ሆኗል ።

“ግኑት እያሄር ሰውነቷ አለቀ ። እንደ ሁለ
ሟሟች ። ያ—ያ፡በ፡ሽበ፡ሸ ገላዋ ተናዳ አለዱ ዋጋ
ረቀ እንጨት ሆነች ። ወይ ሰንዳ አመድ ሣለባ
ሱባት ትመስላለች ። አያናዷ ነያስ ፣ ግርጌም
የጠጡ ፤ ሰትራመድ መንተል መንተል ንያለቻ
ነው ። አፍንጫዋን ቢያሄት ትተነፈሳዋ ህቅ
የምትል እየመሰለች ሄደች ። እንዳም እሷን ባየሁ
ቁጥር የማደርገውን አጣለሁ ። ተበሳጭ ሁሉ ተማረ
አለቀ ። አውጥቼ ፣ አውርጄ ታሰብሁ በኋላ ወዲ
ገሯ ልመልሳት ቆረጥሁ ። ያለንን ሀብትን ላበቃ
ጥቂ ሳማከረው ፣ ‘በል አርፈህ ተቀመጥ ። አሁን
ሁሉንም ነገር ትረሳለች’ በማለት ተቆጣኝ ።

‘ምኑን ትረሳዋለች ፣ እየባሰባት ። የለም አለ
ታጥቄ ገንትን እንዳቷ አላየሁትም ። ያውቃዋ ሀሉ

ሌላ ነው ፡ ልጅዋን ይዛ ቦሰላም ብትሄድ ይሻላል ። ሰውነቷም በብስጭት አልቆ መንማና ሆናለች ። ጉንፋን እንኳን ቢይዛት አትተርፍም ። ግዴለህም አድርሻት ልመለስ' ብለው አይሆንም ብሎ ተቃ ወመኝ ። የሱን ምክር ለመጣስ ደሞ ከበደኝ ።

“አንድ ቀን ጧት እኔ ተመኝታዬ ገና አል ተነሳሁም ። እሷ ቀደም ብላ ተነስታ ተምድጃው አጠገብ ተቀምጣ በስንጥር እንጨት መሬት እየ ጫረች ታንጎራጉራለች ። እንቅልፍ የወሰደኝ መስዬ ተሸፋፍኜ አጮልቄ አያታለሁ ። አንዳንድ ጊዜ ቀና ትልና ወደ ውጪ በሩቁ ታያለች ። ሀሳቧም እንዲሁ እርቆ ይሄዳል ። በዚህ ላይ እንዳለች ብዙ ነሽ ገባች ። ትካዜዋ የተለመደ ስለሆነ ምን ሆን ሻል አላለቻትም ።እሳት ጭራ ልትመለስ ስትል ፤ ‘ብዙነሽ ፤ ህልም አይቼ ነበር ፤ ብነግርሺ ትፈቻ ለሽ?’ አለቻት ።

‘እንዴት ያለ ህልም አየሽ ? እስቲ ንገሪኝ' ብላት በገል የያዘችውን እሳት መልሳ በማስቀ መጥ እሷም በርከክ አለች ።

‘እየውልሽ ፤ ተመሀሪ አምልጬ ይመስለ ኛል ፤ እየተርገበገብሁ እሮጣለሁ ፤ እሱ ሊይዘኝ ተኋላዬ ይሮጣል ። ያገኘኝ ሲል አመልጠዋለሁ ። ሊገለኝ ጥይት ይተኩስብኛል ። መታኝ እልና ውድቅ እላለሁ ። እሩጠ ሊያንቀኝ ሲል ተነስቼ አመልጠዋለሁ ። በንደዚህ ሁኔታ ሲያሳድደኝ ታንድ ዋሻ ውስጥ እገባና ፈጣሪዬ አውጣኝ ! ተመሀሪ

ጋር መናገር አልችልም ። እኔ ሊነር ብልም ሰው አያስጥረኝም ። ያባቷን ገዳይ ባል አድርጋ ተቀመጠች እያለ ያነሳኛል ። ስለዚህ ቶሎ ገላግለኝ! ብዬ ሁለት እጆቼን ወደላይ ዘርግቼ ለመነሁት ። አይዞሽ ! እገላግልሻለሁ ! አለኝ ፣ ተዋሻው አናት ላይ ማራቶኝ ክንፎቹን ዘርግቶ በመቀመጥ ። በመጀመሪያ ሳየው ጥንብ አንሳ አሞራ መስሎኝ ነበር ። ወዲያው ደግሞ እንደሳት የሚንቀለቀል ነገር ሆነብኝ ። በአይኖቼ ጥልቼ ለማየት አልደፈርሁም ። በግንባሬ ተደፍቼ ማረኝ ፈጣሪዬ ! እያልሁ ተማፀንሁት ። አይዞሽ! አትፍሪ ! ቀና በይ! አለኝ ። ቀና ብዬ ሳየው የሀር ጉንጉን የለበሰ ፣ በደረቱ ጎራዴ የያዘ ቀይ ሰጋዬ ያበራል ። ደስ ብሎኝ ሳለ ወዲያው ደግሞ ተሰወረብኝ ። በዚህ ላይ እንዳለሁ መሀሪ ጠመንጃውን አቅምጦ ይዞ እያለከለከ ደረሰለ ። ተዋሻው በር ሆኖ ነይ ውጪ ብዬሻለሁ! ሲለኝ መሸሻዬ አጥቼ ስብረከረክ ሰው ተመስሎ የታየኝ የሀር ጉንጉኑን እንደ ለበሰ ፣ ጎራዴውን እንደታጠቀ ተራራ ላይ ተጋረጠበት ። መሀሪ ለመተኮስ ጠመንጃውን ሲያዞር እኔን ለመግደል እንጂን አቅም የለህም ። እስተዛሬ ያጠፋኸው ነፍስ አያበቃህም ! ብሎ በጎራዴው እንዳገዳ ጠመንጃውን ተወገቡ ላይ ቆምጦ ጣለበት ። በዚህ ጊዜ መሀሪ ደንግጦ ተጠማው ላይ ተደፍቶ ምህረት ሲለምነው ፤ በስተዛሬው ጥፋትህ ምህረት አድርጌልሃለሁ ። ወደፊት ግን ነፍስ ብታጠፋ አይቀጡ ቅጣት ነው የምቀጣህ ። እንዲውም መንኩሰህ ንስሃ መግባት አለብህ ። እሷን ግን ተንግዲህ ወዲህ አታ

ገኛትም! ገላግለኝ ብላኛለች ፤ እገላግላታለሁ!’ ብሎ ወደኔ መለስ በማለት በጎራዴው አማተበ። በዚህ ጊዜ ዋሻው እንደ ማእበል ተንገጫንጮ በላዩ ላይ ድርምስምስ ብሎ ድጭን አለ! ብንን ስል በህልሜ ነው ። እንደዚህ ያለ ቀፋፊ ህልም አይቼ አላውቅም ።ልጄን አልያዝሁትም ። ልጄን ይገፍው ቢሆን ኖሮ ይሻለኝ ነበር’ አለቻት ፤ ጭንቅ እያላት ። የብዙነሽ ፊትም ተከፍቶ አየሁት ። ሆኖም በመጥፎ አልፈታችውም ።

‘በመጀመሪያ ጥንብ አንሳ አሞራ ተመስሎ የታየሽ በኋላም እንደሳት የተንቀለቀለው ፤ በመጨረሻም የሀር ጉንጉን ለብሶ ፤ ጎራዴ ይዞ ያየሽው መልአክ ነው ። ዋሻውም መኖሪያ ቤት ይመስለኛል ። የመሀሪን ጠመንጃም መልአኩ ቆምጦ የጣለበት ዳግመኛ ነፍስ እንዳይገድልና በሰላም አብራችሁ እንድትኖሩ መሆኑ ነው ። ብቻ ደህና ህልም ነው’ አለቻት ። ገነት በብዙነሽ ህልም አፈታት አልተደሰተችም ።

‘በሰው ተመስሎ የታየኝ መልአክ መሆኑን እኔም አውቀዋለሁ ። እኔን ያሰጋኝ የዋሻው መደረማመስና የኔ ተዚያው ውስጥ መቅረቴ ።ወይ ወጥቼ ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር ። ለመሀሪም ተገናዲህ ወዲህ እሷን አታገኛትም ብሎታል ። ይህን ተናግሮም ነው ዋሻውን የደረማመሰው ። እንቺው መጥፎ ህልም ነው ! ይኸው ተነጋ በኋላም እንደ ቀፈፈኝ ነው ያለሁት’ ብላት ይበልጥ በትካዜ ተዋጠች ።

'አይዞሽ ፣ ቅዠትም ሊሆን ይችላል' ስትል ልታበረታታት ሞከረች ።

'ቅዠትስ አይደለም ። ቁልጭ ያለ ህልም ነው' አለቻትና አቋርጣው የነበረውን መሬት መጫር ገመረች ።

'በይ ! አይዞሽ ፤ ለህልም ደሞ ይህን ያህል መጨነቅ አያስፈልግም' ብላት እሳቷን ይዛ ሄደች።

"እየውልህ ፤ ገነት ያየችው ህልም እንኳን እሷን እኔንም አሳሰበኝ ። ጠመንጃዬን መልአኩ ለምን በጎራዴው ቆምጦ ጣለው ? ጠመንጃ ወንድ ልጅ ነው ይባላል ። እኔ ልሞት ወይንስ የገነት ልጅ ሀጣኑ ? እሷስ ዋሻ ውስጥ ገብታ ፤ ዋሻው ተደረማምሶ በዚያው መቅረቷ ለምን ነው ? ክፉኛ አብከነከነኝ ። ተረፋዱ ላይ ላስታጥቁ ስነግረው ብዙነሽ እንደነገረችው ነግሮኝ ፤ ፍችውን ግን አድበሰበሰብኝ ። ትክክለኛውን ፍች እንዲነግረኝ አጥብቄ ለመነሁት ።

'አንተ አርፈህ ተቀመጥ ! ቀን የምታስበውን ነው ያየችው ። ህልሙ መጥፎ ቢመስልም፤አንዳንድ ጊዜ የተገላቢጦሽ ነው የሚደርሰው ። ስለዚህ ህልም እልም ብለህ ተወው' አለኝ ። እኔን ለማጥ ናናት ያህል የተናገረው እንጂ እሱንም እንዳሳሰ በው ባሁኔታው ተረድቻለሁ ።

"ገነት ያን ህልም ታየችበት እለት ዝምሮ ላእምሮዬ ሰራ አልፈታም ነበር ። እሷም መብሰክ ሰኳ እየባሰባት ሄደች ።

"አንድ ቀን ተዋልሁበት ስመለስ ተምድ ጃው ዳር ተጠቅልላ ተኝታ አገኘኋት ። ጨርቅ ደራርባ ለብሳ ተላይ ተላይ ትቃትታለች ። ልጅዋ ተጉያዋ ተሸጉጦ ጡቷን ይመጠምጣል ። ባዶ ስለ ሆነበት ታፉ እያወጣ ፣ እያገባ ይብሰከሰካል ። ጎጆዋ ችን ቅገዝቅገዝ ብላለች ። የቤቱ እቃም በግገኑ ተል ከስክሶ ይታያል ።'ገነት ምን ሆንሽ? አመመሽ እንዴ?' ብዬ ብጠይቃት መልስ አልሰጠኝ አለች ። ቀን እንደዚያ ሆና መተኛቷ በጤናዋ እንዳልሆነ ገና ስገባ ነው የተረዳሁት ። ተመደቡ ላይ ቁርትም ብዬ ተመቀመጤ ብዙነሽ መጥታ ፣'መሀሪ ገነትን አሟታል ፤ ብርድ ብርድ አለኝ ነው የምትለው ። ምች ሳይመታት አልቀረም ። ና ታስታጥቄ ጋር ምሳ ብሉና የምች መድሃኒት ፈልጉላት' አለችኝ ። ሰውነቴ ክፍል አለ ። በምን ጎኗ እንደምትቋቋመው እግዜር ይወቅላት ። አስታጥቂም መጥቶ ፣'እግዜር ይማርሽ' ታላት በኋላ ምሳ በልተን የምች መድ ሃኒቱን ጫካ ሄደን ቅጠል በጥሰን ፣ ስር ምሰን አመ ጣንላት ። አስታጥቂ ታባባ ምገስ የተማረው የቅ ጠል መድሃኒት ሲሆን እኔ ደሞ ታባቴ የተማረ ሁት የስራስር ነበር ። የሁላታችንም ፍቱን መድ ሃኒት ነው ። ተዚያ በፊት ብዙ ሰው ፈውሰንበታል ።

"የኔን መድሃኒት በገል እሳት አድርገን አጠ ናት ። ያስታጥቂን ደሞ ቅጠሉን እየጨሞቀች ሰው ነቷን ብዙነሽ አሸችላት ። ተዚህ በኋላ ተጠቅ ልላ ተኛች ። ሌሊቱን እሳት ፣ ቅንጣት ሆና እንደ

በፊያዋት ፣ እንድያመጣቸ አንተ ። ሀገሬ በሰራ
ውሃ እመጠብቃለሁ ። ለውሳኔ ላይ እለውጣለሁ ።

“ያለ ነገር ሃገ እያዩለሁ ያመጣለ ። ሃገ በሀገ ቂር ተሰመጣኝ የሚጠመው ለሀ የሰራለ ያሁል ያሰተነልሉ ነገር" አሉ ፣ አለያዋቸዋ ቀር ተሰ ኛቸ ። እመናቀን ነው ። እኔም ያለን ነገር ተገናኘ በሙ ነገር ። ግን ቀንኘለ እለለሁም ፤ ቀለሚ በሀ ሀን ተሰብሮ …

“ያማጠብቀውን በኋላ ያደማሬን እስተማሪያት ። ተላይ ዮላይ ማያብሳ እያሳሰበት ሄደ ። እያቀያቸው ወደቀ ተሰሊመረበት ። እያለኝ ያደብለበ ፤ ነገ ፈርም ያርቀው ቀርፈት እበያተቀል ። ያማሬኝ ፣ ያበኝ ፣ እተሬተኝ ተለዋለት ። መመበራሲት ፤ መሰሌ ኒት ፣ መሀበት ያበች ። ባሬሞት ያተማቅቃል ፤ ያተቀረያት ለምን ቀለኸኝ ትሂዳለህ ? ያበኝ እተ ለተተኝ ፤ ተሰብ መተባሪክሪክ ፤ እኔም እተሬ መተ ሪክሪክ ። እንዲህ እያሆንኩት ፋታ ላታገኝ በሰተገ ተሚን ያበች ።

“እለላ እረሱ ነበር ። ተያራል ላይ እበያጉ ፊያት በማሬተኝ ከንያዊ እቅፌ ያገኙለሁ ። እግ ርሙን ቁልቁል ዘርግቶዋለች ። እበታቀቂ ባዙ ናብ ታሰጋቢ ተቀምጠው እንደኔው ያስማዘዘል ። ቁልቁል በመለከታት ትንፋሽ ተመበንበሻ የተ ሰየ ሆናበኝ ። እያደያችም ትዘቅቃ ዝመር ። ላመል የሀል ልብ ተር ትር ትላለች ። እንበቄን ተደረደ ላይ ዝቅ በለሀት ። እበታቀቂ በዱብኛ ጎኔ መልሺ

ጠራረግሁት ። ብዙነሽም ስታለቅስ ጊዜ እሷንም ሰደባት ። ወዲያውም እኔን አስለቅቆ እሱ ታቀ ፋት ። ተፋት ለፊቷ ተቀምጬ ፡ ‘ገኒት ፡ ገንዬ’ ብዬ ጠራኋት ። ቀስ ብላ ገርበብ ያሉትን አይኖቿን ገለ ጠቻቸው ። ድልህ መስለዋል ። ትክ ብላ አየችኝ። አንድ ነገር የምትፈልግ መሰለችኝና ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብዬ ፡ ‘ምን ላድርግልሽ ፡ ገንዬ ?’ ስል ጠየ ቅኋት ። ራሷን ነቀነቀች ። እጄን ጠበቅ አድርጋ ይዛ ልሳኗ መናገር ተስኖት ድምጧ እየተቆራረጠ፡ ‘መሀሪ እኔ ይቅር ብዬሃለሁ ። የልጄን ነገር አደ ራህን ። አባቱንና አያቱን ገለህበታል ። እኔም መሞቴ ነው ። አባትም ፣ እናትም ፣ ሆነህ አሳድ ገው ። በመሬት የሰጠሁህን አደራ በሰማይ እቀ በልሃለሁ’ ብላኝ እጆቿ ዛል አሉ ። አይኖቿም መልሰው ተከደኑ ። ተዚህ በኋላ እንባዬን መግ ታት አልቻልሁም ። ብዙነሽም እዬዬ ትል ገ፲መር።

“እኩለ ሌሊት ሲሆን ከአስታጥቄ ላይ ተቀ ብዬ እንደታቀፍኳት አንገቷ ዝንፍል አለብኝ ። ቀና አደረኳት ። የለችም ፤ አርፋለች! እየውልህ ፤ መከራዋን ተሸክሜ እኔ ቀረሁኝ ። እስካሁንም አለሁ” አሉና አባ መሀሪ አንገታቸውን ደፉ ። ከፊታቸው ላይ መሪር ሀዘን ይታያል ። እኔንም በታሪ ካቸው ወደ ኋላ ስበው ስለ ወሰዱኝ ጭንቅላቴ ተበጠበጠ እጅግ አድርገው አሳዘኑኝ ።

“እየውልህ” አሉኝ ፣ ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው ፤ “እየውልህ ፤ የገኒትን ህልም የፈታነው እሷ ተሞተች በኋላ ነበር ። ተዋሻው ውስጥ

ፃብቷ ዋሻው ተደረማምሶ በዚያው መቅረቷ
ለካም መቃብር መግባቷ ኖሯል ። የኔንም ጠመ
ንጃ መልአኩ ቀልጥሞ የጣለው ፤ በቃህ ሲለኝ
ዳግመኛ ነፍስ እንዳላጠፋ ነበር ። እየውልህ ፤ ተገ
ነት ሞት በኋላ እንኳንስ ሰው አውሬ አልገደል
ኩም ። እርም ብዬ ተውሁት ። ተቧ ሌላም ሚስት
አላገባሁም ። በልጅነቴ መልኩሼ ቀረሁ ። ልጅዋን
አደራ እንዳለችኝ ፤ አደራዋን ተወጥቻለሁ ። እንደ
ናት ባንቀልባ አዝዬ ፤ እንዳባት አሽኮኮ ብዬ
በማር በወተት እቀማጥዬ አሳደግሁት ።በዚህ በኩል
ያስቃጥቄና የብዙነሽ ውለታ የሚዘነጋ አይደለም ።
እየውልህ ፤ ድሬ ፣ ኩዬ ለወግ ለማረግ አብቅቼዋ
ለሁ ። ዛሬ የሶስት ልጆች አባት ነው ። ሰሙን ካሳ
ብዬዋለሁ ። ካሳ መሀሪ ።ለእኔም ያለኝ ጧሪ ፣
ቀባሪዬ እሱው ነው ።የሚኖረው ተዚያው ዞጋ ተና
ስቃጥቄ ጋር ነው ። አስቃጥቄና ብዙነሽም እንደኔው
ሽምግለዋል ። እኔ እድሜ ሲሜንኝ ጊዜ ንስሃ ለመግ
ባት ስል ቃገሬ ገዳም መጥቼ ገባሁ እንጂ ልጄ እንድር
ቀው አይወድም ነበር ። በየጊዜው እየመጣ ይጠ
ይቀኛል ። እኔም እየሄድሁ እጠይቃቸዋለሁ ። ”

አሁን አባ መሀሪ ሲያወሩኝ ደስታ ተላብሰው ፣
ፈገግ ብለው ነው ። እኔም እሳቸውን ሳይ ፈገግ
አልኩኝ ።

“ዛሬ ስራዬ እየዞረሁ መስበክ ነው ።ጥቁር
ደም መጥፎ ነው ፣ ልጄ ፤ በተወለድህበት አገር
እያኖረህም ። ብኩን አድርጎ ነው የሚያስቀርህ ።
መወገዝ ያለበት መጥፎ ልማድ ነው ። ሰው በስህ

ቶት ነፍስ ሲያጠፋ ይችላል ። ይህን በሰላም ፣ በርቅ መፈጠም ሲገባ ባጉል ፣ የዋህነት ዘር እየተቆጠረ ባልዋለበት ፣ በሌለበት እንዳወሩ እየታደነ ይገደ ላል ። ስለዚህ እንዱ ችግር ወጉ ልማዱና ባህሉ ነው ። ደም ታልመለስህ ባገር አያኖርህም ። ተዘፈን ዘፈን ፣ ተሀዘኑ ሀዘን ፣ ተደበቃው ደስቃ እኩል መካፈል አትችልም ። ምንጊዜም ቢሆን አንገት ህን ደፍተህ ተሸማቀህ ነው የምትኖረው ። ባሽ ሙር ይበድቡሃል ። ይሳለቁብሃል ። መልስ ከሰጠሃ ቸውም ፣ 'የወንድምህ ገዳይ እኔ መሰለሁህ እንዴ ? ሂድና ተዚያ ፈልገው' ይሉሃል ። እልህ ያስገቡ ህና የማትፈልገውን ነገር እንድትፈፅም ያደርጉ ሃል ። ተዚህ በኋላም በሰላም እንደማትኖር ስታ ውቀው ተስፋ ትቆርጥና የበለጠ ደም ታፈሳልህ ። ጫካ የገባ ሰው አውሬ ማለት ነውና አውሬ ትሆናለህ ። እኔ ይህን ሁሉ ደም ያፈሰስሁት ባገር መቀመጫ አጥቼ ነው ። ሌላው ቀርቶ አባቴ ሲያስ ቀምጠኝ አልቻለም ። ለሱም ወዶ አይደለም ። በተበኪዮን መሳሚያ አጥቶ ነው ። መወገዝ ያለ በት እንዲህ ያለው ብልሹ ልማድ ነው ። ነፍስ መግደል ባህልም ፣ ወግም አይደለም ። አውሬነትና ድንቁርና ነው ። የሰላም ጠንቅ ነው ። አንተም ባገ ኘኸው ሁሉ ንገርልኝ ። ቁምነገር ያለው ታሪክ ይመስለኛል ። ሰዎች ሁሉ ይስሙት ፣ ይወቁት ። እኦ ተንግዲህ የቀረኝ ነገር የለም ። ልጤ የተራበ ጉድጓደ የተማሰ ሽማግሌ ነኝ ። ኖስቴለኝ ድረስ ግን እንዲህ አይነቱን ብልሹ ተግባር ሰዎች እን ዲያውቁት ፣ አውቀውም ስህቀት እንዳይሰሩ እየ

ዞርሁ እነግራለሁ ። በል እንግዲህ አስገዝምረህ ስላስጨረስኸኝ ከፍ ቃለ ደረጃ ላይ ያድርስህ !"
በማለት መርቀውኝ ታሪካቸውንም ጨረሱልኝ ።

አባ መሀሪን ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናብቻቸው ገዳሉን ስወጣ በአእምሮዬ የሚመጣብኝ ፣ "ጥቁር ደም" ያሉኝ ነው ።እውነታቸውን ነው ። የበከተና ጥቀርሻ የሆነ ተግባር ነው ። ለሞተው ማዘን ሲገባ ሌላውን ያለ ስራው በተወለድሽኝ ዘር እየቆጠሩ መግደል ርካሽ የሆነ ልማድ ነው ። ይህ በከንቱ የፈሰሰ ደም በኔ አእምሮ እንዳቃጨለ ሁሉ በሌሎች ሰዎች ዘንድም እንዲያቃጭል ላገኘሁት ሁሉ እነግራለሁ ። አባ መሀሪ ከፍተኛ አደራ ጥለውብኛል ። ወንድማማችነት እንጂ ዳግመኛ "ጥቁር ደም" የሚባል ነገር አይኑር ....





## ጥቁር ደም . . .

« . . . ጥቁር ደም መጥፎ ነው ልጄ! በተወለድክበት አገር አያኖርህም ። ብኩን አድርጎ ነው የሚያስቀርህ. . . ተሆዘኑ ሀዘን ተደስታው ደስታ እኩል መካፈል አትችልም ። ምንግዜም ቢሆን እንገትህን ደፍተህ ተሸማቀህ ነው የምትኖረው። ያገኘህ ሁሉ ባሽሙር ይሰድብሃል ይሳለቅብሃል። እልህ ያስገባህና የማትፈልገውን ነገር እንድትፈጽም ያደርግሃል። ተዚያ በኋላ በሰላም እንደማትኖር ስታውቀው. የበሰጠ የጥቁር ደም ቁራኛ ትሆናለህ . . . »

ሕትመት ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ

ዋጋው ብር 16.00